# ምዕራፍ ፮፤

## ጸሎት።

ጥያቄ፡- *ጸሎት፡ ምንድር ነው? ትርጉሙስ? ሊፈጸም የሚገባውስ፡ በምን መልክ ነው።*

መልስ፡- “ጸሎት”፡ “ጸልዮት” ከሚለው፡ ከግእዙ ጥሬ ዘር የተገኘ ቃል ሲኾን፡ *“ጸሎትሰ፡ ይእቲ፡ ተናግሮተ ሰብእ፡ ኀበ እግዚአብሔር ልዑል፡”* የሚለው ደግሞ፡ “ጸሎት፡ ሰው፡ ወደልዑል እግዚአብሔር የሚያሰማት ንግግር ናት፡” በሚል ቃል ይተረጐማል። የተቸገረ ሰው፡ ልመናውን፡ ለበላዩ እንደሚያቀርብ፡ የተበደለም፡ አቤቱታውን፡ ለባለሥልጣን እንደሚያሰማ፡ የተደረገለትም፡ ውለታውን፡ ለበጎ አድራጊው እንደሚያበረክት፡ ያገኘም፡ ደስታውን፡ ለሰጪው እንደሚገልጽ፡ እንዲሁ፡ ሰብአዊ ፍጡርም፡ ከፈጣሪው ፊት ቀርቦ፡ አሳቡንና ስሜቱን፡ ፍላጎቱንና ነገሩን የሚገልጽበት ሥርዓት “ጸሎት” ይባላል። በሌላ አገላለጽ፡ ጸሎት፡ ***በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ በተመሠረተ መንፈሳዊ አምልኮ፡ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት*** ነው።

“እውነት” እና “መንፈስ” የተባሉት፡ ኹለቱ ረቂቃን ባሕርያት፡ በንጹሕ የቅድስና ምግባራዊ ሃይማኖት ተዋሕደው ሲቀርቡ፡ ይህ ግንኙነት የሠመረ ይኾናል፤ ማለትም፡ ጸሎተኛውን፡ ከፍጹምነት የብቅዓት ማዕርግ አድርሰው፡ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ተገናኝቶ እንዲነጋገር ያደርጉታል። እነዚህ ሦስት ባሕርያት፡ ማለትም፡ *ሃይማኖት÷ እውነትና መንፈስ፡* ደግሞም፡ ሦስቱ አስፈጻሚዎቹ አካላት፡ እነርሱም፡ *ጠሪና ተጠሪ÷ ጥሪም፡* ኹሉም በየወገናቸው፡ በአንድነት መኖር አለባቸው። በቅድሚያ፡ *ጥሪውን* ለማድረግ፡ ***ሃይማኖት*** ሊኖር ይገባል፤ ቀጥሎ፡ ለጥሪው ምላሽ ለማግኘት፡ *ጠሪው፡* ***እውነተኛ*** መኾን አለበት፤ በመጨረሻ፡ የጥሪው ምላሽ መጥቶ፡ ግንኙነቱ ሲከፈት፡ ንግግሩ፡ መንፈስ ከኾነው፡ *ከተጠሪው፡* ከእግዚአብሔር ጋር፡ በ***መንፈስ ቅዱስ*** ይካኼዳል። ስለዚህ፡ ጸሎት፡ “እለ” ተብሎ፡ ሊፈጸም አይችልም።

ይህም ማለት፡ ጸሎተኛው፡ የሚያውቀውን÷ የሚያመልከውንና የሚያምነውን እግዚአብሔር አምላኩን ለማነጋገር፡ በቅድሚያ፡ በፈጣሪው ላይ ***ፍጹም ሃይማኖት*** ያለው መኾን አለበት! ስለዚህ፡ ተጠሪው አምላክ፡ ጥሪውን ሰምቶ፡ ለጠራው ሰው፡ መልስ ሊሰጠው እንደምን ይችላል? አይችልም። እንዲያውም፡ የግንኙነቱ መስመር፡ ጨርሶ አይከፈትም። አንድ ሰው፡ የሚፈልገውን ሌላ ሰው፡ በስልክ ለማነጋገር፡ በመጀመሪያ፡ የተጠሪውን ስልክ ቁጥር አውቆ፡ በትክክል ካልደወለለት፡ ስልኩም ሊደውል÷ ተጠሪውም፡ የመነጋገሪያውን እጀታ አንሥቶ፡ ጥሪውን ከተቀበለ በኋላ፡ ጠሪውን ሊያነጋግረው አይችልም።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣

## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እንዲሁም፡ በነፋስ ድምፅ (በradio)፡ ዜና ለመስማት፡ ወይም በነፋስ ሥዕል (በtelevison)፡ ድርጊቱን ጭምር ለማየት የሚፈልግ ሰው፡ ለኹለቱም ማቢያዎች፡ በየፈናቸው፡ የተመደበላቸውን መለያ ቁጥር እና/ወይም መስመር፡ አስተካክሎ ካላገኘና ካልከፈተ በቀር፡ ዜናውን ሊሰማ፡ ድርጊቱንም ሊያይ፡ ከቶ አይችልም፡ እንደዚያ ማለት ነው፡፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ ፍጡር፡ ፈጣሪውን፡ አምላኩን፡ እግዚአብሔርን የሚያገኝበት መስመር፡ አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም፡ *ሃይማኖት* ነው፡፡

ያ ጸሎተኛ (ጠሪው)፡ ሃይማኖት ያለው ከኾነ፡ ጥሪው ደርሶ፡ የመነጋገሪያው መስመር ይከፈትለታል፡ ይኹን እንጂ፡ ንግግሩ፡ በኹለቱ ወገኖች ግንኙነት፡ ሊጀመር ይችል ዘንድ፡ ራሱ ጠሪው፡ ***እውነተኛ፥*** የጥሪው ም ምክንያት፡ ***ከእውነት የመነጨ፥ በእውነት የሚቀርብና ለእውነት*** የሚውል መኾን አለባቸው፡፡ እንዲህ ካልኾነ፡ ማለትም፡ መስመሩ ቢከፈትም፡ የጸሎቱ ጥሪ፡ ወደተጠሪው አምላክ ሊደርስ፡ ወይም ተጠሪውን እግዚአብሔርን፡ ወደጸሎቱ ጥሪ ሊያስቀርበው አይችልም፡፡ አዎን! ተጠሪው፡ ራሱ፡ "እውነት" እና "የእውነት አምላክ" ስለኾነ፡ ጠሪው ፍጡር፡ እውነተኛ ኾኖ፡ ለእውነት ዓላማ፡ በእውነት ካልቀረበ፡ የፈጣሪውን ቃል ቀርቶ፡ ፍሊጋውን እንኳ ሊያገኝ ከቶ አይቻለውም፡፡ "እውነተኛ ኾኖ፡ በእውነት መቅረብ" ማለትም፡ የራስን ኃጢአተኛነት አምኖና የሌላውን በደል፡ ያለቂም በቀል፡ በይቅርታ ትቶ፡ ራስን በንስሓ አንጽቶና በሥጋ ወደሙ አጽንቶ፡ የሌላውን ሳይመኙ፡ ከፈጣሪ የተሰጠውንና በድካም ያመረቱትን፡ "ይበቃኛል!" ብሎ አመስግኖ መኖር ማለት ነው፡፡ "ጻድቅ" ወይም "እውነተኛ" የሚያሰኘው፡ ለዚህም ማዕርግ የሚያበቃው ይህ ሃይማኖታዊ ምግባር ነውና፡፡

በሌላ አገላለጽ፡ ጠሪው፡ የሚያቀርበው ጸሎት፡ እስከዚያች አፍታ ድረስ፡ ከፈጣሪው የተደረገለትን በጎ ነገር ኹሉ ባለማወቅ፡ ወደፊትም፡ ይኸው እየተደረገለት የሚቀጥል መኾኑን ባለማመን፡ የራሱ የግል ፍላጎት ብቻ እንዲፈጽምለት በመጠየቅ፡ "በጠላቴ ላይ እንዲህ አድርግበት!" ከሚል ሥጋዊ ስሜት የመነጨ መኾን የለበትም ማለት ነው፡፡ አለዚያ፡ ከዚህ ቀጥዬ የምጠቅስላችሁን መለኮታዊ ቃል ማስተሓቀር ይኾናል፡፡ ይኸውም፡-

*"ለጸሎት በቆማችሁ ጊዜ፡ በሰማይት ያለው አባታችሁ ደግሞ፡ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፡ በማንም ላይ፡ አንዳች ቢኖርባችሁ፡ ይቅር በሉት! እናንተ ግን፡ ይቅር ባትሉ፡ በሰማይት ያለው አባታችሁም፡ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም፡፡"* ደግሞም፡ *"በሰማይት ላለ አባታችሁ፡ ልጆች ትኾኑ ዘንድ፡ ጠላቶቻችሁን ውደዱ! የሚረግሟችሁን መርቁ! ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ! ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ! እርሱ፡ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ፡ ፀሓይን ያወጣልና፡ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ፡ ዝናቡን ያዘንባልና፡፡ የሚወድዷችሁን ብትወድዱ፡ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ* (ኃጢአተኞችስ)፡ *ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ፡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ* (ሃይማኖት የሌላቸውና አረማውያንስ)፡ *ያንኑ ያደርጉ የለምን?*

## ምዕራፍ ፫፤
## ጸሎት፡፡

*"እንግዲህ፡ የሰማዩ አባታችሁ፡ ፍጹም እንደኾነ፡ እናንተ ፍጹማን ኹኑ!" እንዲሁም፡ "ራሳችሁ አትበቀሉ! ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፡፡ 'በቀል የእኔ ነው፡ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ፡' ይላል ጌታ! ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ጠላትህ ግን፡ ቢራብ አብላው! ቢጠማ አጠጣው! ይህን በማድረግህ፡ በራሱ ላይ የእሳት ፍሕም ትከምራለህና፡፡ ክፉውን፡ በመልካም[፻፲፯] አሸንፍ እንጂ፡ በክፉ አትሸነፍ!" የሚለው ነው፡፡*

የጸሎቱ፡ ጥሪ፡ እንዲህ፡ በሃይማኖት ተመልሶ፡ ግንኙነቱ፡ በእውነት ከሠመረ በኋላ፡ ንግግሩ፡ *በመንፈስ ቅዱስ* መካኼድ ይጀምራል፡፡ ይህም ማለት፡ የሚታይ ወይም የሚዳሰስ ነገር ሳይኖር፡ ወይም፡ የድምፅ ማሰማትና የቃላት መለዋወጥ፡ የድጋም ማነብነብም ሳያስፈልግ፡ የሚቀርበው ምስጋና ኾነ ጥያቄ፡ ወይም ፍላጎት፡ ኹሉም፡ በረቂቁ ኅሊና ውስጥ እንኳ ሳይቀር ሊካኼድ ይችላል ማለት ነው፡፡ ነፍስ፡ በዚህ መልክ፡ የራሷን አካል፡ በንስሓ ጾምና በምጽዋት ምግባር አጽድታ፡ በሳሙናና በውኃ ያጸዳችውን ሥጋዊ አካሏንም፡ በንጹሕ ልብስ አጐናጽፋ፡ መላ ሰውነቷን፡ ለእግዚአብሔር ልጅነትና ለሥጋ ወደሙ ጸጋ ባበቃላት፡ በመንፈሳዊ አካሏ፡ እነሆ፡ ኹለንተናዊ ራሷን፡ በፍጹምነት አክብራ፡ በጸሎት፡ ከፈጣሪዋ ፊት ቀርባ ትነጋገራለች፡፡ በዚህ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ባሕርዩ የኾነችውን "እውነት"ን፡ በዚያች ሰውነት ላይና ውስጥ ስለሚያገኝ፡ በመንፈስ ቅዱስ አካሉ ያድርባትና፡ *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡ የሚየመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊየመልኩት ያስፈልጋቸዋል!"*[፻፲፰] የሚለው የጌታ ቃል መፈጸሙ ይረጋገጣል፡፡

### ስለጸሎት አስፈላጊነትና አፈጻጸሙ፡፡

ጥያቄ፡- *በመሠረቱ፡ ጸሎት፡ ለምን አስፈለገ?*

መልስ፡- ለዚህ ጥያቄ፡ በአጭር ቃል፡ አጠቃላይ መልሱን መስጠት ይቻላል፡፡ እርሱም፡ "ለማናቸውም ሥራ፡ ወጣኝና የሚያካኺደው፡ አንድ ሠሪ ሊኖረው እንደሚያስፈልገው ኹሉ፡ እለዚያ፡ ያ ሥራ፡ በሥራነቱ ሊቀጥል እንደማይችል ኹሉ፡ ለፍጡርም እንዲሁ፡ የፈጠረውና የሚያኖረው ፈጣሪ አምላክ ሊኖረው፡ ከዚያ ፈጣሪውም ጋር ያለማቋረጥ ሊገናኝ ያስፈልገዋል፡ ይህም መገናኛ፡ 'ጸሎት' ነው!" የሚል ይኾናል፡ እለዚያ፡ "ጸሎት፡ አያስፈልግም!" ብሎ ለማሰብ መሞከር፡ የፈጣሪን መኖር ወደመካድ ያደርሳል፡፡ ፍጡር፡ ከተፈጥሮ ባሕርዩ የተነሣ፡ አንድ ቀን፡ "ፈጣሪ አለ!" ብሎ ማመኑ፡ የፈጣሪው ማዳንና ጥበቃም፡ "አስፈልጎኛል!" የሚልበት ጊዜ መምጣቱ ስለማይቀር፡ ከዚያ ፈጣሪው ጋር፡ በኾነው መንገድ፡ በግድ መገናኘት ይኖርበታል፡፡ "ጸሎት" የምንለው፡ እንግዲህ፡ ይህን መገናኛ ነው፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡

## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ፍጥረተ ዓለሙ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፡ በምድር ላይ ከተመላለሱት የሰው ልጆች መካከል፡ ምንም ምን ይኹን፡ ማለትም፡ አረማዊዉም፡ የአሕዛብ ወገን የኾነው፡ ጣዖት አምላኪውና አንድ ዓይነት ሃይማኖት የሌለው፡ አምላክ አልባውም ቢኾን፡ በዚያ ሃይማኖቱ ምክንያት፡ ለሚያመልከው ኃይል፡ ጸሎቱን ከማቅረብ በቀር፡ "ጸሎት" አላስፈለገኝም፡ አያስፈልገኝምም!" ያለ፡ እስከኹንና አኹን፡ አንድም አልተገኘም።

"ጸሎት"፡ ለሰብአዊው ፍጡር፡ የቱን ያህል የሚያስፈልገው መኾኑ፡ ተረጋግጦ የተገለጸበት ድርጊት፡ በእውን ተፈጽሞና በግዘፍ ተከሥቶ የታየው፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት ባሕርዩ፡ ከአምላክነት ባሕርዩ ጋር ይገናኝበትና ይነጋገርበት በነበረው የጸሎት ምግባሩ መኾኑን፡ ማንኛውም ክርስቲያናዊ ምእመን፡ በቀላሉ ይገነዘበዋል። አዎን! "ጸሎት" የማያስፈልግ ቢኾን ኖሮ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እርሱ ራሱ ጸልዮ፡ እኛን "ጸልዩ! ስትጸልዩም፡ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ!" ባላለንም ነበር።

ጸሎት የሚያስፈልገን፡ የሰውነት ተፈጥሮአችን፡ በአንድ በኩል፡ በደካማ ጎኑ፡ ራሱን፡ ለከፋቱ ኃይል አጋልጦና አሳልፎ የሰጠ በመኾኑ፡ ዓቅመቢስነትና ግብዝነት ስለሚያጠቃው፡ ከዚህ ባሕርዩ ተላቅቆ፡ በሌላው በኩል ባለው፡ በጠንካራው ጎኑ ብርታትና ቆራጥነት ሊያንሠራራ ይችል ዘንድ፡ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኝ ለማድረግ ነው፡ ያ አስጠቂው ደካማ ጎናችን፡ ይህን ድጋፍ አግኝቶ፡ ሰውነታችን፡ ያን ክፉ ኃይል እንዲቋቋምና እንዲያሸንፍ ለማድረግ ደግሞ፡ ከዚያ የላቀውንና ድሉን የሚያጐናጽፈውን፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ መቀበል አለበት፡ ይህን መለኮታዊ ጸጋ የማግኛው ብቸኛ መንገድ፡ አዎን፡ "ጸሎት" ነው።

ስለጸሎት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት፡ ስለኃይሉም፡ እንዲህ የሚሉት፡ የጌታና የሐዋርያው ቃላት በሚበቃ አብራርተው ያስረዳሉ፡ ለዚህም፡ ቀዳሚ ኾኖ ሊጠቀስ የሚገባው ቃል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለዓለሙ መጨረሻና ዳግም ምጽአቱ፡ *"ጊዜው፡ መቼ እንደኾን አታውቁምና፡ ተጠንቀቁ! ትጉ! ጸልዩም! ...ድንገት መጥቶ፡ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ፡ ስለዚህ ትጉ! ለእናንተም የምነግራችሁን፡ ለኹሉ እላለሁ፡ ትጉ!"* ሲል የተናገረው ነው።

የእርሱ ሐዋርያ፡ ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፡ መንፈስ ቅዱስን ተመልቶ፡ በመልእክቱ የጻፈው ተከታዩ ቃል፡ እንዲህ ይላል፡- *"እንግዲህ ወዲህስ፡ በእግዚአብሔርና በኃይሉ ብርታት ጽኑ! የዲያብሎስን የተንኰል አሽከላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ ልበሱ! የምትጋደሉበት ስልፋችሁ፡ ከሥጋዊውና ከደማዊው ኃይል ጋር አይደለምና! ከሰማይ በታች ካሉ፡ የዚህም፡ የጨለማው ዓለም ገዦች፡ አለቆችና ሥልጣናት ከኾኑት፡ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊተ አጋንንት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ፡ ክፉውን ቀን ለመቃወም፡ ድል ለመንሣትም እንድትችሉ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ አንሡ! በኹሉም ፈጽማችሁ የጸናችሁ ኾናችሁ ለመገኘት፡ በኹሉ የተዘጋጃችሁ ኹኑ!*

# ምዕራፍ ፰፡
## ጸሎት።

"እንግዲህ፡ ወገባችሁን፡ በእውነት ታጥቃችሁ፡ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፡ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት፡ እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በኹሉም ላይ ጨምራችሁ፡ የሚንበለበሉትን፡ የክፉውን ፍላጻዎች ኹሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን፡ የሃይማኖትን መከላከያ ታጠቁ፤ የመዳንንም ራስ ቍር፡ በየራሳችሁ ላይ አጥልቁ፤፡ የመንፈስንም ሠይፍ ሰንግሉ (ምዘዙ)፤ እርሱም፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በምልጃም ኹሉ፡ ዘወትር፡ በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ፡ ስለቅዱሳን ኹሉ እየለመናችሁ፡ በመጽናት ኹሉ ትጉ፤"[፻፲፱]

ጥያቄ፦ ልንጸልይ የሚገባን፡ እንዴት ነው?

መልስ፦ ጸሎታችን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን መመሪያ የተከተለ ሊኾን ይገባል። እንደሌሎቹ ምግባሮቻችን ኹሉ፡ በዚህም፡ በጸሎታችን አፈጻጸም፡ በብርቱ ልንጠነቀቅ ይገባናል። ይኸው፡ የጌታ ቃል የሚለን እንዲህ ነው፦ "ስትጸልዩ፡ እንደግብዞች አትኹኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ፡ በምኵራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና። እውነት እላችኋለሁ፤ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን፡ ስትጸልይ፡ ወደእልፍኝህ ግባ፤ መዝጊያህንም ዘግተህ፡ በሥውር ላለው አባትህ፡ ጸልይ፤ በሥውር የሚያይ አባትህ፡ በግልጥ ይከፍልሃል።"[፻፳]

ከዚህ መለኮታዊ መመሪያ፡ የምናገኛቸውን ቁምነገሮች ላመልክታችሁ፤ በመጀመሪያ ነገር፡ ይህ ቃል፡ የግል ጸሎትን የሚመለከት ቢኾንም፡ "ማናቸውም ዓይነት፡ የጋራና የኅብረት፡ የማኅበራዊውና የቤተ ክርስቲያኑ ጸሎቶቻችን ጭምር፡ በዚሁ መሠረትነት ሊፈጸሙ ይገባቸዋል፤" የሚለውን ኹለንተናዊ ትርጓሜም እንደሚያካትት ለመገንዘብ አያዳግታችሁም፡ ባጭር ቃል፡ ***ጸሎቶቻችን ኹሉ፡ ለታይታ ሳይኾኑ፡ በሥውር ለሚያየን ፈጣሪያችን፥ እኛም፡ ከልብ ኾነን፡ በመንፈስና በእውነት አምልኮ፡ በሥውር የምናቀርባቸው ሊኾኑ ይገባል*** ማለት ነው።

እስኪ፡ ሌላውን ቁምነገር ደግሞ፡ በማስተዋል እንመልከተው፤ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን ዜና መዋዕላችን እንደሚታወቀው፡ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የተለየንበት ጊዜ የለም። ፈጣሪያችንን የምናመልክበት ሃይማኖታችን፡ ጥንት በዘመነ ፍጥረት፡ በኪዳኑ ልቦናችን ላይ የተመሠረተ ሲኾን፡ ኋላ፡ ይህንኑ አምልኮታችንን፡ በኪዳኑ ኦሪት አጽንተን፡ በመጨረሻ፡ በኪዳኑ መንፈስ ቅዱስ፡ ለፍጹምነት ማዕርግ አብቅተነው መኖራችንን እንዳትዘነጉት ያስፈልጋል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

እንዲሁም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ ሣለ፡ ዓለሙን ያዳነበት ቤዛነቱን ከመፈጸሙ በፊት፡ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፡ *"ጌታ ሆይ! ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ፡ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን!"* ብሎ በጠየቀው ጊዜ፡ ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን፡ "አቡነ ዘበሰማያት!" ብለው እየጠሩ እንዲጸልዩ ያስተማራቸው፡ ያ የራሱ ጸሎት፡ ኋላ፡ በመስቀል መከራውና ባፈሰሰው ደሙ፥ ሙቶ በመነሣቱም፡ መልስ እንዳገኘ አምናችኋል::[፻፴፩]

ስለዚህ፡ እርሱ በፈጸመው፡ በዚያ መሥዋዕትነቱ ምክንያት፡ ዛሬ እናንተና እኔ፥ በእርሱ የሚያምኑ የሰው ልጆች ኹሉ፡ የምንኖረው ሕይወት፡ ሌላውን፡ ተጨማሪውን፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ ብቻ ሳይኾን፡ ዓበይት ስጦታዎቹ የኾኑትን፡ እውነቱንና መንግሥቱን፡ በምልዓት ባገኘንበት፡ በትንሣኤ ዘመን ውስጥ በመኾኑ፡ *<u>ይህን የመሰለውን የተትረፈረፈ ቸርነቱን ላደረገልን ፈጣሪያችን የምናቀርብለት ጸሎት፡ ይህንኑ ሃይማኖታችንንና ምስጋናችንን የሚገልጽ ኾኖ ሊገኝ ይገባል::</u>*

እንግዲህ፡ እርሱን፡ ደጉንና ለጋሡን ፈጣሪ፡ እንዲህ፡ በሃይማኖት አውቀነውና ቅዱሳት ኪዳናቱን ጠብቀን፡ በእርሱና በእኛ መካከል፡ በጽኑ የተመሠረተው፡ የፍቅር ግንኙነት ሳይቋረጥ፡ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚቻለን፡ ለእርሱ ቤተ መቅደስነት የተሰጠውን፡ ይህን ሰውነታችንን፡ ዘወትር፡ በንስሓ እያደስን፥ በእውነተኛውና በመንፈሳዊው አምልኳችንም፡ በፊቱ ቆመን፡ በግል፥ በቤተሰብና በማኅበር፡ ወደእርሱ በምናቀርበው ልባዊ ጸሎታችን ነው::

ይህ ጸሎታችን፡ "በሰማያት የምትኖር አባታችን እግዚአብሔር ሆይ!" ብለን ከምንጠራው፥ ከካህናችንና ሊቀ ካህናታችን፥ ከንጉሣችንና ንጉሠ ነገሥታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እንዲሁም፡ "ዛሬ፡ በሰማያት የምትኖሪ እናታችን ማርያም ሆይ!" ብለን ከምንጠራት፡ ከዘለዓለማዊቷ መቅደሳችን፥ አገራችንና ንግሥታችን፡ ቅድስት ድንግል ዙፋን ፊት፡ በእውነትና በመንፈስ ቆመን፡ ቃል ለቃል የምንነጋገርበት ሥርዓት መኾኑን፡ በእርግጥ አውቀን፡ በአግባብ ልንፈጽመው ይገባናል::

ይህንኑ ጸሎታችንን የምናደርገው፡ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው አእምሮአችን ብቻ ሳይኾን፡ በሥጋዊው አእምሮአችን ጭምር ሊኾን ስለሚገባ፡ ይኸው ጸሎታችን፡ በተመስጦ ይቀርብ ዘንድ፡ ጸሎቱ፡ ትርጒሙ በሚገባን ቋንቋ የሚካኼድ እንዲኾን ያስፈልጋል:: በግእዙ፥ ወይም፡ በኢትዮጵያኛው (ዐማርኛው)፥ ወይም፡ በሌላኛው ቋንቋ ማለት ነው::

ስለዚህ፡ እርሱ እግዚአብሔር ወልድ፡ ሰው ኾኖ፡ ስለጸሎት ያስተማረንን እያሰብን፡ በእውነተኛ ንስሓ ኾነን፡ ለእርሱ፡ ምስጋናችንን ለማቅረብና ቅዱስ ቁርባኑን ለመቀበል፡ በየዕለታቱ፥ በየሰንበታቱና በየበዓላቱ፡ በቤታችንና በቤተ ክርስቲያን የምናደርገውን፥ ከዚህ በኋላ፡ እከታትዬ የማቀርብላችሁን ጸሎታችንን፡ በያለንበት ከማድረስ እንዳታስታጕሉ አደራ እላለሁ::

# ምዕራፍ ፫:
# ጸሎት::

---

## ስለኢትዮጵያውያን: የምስጋና እና የሰላምታ ጸሎታት ሓተታ::

ጥያቄ:- *ቀደም ብለህ የጠቀስሃቸው: ከኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎትና ከኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ጸሎት ጋር: የተለመዱትን: "አቡነ ዘበሰማያት"ን እና "በስላመ ገብርኤል"ን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁት: የጌታችን የምስጋናና የእመቤታችን የሰላምታ ጸሎታት: የቀደሙትን በማሻሻል: ወይም እንደአዲስ ኾነው መቅረባቸው ነውን? በበለጠ አብራርተህና አስፋፍተህ ብትገልጽልን?*

መልስ:- ስለየትኞቹ ጸሎታት ማለታችሁ እንደኾነ: በትክክል ለዩልኝ!

ጥያቄ:- *"ኢትዮጵያውያን: ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎት" እና "ኢትዮጵያውያን ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት የሰላምታ ጸሎት" የተባሉት: ከመጻሕፍትህ ያገኘናቸው ናቸው::*

መልስ: እኒህማ: የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንን: የዘመኑ ምሕረት ሕይወት በማንጸባረቅ: የቀደሙትን የ"አቡነ ዘበሰማያት"ንና የ"በስላመ ገብርኤል"ን ጸሎታት መሠረት በማድረግ የሚጸለዩ ናቸው:: የእነርሱንም ሓተታ: እተነትንላችሁ ዘንድ: እስኪ: በእናንተው አንደበት ጸሎቶቹን አሰሙኝ!

ጥያቄ:- "ኢትዮጵያውያን: ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት: የምስጋና ጸሎት" የሚለው: የመጀመሪያው ሲኾን: የእርሱም ሙሉ ቃል: እንዲህ ተብሎ ይነበባል:

"አባታችን እግዚአብሔርኣ ሆይ! ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ: *"አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ! ትምጻእ መንግሥትከ! ወይኩን ፈቃድከ: በከመ በሰማይ: ከማሁ በምድር! ሲሳየነ: ዘለለዕለትነ: ሀበነ ዮም! ኅድግ ለነ: አበሳነ: ወጌጋየነ: ከመ ንሕነኒ ንኅድግ: ለዘአበሰ ለነ! ኢታብአነ እግዚኦ: ውስተ መንሱት! አላ አድኅነነ: ወባልሓነ: እምኵሉ እኩይ! እስመ ዚአከ: ይእቲ መንግሥት: ኃይል: ወስብሓት! ለዓለመ ዓለም::"* ብሉ ብሎ: ያስተማረንን: ያን ጸሎታችንን: በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ: ለነፍሳችንና ለሥጋችን: ቸርነትህን አበረከትህልን፡ ምሕረትህን አደረግህልን፡ ፍቅርህን ፈጸምህልን፡ ጸጋህንም ሰጠኸን:: ስለዚህ እናመሰግንሃለን::

"ከቅድስት ድንግል ማርያም: በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት: የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ: በዓለሙ ኹሉ ወረደልን:: ስለዚህ: በሰማይ ብቻ ሳይኾን: ዛሬ በምድርም የምትኖር ኾንህ:: ስምህ: በምድርም ተቀደሰ:: መንግሥትህም መጣችልን:: በሰማይ የኾነው ፈቃድህ: በምድርም እንዲሁ ኾነ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን። ለዘላለም ሕያዋን የሚያደርገንን፡ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን። እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

"የአንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን።

"ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፡ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን።

"ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፡ ፍቅርህና ጸጋህ፡ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

"'ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ' በተባለው፡ በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፡ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለማዙፋ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን። ኃይልና ምስጋና፡ መንግሥትም ያንተ ናቸው፡ ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን።"

"ኢትዮጵያውያን ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት የሰላምታ ጸሎት" የሚለው ደግሞ፡ ኹለተኛው ሲኾን፡ የእርሱም ሙሉ ቃል፡ እንዲህ ተብሎ ይነበባል፡-

"እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ 'ሰላም!' እንልሻለን። በአሳብሽ ድንግል ነሽ፡ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ ላንቺ ይገባል።

"ማኅጸንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ። ቀድሞ በነቢያት፡ 'ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር' የተባልሽ፡ እኛም፡ 'እምነ ጽዮን' ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ።

"እግዚአብሔር አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳኑ ምሕረቱን ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ 'ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ' እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን። በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንቺ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፡ እኛም ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ፡ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን። ይህን ያደረገ፡ ቸሩ አባታችን፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ለዘለዓለሙ፡ አሜን።"

# ምዕራፍ ፭፤ ጸሎት::

## ስለኢትዮጵያውያን: የምስጋና እና የሰላምታ ጸሎታት ሓተታ::

መልስ:- መልካም! እንግዴህ: ቊም ነገር ላለው ጥያቄያችሁ: የምሰጣችሁን የማብራሪያ መልስ: በማስተዋል ተመልከቱት! እነዚህ ኹለት ጸሎቶች: በዚህ መልክ ተዘጋጅተው የቀረቡበትን ምክንያት: በኹለት ገጽታው እያሳየሁ አስረዳችኋለሁ:-

የመጀመሪያው: ጸሎቶቹ በዚህ መልክ የተዘጋጁት: "የቀደሙትን በማሻሻል": ወይም: "እንደአዲስ ኾነው" አለመኾኑን ነው: ነገር ግን: በዚህ ውይይታችን: ቀደም ብላችሁ እንዳወቃችሁት: ኢትዮጵያውያን: ከጥንቱ: ከ"ኪዳን ልቡና" አምልኳቸው ዘመን አንሥተው: በየልባቸው ጽላት ላይ ተጽፎ: እያሰቡትና በሕይወታቸው እየፈጸሙት: በአንደበታቸውም እየተናገሩት የኖሩትን: ያንኑ: የቀደመውን የጸሎት ቃል *"በማጽናት"* መኾኑን ልትገነዘቡት ያስፈልጋል::

ኹለተኛው ደግሞ: እንዲህ ነው:- በቤተ ክርስቲያናችን ነባር ጸሎቶች ላይ በመመሥረት: ስለእግዚአብሔር: በአንድነቱ: በሦስትነቱም: ስለእግዚአብሔር አብ: ስለእግዚአብሔር ወልድ: (ኢየሱስ: መድኃኔ ዓለም: ስቅለት: መስቀል: ልደት: ግዝረት: ትንሣኤ: ክርስቶስ በሚል የተለያየ ስያሜ): ስለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ: እንዲሁም: ስለቅድስት ድንግል ማርያም: ስለቅዱሳን መላእክት: ስለነቢያትና ስለሐዋርያት: ስለጻድቃንና ስለሰማዕታት: ተስፋፍተው የተደረሱ: አያሌ የሃይማኖት: የቅዳሴና የውዳሴ ጸሎቶች እንዳሉን: በማንም ዘንድ ይታወቃል: በተለይም: *"ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሓዲሰ!"* ማለትም: "እግዚአብሔርን: በአዲስ ምስጋና አመስግኑት!" በሚለው የመዝሙረ ዳዊት ቃል: በየዕለቱ: ብዙ ዓይነት: አዳዲስ የቅኔ ማዕበል: በየመልኩ እየተቈጠረና እየተዘጋጀ: በማኅሌት ውስጥና በየጉባኤው: ያለማቋረጥ ሲፈስስ እንዲኖር የሚደረግበት እውነታ: ዘወትር እየተካኼደ ሲፈጸም: እነሆ ይታያል:: የእነዚህ ኹለት ጸሎቶች ዝግጅትም: ይህንኑ ባህል እንደተከተለ አድርገው: በቀና መንፈስ ቢመለከቱትና ቢቀበሉት ያስኬዳል::[፻፳፱]

ነገር ግን: መሠረታዊውና ዋናው ምክንያት: ይህ አይደለም:: "የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ጸሎት" የሚለው ምንባብ: ያ: ጥንት: ከዘመነ ብሉይ: እስከዘመነ ሓዲስ: እግዚአብሔር: እንደተንቢቱ: በኢትዮጵያውያን ልብ ላይ ጽፎ: በየልቡናቸው ያኖረውና እነርሱም ሕይወታቸው አድርገውት የኖሩት: የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው: በጽሑፍ ሠፍሮ የተገለጸበት መኾኑን ቀደም አድርጌ አብራርቼላችኋለሁ:: ከዚህ የተነሣ: እኛ ኢትዮጵያውያን: በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት: ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቅድስት እናቱ: ለድንግል ማርያም ያለን ቅርበትና ፍቅር: ከሌሎቹ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይልቅ: የተለየ ስለኾነ: የ"አቡነ ዘበሰማያት" እና የ"በሰላመ ገብርኤል" ጸሎቶች: ጥሬ ቃላታቸው እንደተጠበቁ ኾነው: እነዚህ ጸሎቶች: በአዲስ ኪዳኑ ደም ያስገኙት የዘለዓለም ፍሬ: የቱን ያህል ጣፋጭነት ያለው መልካም እንደኾነ ለመግለጽ: አኹን ባሉበት መልክ: በጽሑፍ ተዘጋጅተው መቅረባቸው: ፍጹም ተገቢ ኾኖ ይገኛል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፥
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በዚህም ኹሉ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ በልብ፡ በእስትንፋስና በቃል ብቻ ሲገለጹና ሲነገሩ፡ ሲደመጡም የኖሩት፡ እነዚሁ ጸሎቶች፡ እንደዚያ፡ በረቂቅነት ባሕርይ ከነበሩበት ህልውናቸው ወጥተው፡ ዛሬ ለሚገኙበት የግዘፈት ኹኔታቸው በቅተው፡ እንዲህ ለመነበብ የቻሉት፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ ጊዜው በመድረሱ መኾኑን እንመለከታለን። በዚህ ረገድ የተፈጸመው ተግባር፡ ተገቢና ጠቃሚ ነው ቢባል ያስኬዳል የሚያሰኘው፡ ለዚህ ነው።

በዚህ ውይይታችን ውስጥ፡ ቀደም ብሎ ተብራርቶላችሁ እንደተረዳችሁት፡ በሥጋዊ አካል ግዘፋ የምትታየው ሕያዊት ነፍስ፡ በሃይማኖቷ የጸናች፡ በምግባሩዋም የቀናች ከኾነች፡ በጥምቀት ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር ባገኘችው ልጅነት ምክንያት፡ በለበሰችው መንፈሳዊ አካል፡ መኖር ከምትችልበት ብቅዓት ትደርሳለች፤ ይህም ማለት፡ ይህች ነፍስ፡ ፍላጎቷና ብቅዓቷ ካላት፡ በሥጋዊ አካሏ ግዘፋ እያለች፡ በመንፈስ፡ በትንሣኤ ሕይወት ውስጥ ተመስጣ ገብታ መኖር ትችላለች ማለት ነው። ይህ ጸጋ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በወረደው መንፈስ ቅዱስ፡ ለእያንዳንዱ ሰው ስለቀረበለት፡ ይህንኑ ጸጋ ለመቀበል ፈቃደኛ የኾነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፡ በመንፈሳዊ ተድላ ደስታ ይኖራል። በዚህ ጊዜ፡ ፈጣሪው፡ በፍጹም ፍቅር ያደረገለትን ቸርነትና ምሕረት፡ የሰጠውንም ዘላለማዊ ጸጋ አውቆ፡ ያመሰግናል።

ይህን፡ "አባታችን እግዚአብሔር ሆይ" የሚለውን፡ የምስጋና ጸሎት፡ ለፈጣሪው፡ "እናታችን ማርያም ሆይ" የሚለውንም የሰላምታ ጸሎት፡ ለአምላክ እናት ለማቅረብ፡ ብቅዓቱንና ችሎታውን የሚያገኘው፡ በዚህ ሕይወት ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ብቻ ነው። ይህን ብቅዓትና ችሎታ ያገኘው፡ በ"አቡነ ዘበሰማያት" ጸሎት፡ ለእግዚአብሔር አብ የቀረቡት፡ የእግዚአብሔር ወልድ ልመናዎች ኹሉ፡ ጸሎቱን ባስተማረው፡ በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና በእናቱ በድንግል ማርያም ኪዳንነት፡ መልስ አግኝተው መፈጸማቸውን፡ በሃይማኖቱ አረጋግጦ ስላወቀ መኾኑን፡ ልትገነዘቡት ይገባችኋል።

### "አባታችን እግዚአብሔር ሆይ!" ስለሚለው የምስጋና ጸሎት ሓተታ።

*ጥያቄ፡- በ"አቡነ ዘበሰማያት" ጸሎት፡ ለእግዚአብሔር አብ የቀረቡት፡ የእግዚአብሔር ወልድ ልመናዎች ኹሉ፡ ጸሎቱን ባስተማረው፡ በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና በእናቱ በድንግል ማርያም ኪዳንነት፡ መልስ አግኝተው የተፈጸሙ መኾናቸውን፡ በሃይማኖት አረጋግጦ ማወቅ እንዴት ነው?*

# ምዕራፍ ፳፡ ጸሎት::
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ::

---

**መልስ:-** ይህ: "አቡነ ዘበሰማያት" የሚለው ጸሎት: ራሱ: ኢየሱስ ክርስቶስ የጸለየው: የራሱ ጸሎት ነበረ፥ ማለትም: ሰው የኾነው እግዚአብሔር ወልድ: በሰውነቱ: ለአምላክነቱ የጸለየው: ለመጀመሪያ ጊዜም: ከፍጡር: በእውነትና በመንፈስ የቀረበ: ፍጹም ልመና ኾኖ ስለተገኘ: በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ተሰሚነትን ሊያተርፍ: ተገቢውንም ምላሽ ሊያስሰጥ የቻለ ጸሎት ነበር ማለት ነው:: ይኸው ጸሎት: ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ: *"ጌታ ሆይ! ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ: እንጸልይ ዘንድ አስተምረን!"* ብሎ በጠየቀው ጊዜ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ለተከታዮቹ ያስተማራቸው: የራሱ ጸሎት መኾኑንም: ቀደም ብዬ ጠቅሼላችኋለሁ::

ስለዚህ: ዛሬ እኛ: ይህን ጸሎት: ወደፈጣሪያችን በምናቀርብበት ጊዜ: የምንጸልየው: በእውነተኛው የአምልኮ መንፈስ ኾኖ ሲገኝ: ጸሎቱ: በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት: ተገቢውን ፍጹም መልስ አግኝቶ: የመጨረሻውን የትንሣኤ ሕይወት እንድንቀዳጅ ያደረገን መኾኑን: መንፈስ ቅዱስ: ወዲያው ይገልጽልንና: "አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! እናታችን ማርያም ሆይ!" የሚሉትን: ኹለቱንም የማይለያዩ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎቶች በተመስጦ እንድንጸልይ ጸጋውን እንታደላለን::

አሁን እናንተ ያቀረባችሁትን: ይህን ጥያቄያችሁን: እስከዚች አፍታ ድረስ እያካኼድነው ባለነው: በዚህ ውይይታችን ውስጥ ባገኛችሁት እውቀት ብቻ: እናንተው: ራሳችሁ ልትመልሱት ስለምትችሉ: እኔ እየጠየቅኋችሁ: እናንተም እየመለሳችሁልኝ: በምንፈጽመው ቃለ ምልልስ: ከግብ የምናደርሰው ይኾናል:: በዚህ መሠረት: "አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! እናንተ ስትጸልዩ: *'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ! ትምጻእ መንግሥትከ! ወይኩን ፈቃድከ: በከመ በሰማይ: ከማሁ በምድር! ሲሳየነ: ዘለለዕለትነ: ሀበነ ዮም! ኅድግ ለነ: አበሳነ: ወጌጋየነ: ከመ ንሕነኒ ንኅድግ: ለዘአበሰ ለነ! ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት! አላ አድኅነነ: ወባልሐነ: እምኩሉ እኩይ! እስመ ዚአከ: ይእቲ መንግሥት: ኃይል: ወስብሐት! ለዓለመ ዓለም::'* በሉ! ብሎ: ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረንን: ያን ጸሎታችንን: በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ: ለነፍሳችንና ለሥጋችን: ቸርነትህን አበረከትክልን፥ ምሕረትህን አደረግህልን፥ ፍቅርህን ፈጸምክልን፥ ጸጋህንም ሰጠኸን:: ስለዚህ እናመሰግንሃለን::" በሚል መግቢያ የምንጀምረውንና ምላሽ ማግኘቱን አረጋግጠን: ፍጹም ምስጋናችንን ብቻ: ለፈጣሪያችን የምናቀርብበትን: ይህንኑ ጸሎታችንን: እንዲህ እያልን: እንቀጥለዋለን::

ስንቀጥልም: የምናመሰግነው: ለምን እንደኾነ እየተገነዘብን ሊኾን ስለሚገባ: ይኸው እውነታ: በዚሁ ቃለ ምልልሳችን ውስጥ ተብራርቶልን እናገኘዋለን፥ ይኸውም: በቅድሚያ: በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርንበትን ሰውነታችንን: ማለትም: ነፍሳችንንና ሥጋችንን ለማኖር: ከዚያ: ያን ህልውና: በምድር ላይ: በጤንነትና በደህንነት ለማቆየት: በመጨረሻም: ለዘለዓለም ሕይወት ለማብቃት: ስለሚያስፈልጉን ረቂቃንና ግዙፋን ሲሳያት የተነገረበት ሐተታ ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህ ሐተታ፡ ፈጣሪያችን፡ ገና ሳንጠይቀው፡ አስቀድሞ፡ በያይነቱና በየመልኩ፡ አጅግ አትረፍርፎ፡ በቸርነቱ ያዘጋጀልን ወሰን የሌለው የተፈጥሮ በረከቱ፡ በዚያ፡ በረከቱ ላይ ዓምፀን፡ በካድነው ጊዜም፡ ተቀይሞ፡ ልቅጣቸው ሳይል፡ እንደገና፡ ራሱን ከፍ፡ ያደረገልን ሙሉ ምሕረቱና ያን ምሕረቱን ለማስገኘት፡ በቤዛነት፡ የፈጸመልን ፍጹም ፍቅሩ፡ ያን፡ ፍቅሩንም፡ ለዘለዓለም ለማጽናት፡ በምልዓት የሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ እነዚህ ኹሉ ሲሳዩትና ሀብታት፡ ምን እንደኾኑ፡ እንዴትና በምን መንገድ ልናገኛቸው እንደቻልን የሚገልጽልን፡ በእኔ ጠያቂነትና በእናንተ መላሽነት፡ ከዚህ እንደሚከተለው የምንለዋወጠው ይኾናል፡-

ጥያቄ፡- *በተገላቢጦሽ፡ አንተ ጠያቂ፡ እኛ መላሾች ልንኾን ማለትህ ነው?*

መልስ፡- *አዎን!* ወዲያውም፡ በኢትዮጵያዊነት እውቀታችሁ፡ ከምን ደረጃ እንደደረሳችሁ፡ ለእኔ መመዘኛ ይኾነኛል።

ጥያቄ፡- *መልካም! ለዚህ በመብቃታችን ደስ ብሎን፡ ጥያቄህን ልንሰማው እንጠብቃለን።*

መልስ፡- እኔም፡ "እሺ!" ብዬ፡ ውይይታችንን፡ በእኔ ጠያቂነት፡ እንዲህ ስል ቀጠልሁ።

ጥያቄ፡- ጥያቄያችንን የምንጀምረው፡ *"አባታችን ሆይ!"* በሚለው፡ በጸሎቱ መግቢያ ይኾናል።

እግዚአብሔር፡ እኛ ፍጡሮቹ፡ እርሱን በምንፈልገው ጊዜ፡ *"ልትጠሩኝ የሚገባችሁ፡ 'ፈጣሪያችን!'* ወይም፡ *'አምላካችን!'* ወይም፡ *'ጌታችን!'* ወይም፡ *'ንጉሣችን!'* ወይም፡ *'ገዢያችን!' ብላችሁ ነው፡"* ለምን አላለም? ለምን፡ *"አባታችን ሆይ!"* ብላችሁ ጥሩኝ አለ? ይህ ፈቃድና ክብር የተገኘው፡ በተቀባዩና በተጠቃሚው ጥያቄ ሳይኾን፡ አኹንም እንደገና፡ ከሰጪው የቸርነት ልግሥና መኾኑ፡ በጸሎቱ ትምህርት ታውቋል። እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! ፍጥረትን፡ ከአለመኖር ወደመኖር ያመጣ፡ ፈጣሪ፡ ፍጡሩ፡ ከእርሱ ጋር ያለው የግንኙነት ደረጃ፡ ይህን የሚያህል የዝምድና ቅርበት ያለው እንዲኾን መፍቀዱ፡ ምን ይደንቅ! ምን ይጠልቅ! ይህ የግንኙነት ደረጃና ይህ የዝምድና ቅርበት፡ በአባትና በልጅ መካከል ባለው የተፈጥሮ አንድነትና የፍቅር መጠን እንዲኾን በመደረጉ፡ የአንድነቱ ዓይነትና የፍቅሩ ጽንፍ፡ በምን መሥፈሪያ፡ ሊለካ፡ በምንስ ቃል ሊገለጽ ይቻላል?

መልስ፡- *አይቻልም።*

# ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት::

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ::

ጥያቄ:- ይህን: የአንድነት ዓይነትና የፍቅር መጠን: እኔ: እዚህ ላይ አብራርቼ ልገልጸው ከምሞክረው ይልቅ: ሐዋርያው: *"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ: አብ: እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን: እዩ! እንዲሁም ነን:"* ብሎ በጻፈው ቃል ተወስነን: ብናጠቃልለው የሚበቃ ይመስለኛል:[፻፳፫] እናንተስ: ምን ይመስላችኋል?

መልስ:- *አዎን! እኛም: "ይበቃል!" እንላለን::*

ጥያቄ:- ለነገሩማ: ፈጣሪያችን: ሰው ኾኖ: በምድር ላይ በተመላለሰበት ጊዜ: በእርሱና በሰብአዊው ፍጡሩ መካከል ሊኖር የሚፈልገው: እውን ያደረገውም የግንኙነት ዓይነትና መጠን: ምንና እንዴት እንደ ኾነ: እኛ ደካሞች ፍጡሮቹ: በቀላሉ ሊገባንና ልንረዳው: ልንገነዘበውም እንችል ዘንድ: የሰውነት ባሕርያችንንና የተፈጥሮ ዓቅማችንን በሚያውቀው መለኮታዊ አንደበቱ: የተናገረውን ቃሉን: እስኪ እንስማ!

ይህም: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ስለጸሎት: ለደቀ መዛሙርቱ: *"ለምኑ! ይሰጣችሁማል: ፈልጉ! ታገኙማላችሁ: መዝጊያን አንኳኩ! ይከፈትላችሁማል::"* ሲል: ባስተማራቸው ጊዜ: አያይዞ ያስማው: እንዲህ የሚለው ምሳሌ ነው:- *"አባት ከኾናችሁ: ከእናንተ: ከማንኛችሁም: ልጁ: እንጀራ ቢለምነው: እርሱ: ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው: በዓሣ ፋንታ: እባብ ይሰጠዋልን? ወይስ: እንቍላል ቢለምነው:ጊንጥ ይሰጠዋልን? እንኪያስ: እናንተ: ክፉዎች ስትኾኑ: ለልጆቻችሁ: መልካም ስጦታን መስጠትን ካወቃችሁ: በሰማይ ያለው አባት: ለሚለምኑት: እንዴት አብልጦ: መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው!?"*

የሚያስፈልገንን ኹሉ: እንዲህ: አስቀድሞ የሰጠንና የሚሰጠን የሰማዩ አባታችን: እኛ ደግሞ: በእውነተኛው የሃይማኖት አምልኮ ኾነን: በጸሎት የምንጠይቀው ነገር ቢኖር እንኳ: እርሱ የሚሰጠን ስጦታ ምን ዓይነት እንደኾነ በማስተዋል ተመልከቱት! በሥጋ የወለዱን አባቶቻችንና እናቶቻችን የሚሰጡን: ያንኑ: የጠየቅናቸውን ቢኾን ነው፡ ያም: አላቂና ጠፊ የኾነው: ምድራዊው ነው:: የእርሱ ስጦታ ግን: እንዲህ አይደለም፡ እኛ ከፈለግነውና ከጠየቅነው በላይ: እጅግ የላቀ፡ ወደር የማይገኝለትና በገንዘብ ሊተመን የማይቻል: የማያልቅና ዘለዓለማዊ፡ ፍጹምና የመጨረሻው ስጦታ ነው እንጂ:: እርሱም: *መንፈስ ቅዱስ ነው::*

እንግዲህ: *"በምድር ላይ: አባት አታድርጉ! የሰማዩ አባታችሁ: አንድ ነውና::* ስለዚህ: እኔን: *'አባታችን!' በሉኝ!"* ያለንን: ቃሉን ተከትለን: እኛ: *"አባታችን ሆይ!"* እያልን የምንጠራው: ቀድሞ: በሥጋ የፈጠረን: ኋላ: በነፍስ: መልኩን ሰጥቶ ያከበረንና በመጨረሻ: በመስቀል ላይ ተቤዥቶን ያዳነን በመኾኑ: እንደፈጣሪያችን፡ አምላካችንና መድኃኒታችን ብቻ ሳይኾን: በይበልጥ: እርሱ: "በሥጋም፡ በነፍስም: በመንፈስም: በወለደን: በአባትነቱ እንድናውቀውና እንድንጠራው ስለፈለገ ነው!" ብለን እናምናለን::[፻፳፬]

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እውነተኛውና ዘለዓለማዊው አባትነት፡ የእርሱ ብቻ መኾኑን በማመን፡ በሥጋ፡ ከወለዱን አባቶቻችንና እናቶቻችን ይልቅ፡ ልንወድደው ፡ ልንታዘዘው ፡ ልናከብረውና ልንፈራው አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! በጣሙን ይገባል።*

ጥያቄ:- ከዚህ ቀደም ብሎ እንደሰማችሁት፡ ሰውን ስለወደደ፡ ሰው የኾነውን እግዚአብሔርን፡ በቅርብ አውቆት፡ እጅግ ያፈቀረውና ያገለገለው፡ ሐዋርያውና ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ *"የእግዚአብሔር ልጆች' ተብለን ልንጠራ፡ አብ፡ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ! እንዲሁም ነን።"* ሲል እንደጻፈው፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን የኾነውን እግዚአብሔርን፡ *"አባታችን!"* ብለን እንድንጠራው ፡ እኛም፡ *"የእግዚአብሔር ልጆች!"* ኾነን፡ በዚህ ስም እንድንጠራ፡ ይህን ሀልውና ፡ ይህን ክብር ፡ ይህን እውቀትና ይህን ጸጋ ያገኘነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለኾነ፡ እጅግ ደስ ብሎን፡ ይህን ላደረገ፡ ለእርሱ፡ የዘወትር ምስጋናችንን ልናቀርብ አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! በእርግጥ ይገባል።*

ጥያቄ:- አሁን፡ የምንቀጥለው፡ ከዚሁ፡ ከጸሎቱ መግቢያ ጋር ስለተያያዘው፡ "በሰማያት የምትኖር!" ስለሚለው ቃል ይኾናል።

በዚህ ቃል መሠረት፡ "መኖሪያው፡ በሰማያት ብቻ ነው!" ተብሎ ይታመን የነበረው፡ ራሱ እግዚአብሔር፡ *መጀመሪያ*፡ በልጁ፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም *መምጣት*፤ ከዚያ በኋላ፡ የመጣበትን ተልእኮ ፈጽሞና ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ፡ ወደሰማያት እስካረገባት ቀን ድረስ፡ በምድር ላይ በመመላለሱ፡ በመጨረሻ፡ በቅዱስ መንፈሱ፡ ወደዚችው ምድር ተመልሶ መጥቶ፡ በሰዎች መካከል በመገኘቱ፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ በመሬትና በፍጥረተ ዓለሙ መልቶ፡ የሚኖር አልኾነምን?

መልስ:- *አዎን! የሚኖር ኾኗል።*

ጥያቄ:- ይህንስ እውነታ፡ *"እኔም፡ አብን እለምናለሁ፥ ለዘለዓለምም፡ ከእናንተ ጋር እንዲኖር፡ ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፥ እርሱም፡ ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለኾነ፡ ሊቀበለው የማይቻለው፡ የእውነት መንፈስ ነው፥ ነገር ግን፡ በእናንተ ዘንድ ስለሚኖር፥ በውስጣችሁም ስለሚኾን፡ እናንተ ታውቃላችሁ። ...የሚወድደኝ ቢኖር፡ ቃሌን ይጠብቃል፥ አባቴም ይወድደዋል፤ ወደእርሱም እንመጣለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።"* ባለው ቃሉ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አረጋግጦ ያጸና[፻፳፭] አይደለምን?

መልስ:- *አዎን! አጽንቶታል።*

# ምዕራፍ ፫፤ ጸሎት።
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

ጥያቄ:-    ታዲያ! እንዲህ ከኾነ: እኛ ኢትዮጵያውያን: ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን: በዚህ የምሕረት ዘመን: የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት: *"አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! ከቅድስት ድንግል ማርያም: በተወለደው ልጅህ መድኀኒትነት: የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ: በዓለሙ ኹሉ ወረደልን። ስለዚህ: በሰማይ ብቻ ሳይኾን: ዛሬ: በምድርም የምትኖር ኾንህ።"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:-    *አዎን! ይገባል።*

ጥያቄ:-    መልካም! *"ስምህ ይቀደስ! (ማለትም: ይከበር! ይመስገን!)'* በሉ!" ያለውን ደግሞ እንመልከት! እግዚአብሔር ወልድ: በዚህ ዓለም: በሰውነት ተገልጦ: እጅግ ብዙ የኾነውን የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራቱ: የእግዚአብሔር ስም: በምድር ላይ: በሰዎች መካከል አልተቀደሰምወይ? አልከበረምወይ? አልተመሰገነምወይ?

መልስ:-    *አዎን! ተቀድሷል፡ ከብሩዋል፤ ተመስግኗል።*

ጥያቄ:-    ይህንስ እውነታ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፈጸማቸው: እጅግ ብዙዎች ከኾኑት ተአምራት መካከል: አንዳንዶቹን ብቻ: በምሳሌነት በመጥቀስ ማስረዳት ይቻል የለምን? እነዚህም: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ከአጋንንት ሠራዊት ቊራኛ የፈወሰው: ያ ሕመምተኛ: ለጌታ አድሮ: ከእርሱ ጋር ይኖር ዘንድ: ጌታን በለመነው ጊዜ: ጌታ: *"አይኾንም! ወደቤትህ ተመለስ! እግዚአብሔር: እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ ንገር!'* ብሎ ስላሰናበተው: ያ ሰው: ጌታ: እንዴት ያለ: ታላቅ ነገር እንዳደረገለት: በከተማው ኹሉ እየተዘዋወረ አልሰበከምን?

ደግሞስ: ወደኢየሩሳሌም ሲኼድ: በሩቅ ቆመው: እየጮኹ: *"ኢየሱስ ሆይ! አቤቱ ማረን!"* ላሉት: ለዐሥሩ ለምጻሞች: *"ኺዱ! እየራሳችሁን: ለካህናት አሳዩ!"* ብሏቸው: ሲኼዱ: ገና በመንገድ ላይ ሣሉ ስለነጹ: *"ከእነርሱ: አንዱ: እንደተፈወሰ ባየ ጊዜ: በታላቅ ድምፅ: እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ: እያመሰገነውም: በእግሩ ፊት: በግንባሩ ወደቀ: እርሱም ሳምራዊ ነበረ። ኢየሱስም መልሶ: 'ዐሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ? ከዚህ: ከልዩ ወገን በቀር: እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም:' አለ። እርሱንም: 'ተነሣና ኺድ! እምነትህ አድኖሃል፡' አለው።"* ታዲያ: በዚያኛው የምሥራች ስብከት፥ በዚህኛውም የምስጋና ስግደት: የእግዚአብሔር ስም አልተቀደሰምን? አልከበረምን? አልተመሰገነምን?

በመጨረሻስ: ጌታ: ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዓላማ ካገባደደ በኋላ: በመስቀል ላይ: የሞት ጽዋውን ተቀብሎ: ከሙታን ተለይቶ ወደተነሣበት መቃብር ከመውረዱ በፊት: በነበረችው ሌሊት: *"አባት ሆይ! እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ: በምድር አከበርሁህ።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*"...አኹንም፡ ዓለም ሳይፈጠር፡ በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር፡ በራስህ ዘንድ አክብረኝ። ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች፡ ስምህን ገለጥሁላቸው፥ የአንተ ነበሩ፥ ለእኔም ሰጠሃቸው፤ ቃልህንም ጠብቀዋል። ...በእውነትህ ቀድሳቸው፡ ቃልህ፡ እውነት ነው። ወደዓለም እንደላክኸኝ፡ እንዲሁ፡ እኔ፡ ወደዓለም ላክኋቸው፡ እነርሱም ደግሞ፡ በእውነት የተቀደሱ እንዲኾኑ፡ እኔ፡ ራሴን፡ ስለእነርሱ እቀድሳለሁ።"* ብሎ፡ በተናገረው ቃሉ፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር ስም፡ ከዚያች ቀን አንሥቶ፡ በምድር ላይ፡ በእውነት የመቀደሱ፡ የመክበሩ፡ የመመስገኑ እውነታ መጀመሩን፡ ማረጋገጥ አይደለምን?[፻፳፪]

መልስ:- *አዎን! ነው።*

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን፡ በዚህ የምሕረት ዘመን፡ የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት፡ *"ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ።"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል።*

ጥያቄ:- መልካም! አኹን ደግሞ፡ *"'መንግሥትህ ትምጣ!' በሉ!"* ስለሚለው፡ ስለሚቀጥለው የጸሎቱ ኃይለ ቃል፡ በአትኩሮት እንመለከታለን፡ በዚህም ጊዜ፡ ከጥያቄው ጋር አግባብነት ያላቸውን፡ አንዳንድ፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶችን፡ ለማስታወስ ያህል፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና እናነሳሳቸዋለን። የዚህ ጸሎት ልመና፡ ምላሹን አግኝቶ፡ የሰው ልጆች፡ መልካሙ ፍላጎታቸው ተሟልቶላቸው፡ በሰላማዊ ሰረፍት ለመኖር መቻላቸውን፡ እስካሁን ከተወያየንባቸው ርእሶች እንደተረዳችሁት አምናለሁ።

እንደማይዳሰሰውና እንደማይደረስበት፡ እንደሰማዩ ኀዋ፡ የማትጨበጥ ረቂቅ በመኾኗ፡ "መንግሥተ ሰማያት" እየተባለች ስትጠራ የኖረችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዓለሙ ኹሉ መልታ፥ በሰው ልቦናም ውስጥ ሰፍና እንድትገኝ፡ ፈጣሪ፡ በቸርነቱ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ለሰው ልጆች ሰጥቷት የነበረች፡ የመልካም ህልውና ሥርዓት መኾኗን አውቃችኋል፡ ነገር ግን፡ ይህችኑ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የሰው ልጆች ስላልፈለጓትና ተፃራሪዋ የኾነውን ሌላውን ዓይነት አኗኗር ስለመረጡ፡ ከእነርሱ ተሠውራ ከቆየች በኋላ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ በንስሓ፡ ወደፈጣሪያቸው ተመልሰው፡ በእውነት ስለፈለጓት፡ እነሆ፡ በመለኮታዊው ምሕረት፡ እንደገና ሊያገኟትና ሊኖሩባት እንዲችሉ መደረጉን፥ ይህም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በተቀዳጁት፡ የትንሣኤ ሕይወት ተረጋግጦ እውን እንደኾነላቸውም ተገንዝባችኋል።

# ምዕራፍ ፭፤ ጸሎት።

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

አዎን! ይህች "የእግዚአብሔር መንግሥት": ዛሬ: በምድር ላይ: በሰዎች መካከል: እንዲህ: ገዝፋ እንድትገኝ የተደረገበት: የመጨረሻውና ዘለዓለማዊው ማረጋገጫ ማኅተም የተገኘው: በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መኾኑ ቢታወቅም: ይህ እውነታ: ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ: ሳይደበዝዝና ሳይዳከም: ከመጥፋትም ድኖ: ለዚህ: ለፍጻሜ ብቅዓት ይደርስ ዘንድ: በሕያውነት እንዲቀጥል ለማድረግ የተቻለው: እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን: የቀደሙትን: ስድስቱን የእግዚአብሔርን ቅዱሳት ቃል ኪዳናት: በፍጹም ታማኝነት: በሃይማኖት ጠብቀው: በምግባርም አጽንተው: ተቃዋሚውን የክፋት ጦር በመቋቋም: ሲጋደሉ በመኖራቸው መኾኑን: ይህም: የመለኮት ቸርነት: ያስገኘው ጸጋ እንጂ: በሰብአዊው ሀብት: ጥበብና ኃይል የተደረገ አለመኾኑን: በሚበቃ ተረድታችሁታል።

በዚህ ረገድ: በቅድሚያ: *"የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና: ንስሓ ግቡ!"* የሚለው: የአምላክ የአዋጅ ቃል: ለምን እንደተነገረ ለማወቅ የሚሳነው ሰብአዊ ፍጡር "ይኖራል" ብሎ ማሰብ ያዳግታል። ይህ የአዋጅ ቃል: እግዚአብሔር: ይህችኑ: ዘለዓለማዊት መንግሥቱን: እንደገና: በምድር ላይ: በሰዎች መካከል ሊገልጣት ፈቃዱ ኾኖና ወስኖ: ይህን ተልእኮ ለመፈጸም: "ይወርዳል: ይወለዳል!" ተብሎ ሲተነበይለት የቆየው: ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ: እነሆ: ደርሶ: በደጃፍ ቆሞ የሚገኝ መኾኑን በማረጋገጥ: መጥምቁ ዮሐንስ: በምሥራችነት የተናገረው ነበር። ኋላም: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ይህችኑ: "የእግዚአብሔር መንግሥት" የተባለችውን ረቂቅ መንግሥቱን: በመስቀሉ ዙፋን ላይ ኾኖ: በሠዋው ሥጋውና ባፈሰሰው ደሙ: በምድር ላይ: እንደገና አድሶና አግዝፎ እስኪገልጣት ድረስ: ይህንኑ የአዋጅ ቃል: ሲያሰማ የቆየ መኾኑን: ቀደም አድርጋችሁ አውቃችኋል።

አዎን! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ሰይጣንን: እንዲህ: ድል ነሥቶ: ኃጢአትን ደምስሶ: ሞትንም አጥፍቶ: በኃይልና በምስጋና: በመንግሥታዊም ሥልጣን ከተነሣ በኋላ ግን: "ሰማያዊት" ትባል የነበረችው: ይህችው: የእግዚአብሔር መንግሥት: በምድር ላይ: እንደገና እንድትገለጥ: የማትታይና ረቂቅ የነበረችውም: ገዝፋ: እንደገና በገሃድ እንድትታይ አደረገ። የተገለጠችው: የታየችውም: በዕለተ እሑድ ሰንበት ሌሊት: በእርሱ በራሱ: በኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ቀደም ብሎ: በአይሁድ ቤተ ክህነት ተከስሶ: በዕለተ ዓርብ የፋሲካ ቀን: በምድራዊው የቄሣር መንግሥት ባለሥልጣን ፊት: ለፍርድ ቀርቦ ሳለ: መኰንኑ ጲላጦስ: *"የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?"* ብሎ በጠየቀው ጊዜ: ገና በደሙ ታጥባና ታትማ: በትንሣኤውም ታድሳና ገዝፋ ስለምትከሰጸው መንግሥቱ: *"መንግሥቴ: ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ: ከዚህ ዓለም ብትኾን: ወደዓለም እንዳልሰጥ: ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አኹን ግን: መንግሥቴ: ከዚህ አይደለችም!"* በማለት[፻፳፯] መልስ: አስቀድሞ የሰጠው: በዚህ ምክንያት መኾኑን ልታውቁት ይገባል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር: ማነው?

---

*ታዲያ!* *"የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና: ንስሓ ግቡ!"* የተባለችው: ይህች *"የእግዚአብሔር መንግሥት"*: ራሱ: ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ አይደለምን? በዚህስ: በኢየሱስ ክርስቶስ: ሕያው ሰውነት: ያች: እንደሰማይ የራቀችና የመጠቀች፥ የማትዳሰስና የረቀቀች በመኾኗ: *"መንግሥተ ሰማይ!"* ትባል የነበረችው: *"የእግዚአብሔር መንግሥት!"*: በመጨረሻው ዘመን: በምድር ላይ: እንዲህ ገዝፋ መገለጧን: ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ: በአዋጅ ማሳወቅ አይደለምን?

**መልስ:-** *አዎን! ነው::*

**ጥያቄ:-** ይህንስ እውነታ: *"የእግዚአብሔር መንግሥት: መቼ ትመጣለች?"* ብለው ለጠየቁት ተቃዋሚዎቹ: *"የእግዚአብሔር መንግሥት: በመጠባበቅ አትመጣም፤ ደግሞም: 'እነኋት በዚህ: ወይም እነኋት በዚያ ናት!' አይሏትም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት: እነሆ: በመካከላችሁ ናትና!"* ብሎ[፻፳፰] በሰጠው ቃል: ራሱ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አረጋግጦታል አይደለምን?

**መልስ:-** *አዎን! አረጋግጦታል::*

**ጥያቄ:-** እንዲህ: በጌታ ቃል: *"በመካከላችሁ ናት!"* የተባለችውና አልፎ አልፎ: በመንግሥተ ሰማያትነት ስያሜ የምትጠራው: ይህችው የእግዚአብሔር መንግሥት: በምድር ላይ በመካከላችን ስትኖር: ምንን እንደምትመስል፥ እኛም: ዛሬ: በሕይወተ ሥጋ እያለን: እንዴት ልንኖራት እንደሚገባን: በበለጠ አረጋግጠን ለማወቅ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ለደቀ መዛሙርቱ: በምሳሌ የተናገራቸውን: ከዚህ የሚከተሉትን: የትምህርቶቹን የመግቢያ ቃላት: እስኪ: እየጠቃቀስሁላችሁ ስሟቸው!

*"መንግሥተ ሰማያት: በእርሻው መልካም ዘርን የዘራ ገበሬን፥ ...ሰው ወስዶ: በእርሻው የዘራት: የሰናፍንጭ ቅንጣትን፥ ...ኹሉ እስኪቦካ ድረስ: ሴት ወስዳ: በሦስት መሥፈሪያ ዱቄት ውስጥ የሸሸገችውን እርሾ፥ ...በእርሻ ውስጥ የተሠወረ መዝገብን፥ ...መልካም ዕንቍን የሚሻ ነጋዴን፥ ...ወደባሕር የተጣለች፥ ከኹሉም ዓይነት የሰበሰበች መረብን፥ ...ለወይኑ አትክልት: ሠራተኞችን ሊቀጥር: ማልዶ የወጣ: ባለቤትን፥ ...ለልጁ ሠርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች:: ...ኢየሱስም: 'ይህን ኹሉ አስተዋላችሁን?' አላቸው፤ 'አዎን!' አሉት:: እርሱም: 'ስለዚህ: የመንግሥተ ሰማያት ደቀ መዝሙር የኾነ ጸሓፊ ኹሉ: ከመዝገቡ: አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል፤' አላቸው::*

*"...ደቀ መዛሙርቱ: ወደኢየሱስ ቀርበው: 'በመንግሥተ ሰማያት: ከኹሉ የሚበልጥ: ማን ይኾን?' አሉት:: ሕፃንም ጠርቶ: በመካከላቸው አቆመ::*

## ምዕራፍ ፫፤ ጸሎት::
## “እናታችን ማርያም ሆይ!” ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ::

---

ጌታችን ኢየሱስም “እንዲህ አለ:- 'እውነት እላችኋለሁ፡ ካልተመለሳችሁ: እንደሕፃናትም ካልኾናችሁ: ወደእግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም:: እንግዲህ: እንደዚህ ሕፃን: ራሱን የሚያዋርድ ኹሉ: በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ: እርሱ ነው::'” ይህ የጌታ ቃል: “እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይ: ሕፃናትን ወደእርሱ ሲያመጧቸው: ደቀ መዛሙርቱ በገሠጿቸው ጊዜ: 'ሕፃናትን ተዉአቸው! ወደእኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው! መንግሥተ ሰማያት: እንደነዚህ ላሉ ናትና!'” ካለው ጋር ይተባበራል::

“...መንግሥተ ሰማያት: አገልጋዮቿን ኹሉ: ሊቈጣጠር የወደደ ንጉሥን ትመስላለች፡” እርሱም: የእያንዳንዳቸውን በደል: እስከሰባት ጊዜ ብቻ ሳይኾን: እስከሰባ ጊዜ ሰባት ድረስ: ይቅር የሚል፡ ዕዳቸውንም: በምሕረት የሚተውላቸው ስለኾነ: እነርሱም: ለባልደረቦቻቸው: እንደርሱ ኹሉ: እንዲያደርጉ የሚጠብቅ ንጉሥ ነው:: ደግሞም: “'የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ: ትእዛዛትን ኹሉ: ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁና: የሚጐድለኝ ምንድር ነው?' ብሎ: አንድ ጐበዝ: ላቀረበለት ጥያቄ: ጌታችን ኢየሱስ: 'ፍጹም ልትኾን ብትወድ: ኺድና ያለህን ሽጠህ: ለድሆች ስጥ! ገንዘብህንም: በሰማያት ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከተለኝ!' አለው:: ጐበዙም: ይህን ቃል በሰማ ጊዜ: ብዙ ንብረት ነበረውና: እያዘነ ስለኼደ: ኢየሱስ: ለደቀ መዛሙርቱ: 'እውነት እላችኋለሁ! ለባለጠጋ ወደመንግሥተ ሰማያት መግባት: ጭንቅ ነው፤ ዳግመኛም እላችኋለሁ:- ባለጠጋ: ወደእግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ: ግመል: በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል!' አለ::”

“...ለጽዮን ልጅ: 'እነሆ ንጉሥሽ: የዋህ ኾኖ: በአህያ ላይና በአህያዪቱ ግልገል፥ በውርንጫዪቱም ላይ ተቀምጦ: ወደአንቺ ይመጣል፤' በሉአት!” ደግሞም: “ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ: ምስጋናን: ለራስህ አዘጋጀህ!” ተብሎ: በነቢይ የተነገረው: ይፈጸም ዘንድ:” ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በአህያዪቱ ላይ ተቀምጦ፥ የዘንባባ ዝንጣፊ በያዙ ሕፃናትና ልብሳቸውን እያነጠፉ በተቀበሉት ሕዝብም ታጅቦ: “ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ! በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ: የተባረከ ነው! ሆሣዕና በአርያም! ...በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ: ቡሩክ ነው!” እየተባለ ወደኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ: የራሱን ንጉሥነት፥ ከሰዎች ተሠውራ የቈየችው መንግሥቱም: እነሆ: ገዝፋ: በገሃድ መገለጿን: ለዓለሙ ኹሉ: በአዋጅ ማሳወቁ እንደነበረ ግልጽ አይደለምን?

መልስ:- አዎን! ነው::

ጥያቄ:- ይህንስ እውነታ: “'በእግዚአብሔር ስም የምትመጣ: የአባታችን የዳዊት መንግሥት: የተባረከች ናት፤ ሆሣዕና በአርያም!' እያሉ ይጮኹ ነበር:: ...“ደቀ መዛሙርቱ: ኹላቸው: ደስ እያላቸው: ተአምራትን ኹሉ ስላዩ: በታላቅ ድምፅ: እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ ጀምረው: 'በጌታ ስም: የሚመጣ ንጉሥ: የተባረከ ነው፤ በሰማይ: ሰላም፥ በአርያምም: ክብር ይኹን!' አሉ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*“ከሕዝብም መካከል፡ ከፈሪሳውያን አንዳንዱ፡ ጌታን፡ 'መምህር ሆይ! ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው! አሉት። መልሶም፡ 'እላችኋለሁ፡ እነዚህ፡ ዝም ቢሉ፡ ድንጋዮች ይጮኻሉ!' አላቸው።”* የሚለው የወንጌላውያኑ ቃል የሚያጸናው አይደለምን? በዚህስ ኹሉ፡ እግዚአብሔር፡ በምድር ላይ መመስገኑ፡ 'ስምህ ይቀደስ!' የሚለው የጸሎቱ ልመናም፡ ተገቢውን ምላሽ ማግኘቱ አይደለምን?[፻፳፱]

**መልስ:-** *አዎን! ነው።*

**ጥያቄ:-** ደግሞስ፡ በወይን አትክልት በተመሰለች መንግሥቱ እንዲያገለግሉ፡ አደራውንና ኃላፊነቱን የሰጣቸው አገልጋዮች፡ ለተጣለባቸው አደራና ኃላፊነት፡ ሳይበቁ በመቅረታቸው፡ እንዲያውም፡ በክህደት ዓምፀው ተነሥተውበት፡ የሥራ ፍሬአቸውን ተቈጣጥሮ እንዲያቀርብ የታዘዘ ልጁን በመግደላቸው፡ ባለቤቱ፡ በእነርሱ ላይ ተገቢው ቅጣት እንዲፈጸምባቸው ማድረጉን ከገለጸላቸው በኋላ፡ *“ስለዚህ እላችኋለሁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከእናንተ ትወሰዳለች! ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች!”* ያላቸው፡ የትኛዋን መንግሥት ነው? ይህችኑ፡ እርሱ፡ *“ሆሣዕና በአርያም! በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው!”* ተብሎ፡ በጽዮን ንጉሥነቱ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፡ ከጽዮን ንግሥት እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር፡ የሚመራትንና የሚያስተዳድራትን መንግሥቱን አይደለምን?

**መልስ:-** *አዎን! ነው።*

**ጥያቄ:-** *“እናንት ግብዞች፡ ጻፎችና ፈሪሳውያን! የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ በሰው ፊት ስለምትዘጉ፡ ወዮላችሁ! እናንተ አትገቡም፡ የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ!”* ደግሞም፡ *“እናንተ ግን፡ የምትበሉትን፥ የምትጠጡትንም አትፈልጉ! አታወላውሉም! ይህንስ ኹሉ፡ በዓለም ያሉ አሕዛብ ይፈልጉታልና። የእናንተም አባት፡ ይህ፡ እንዲያስፈልጋችሁ ያውቃል። ዳሩ ግን፡ እናንተ፡ መንግሥቱን፡ እውነቱንም ፈልጉ! ይህ ኹሉ ይጨመርላችኋል።”* እንዲሁም፡ *“አንተ ታናሽ መንጋ! መንግሥትን ሊሰጣችሁ፡ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና፡ አትፍሩ! ያላችሁን ሽጡ! ምጽዋትም ስጡ! ...ወገባችሁ የታጠቀ፥ መብራታችሁም የበራ ይኹን! ...ተዘጋጅታችሁም ኑሩ! የሰው ልጅ፡ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።”* የተባለችው፡ መንግሥት፡ የትኛዋ ናት? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *“በመካከላችሁ ናት!”* ያላት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አይደለችምን?[፩፻፴]

**መልስ:-** *አዎን! ናት።*

# ምዕራፍ ፫፡ ጸሎት።

## “እናታችን ማርያም ሆይ!” ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

---

ጥያቄ፡- የዚች መንግሥት ባለቤት የኾነው፡ እርሱ ንጉሥዋ፡ *“በምን ሰዓት እንደምመጣ አታውቁምና፡ እንግዲህ፡ ነቅታችሁ፡ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ!”* ብሎ፡ አገልጋዮቹን ካስጠነቀቀ በኋላ፡ ይህንኑ ማስጠንቀቂያውን በማጠናከር፡ *“እንኪያስ፡ ምግባቸውን፡ በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ፡ ጌታው፡ በቤተሰቦቹ ላይ የሾመው፡ ታማኝና ልባም አገልጋይ ማነው? ጌታው መጥቶ፡ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው፡ ያ አገልጋይ፡ ብፁዕ ነው፡ እውነት እላችኋለሁ፡ ባለው ኹሉ ላይ ይሾመዋል። ያ፡ ክፉ አገልጋይ ግን፡ ‘ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል፡’ ብሎ፡ በልቡ ቢያስብ፡ ባልንጀሮቹን አገልጋዮችንም ሊመታ ቢጀምር፡ ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፡ የዚያ አገልጋይ ጌታ፡ ባልጠበቀት ቀን፡ ባላወቀትም ሰዓት ይመጣል፡ ከኹለትም ይሰነጥቀዋል፡ ዕድሉንም፡ ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፡ በዚያም፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይኾናል!”* ያለው፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ አደራውን ‘ጠበቀውም’ ኾነ ያልጠበቀው አገልጋይ፡ ተሹመው የሚያገለግሏት መንግሥት፡ የትኛዋ ናት?

በመጨረሻውስ የፍርድ ጊዜ፡ *“መንግሥተ ሰማያት፡ መብራታቸውን ይዘው፡ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ፡ ዐሥር ቈነጃጅትን፡* ከእነርሱም፡ ተዘጋጅተው ስለጠበቁት፡ ከሙሽራው ጋር፡ አብረው ወደሠርጉ የገቡትን፡ አምስቱን ‘ልባሞች’፡ ተዘጋጅተው ስላልጠበቁትና የሠርጉ ደጃፍ ስለተዘጋባቸው፡ ከሙሽራው ጋር ወደሠርጉ ሳይገቡ የቀሩትን፡ አምስቱን ‘ሰነፎች’፡ …እንዲሁም፡ *ሦስት ጉበዛዝት ሠራተኞቹን ጠርቶ፡ ሠርተው እንዲያተርፉበት፡ ለእያንዳንዱ፡ እንደየዓቅሙ፡ ለአንዱ፡ አምስት መክሊት፡ ለአንዱ፡ ኹለት፡ ለአንዱም፡ አንድ ሰጥቶ ወደሌላ አገር ኼዶ፡ ከብዙ ዘመን በኋላ ተመልሶ፡ የሥራ ፍሬአቸውን በተቈጣጠራቸው ጊዜ፡* ሠርተው ላተረፉት፡ ለኹለቱ ትጉሆች፡ ሹመትንና ደስታን ያበረከተ፡ ምንም ባላተረፈው፡ በአንዱ ሐኬተኛ ላይ ግን፡ *ውርደትንና ሥቃይን የበየነ ሰውን፡ ትመስላለች፡”* የተባለችው የሙሽራው ሠርግና የባለገንዘቡ ሥራ ማን ናት? በምድር ላይ፡ በሰዎች መካከል ያለችው፡ የሙሽራውና የባለቤቱ የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት አይደለችምን?

መልስ፡- *አዎን! ነው።*

ጥያቄ፡- *“የሰው ልጅ፡ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር፡ በክብሩ መጥቶ፡ በፍርዱ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ፡”* በጎ ሥራ ለሌላቸው፡ በግራው ላሉት፡ የሐሰትና የክህደት አገልጋዮች፡ *“እናንተ ርጉማን! ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ፡ ወደዘለዓለም እሳት፡ ከእኔ ኺዱ!”* ሲላቸው፡ በጎ ሥራን ሠርተው ለተገኙት፡ በቀኙ ላሉት፡ እውነተኞችና ታማኞች አገልጋዮቹ ግን፡ *“እናንተ የአባቴ ቡሩካን! ወደእኔ ኑ! ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፡ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ!”* የሚላቸው፡ ይህች መንግሥት የትኛዋ ናት?

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ሰዎች፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ ሥጋ እያሉ፡ በእግዚአብሔር አምነው፡ በእውነትና በታማኝነት ያገለግሉባት ዘንድ፡ እርሱ፡ ዓለምን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፡ ለሰው ልጆች አዘጋጅቶ የሰጣቸው፡ ይህችው፡ በመካከላቸው የምትገኘው መንግሥቱ አይደለችምን? በዚህ ቃሉም፡ ሰዎች፡ እስከዛሬና ወደፊት እስከመጨረሻው፡ በእግዚአብሔር አምነው፡ በእውነትና በታማኝነት ካገለገሏት፡ በምድር ላይ፡ በአካለ ሥጋ እያሉ፡ በአካለ መንፈስ ሲኖሩባት የቆዩትን መልካም ሕይወታቸውን፡ በዚያ የፍርድ ቀን፡ በአዋጅና በይፋ ተቀብለው፡ በአዲሱ የትንሣኤ አካል፡ ለዘለዓለም የሚቀጥሉባት መንግሥቱ አይደለችምን? ነገር ግን፡ እርሱን ክደው፡ በእርሱም ላይ በምሥጢር ዓምፀው፡ የከፋት ሥራን፡ በፍላጎታቸውና በምርጫቸው ሲፈጽሙ ከኖሩ፡ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደተዘጋጀ የዘለዓለም ሥቃይ እንዲኼዱ፡ ፍርዳቸውን የሚቀበሉባት፡ የጻኝነት መንግሥቱ፡ ያችው፡ አንዲቱ፡ የፈተኛዪቱና የኋለኛዪቱ መኾኗን፡ ንጉሡ፡ ለዜጎቹ፡ አስቀድሞ ማሳወቁ አይደለምን?

*መልስ:-* *አዎን! ነው።*

ጥያቄ: በራእየ ዮሐንስ: *"ከሊቃናቱ አንዱ፡ 'እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ እርሱም፡ የዳዊት ሥር፡ መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ፡ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ፡ ድል ነሥቷል!' አለኝ። በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም፡ በሊቃናቱም መካከል፡ እንደታረደ በግ፡ ቆሞ አየሁ፡ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት፡ እነርሱም፡ ወደምድር ኹሉ የተላኩ፡ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው። እርሱም መጥቶ፡ በዙፋን ላይ ከተቀመጠ፡ ከዚያ፡ ከቀኝ እጁ፡ መጽሐፉን ወሰደው። መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ፡ አራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ ሊቃናት፡ በበጉ ፊት ወደቁ፡ እያንዳንዳቸውም፡ በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የኾነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ። 'መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ፡ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፡ ታርደሃልና፡ በደምህም፡ ለእግዚአብሔር፡ ከነገድ ኹሉ፡ ከቋንቋም ኹሉ፡ ከወገንም ኹሉ፡ ከሕዝብም ኹሉ፡ ሰዎችን ዋጅተህ፡ ለአምላካችን፡ መንግሥትና ካህናት ይኾኑ ዘንድ አደረግሃቸው፡ በምድርም ላይ ይነግሣሉ!' እያሉ፡ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።"* ተብሎ የተጻፈው ቃል፡ የሚናገረው፡ ስለየትኛዋ መንግሥት ነው? ስለእኛ፡ በመስቀል ላይ፡ እንደበግ ታርዶና እንደአንበሳ ድል አድርጎ፡ *"እነሆ፡ በመካከላችሁ ናት!"* ያላት፡ ይህችው መንግሥቱ አይደለችምን?

*መልስ:-* *አዎን! ናት።*

*ጥያቄ:-* *"ዓለሙን ኹሉ የሚያስተው፡ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው፡ ታላቁ ዘንዶ፡ እርሱም፡ የቀደመው እባብ፡ ወደምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ፡ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።*

# ምዕራፍ ፫፡ ጸሎት።

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

*" ...በሴቲቱም ላይ ተቈጥቶ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፡ የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን፡ ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ኼደ፡ በባሕር አሸዋም ላይ ቆመ።"* በሚለው፡ በዚሁ በራእየ ዮሓንስ ቃል መሠረት፡ ዘንዶው፡ ተቈጥቶባት እያሳደዳት ያለችው፡ ይህች ሴት ማናት? "ኢትዮጵያ" ተብላ የምትጠራው፡ ዘለዓለማዊቷ ንግሥት ድንግል ማርያም፡ ከንጉሡ ነገሥት ልጇ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የምትመራት፡ ይህችው[፻፴፪] መንግሥት አይደለችምን?

**መልስ፦** *አዎን! ናት።*

**ጥያቄ፦** የእግዚአብሔር ትእዛዛትና የኢየሱስ ምስክር የኾኑትን ቃል ኪዳናት በመጠበቃቸው፡ ዘንዶው እየተዋጋቸው ያሉት፡ "ከሴቲቱ ዘር የቀሩት" የተባሉት ወገኖችስ እነማናቸው? ኢትዮጵያውያን አይደሉምን?

**መልስ፦** *አዎን! እነርሱ ናቸው እንጂ፡ ሌላ ማን ሊኾን ይችላል።*

**ጥያቄ፦** ኢትዮጵያውያንን፡ ከሌሎቹ የዓለም ሕዝቦች፡ የዓለም ሃይማኖተኞችና የዓለም ክርስቲያኖች እንኳ ሳይቀር፡ የተለዩ ያደረጋቸው፡ ዋነኛው መለዮ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥተው፡ እስከዛሬ ድረስ፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ኾነው፡ በእርሷ ሥር የሚተዳደሩ ከመኾናቸው አይደለምን? ለዚህ እውነታም፡ የዚች መንግሥት መታወቂያና መገለጫ የኾኑትን፡ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት፡ ጠብቀውና ሕይወት አድርገው መኖራቸው፤ በስሞቻቸው፡ መጠሪያቸው፡ ምልክቶቻቸውንም፡ በሰንደቅ ዓላማነትና በማንነትምነት አዘጋጅተውና በይፋ አውጥተው፡ የሚሠሩባቸው መኾናቸው፡ በቂ ማስረጃ ኾኖ ይታይ የለምን?

**መልስ፦** *አዎን! በገሃድ ሲታይ ኖርዋል፡ ዛሬም፡ ይኸው፡ እየታየ ነው። እዚህ ላይ ግን፡ ከዚህ ርእስ ሳትወጣ፡ ቀደም አድርገህ፡ ጠቅሰህልን የነበረውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአይሁድ ከሳሽነት ተይዞ፡ ለፍርድ፡ በሮማዊው ጲላጦስ ፊት ቀርቦ ሳለ፡ "መንግሥቴ፡ ከዚህ ዓለም አይደለችም፡ መንግሥቴስ፡ ከዚህ ዓለም ብትኾን፡ ወደአይሁድ እንዳልሰጥ፡ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር። አሁን ግን፡ መንግሥቴ፡ ከዚህ ዓለም አይደለችም።" ብሎ የተናገረው ቃል፡ እስካኹን፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት፡ ካሰማኸን ሐተታ ጋር፡ እንዴት ሊታረቅ እንደሚችል፡ አየይዘህ ብታስረዳን እንወድዳለን።*

**ጥያቄ፦** እስካሁን የጠቃቀስኳቸውንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ያስተማራቸውን ትምህርቶች ትርጓሜ፡ እናንተው፡ ከየመጻሕፍቱ እያወጣችሁ እንድትመለከቷቸው አሳስባችኋለሁ።

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

አኹን ያነጋገችሁት ነጥብ ግን፡ የእእምሮአችሁን ንቃትና ብስለት፡ እንዳለፉት ጊዜያት፡ በበለጠ ያመለከተኝ ስለኾነ፡ እንደገና መደሰቴን ሳልገልጽላችሁ አላልፍም። ለዚህ፡ ለሠነዘራችሁት ጠቃሚ አሳባችሁ፡ ማስታረቂያ የሚኾነውን ፍሬ ነገር ለማግኘት፡ ከዚሁ፡ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልስ ጋር ተያይዞ የተጻፈውን፡ እንዲህ የሚለውን ቃል፡ በማስተዋል ተመልከቱት! "ጲላጦስም፦ 'እንግዲያ ንጉሥ ነህን?' አለው። ኢየሱስም መለሰ: 'እኔ ንጉሥ እንደኾንሁ፡ አንተ ትላለህ። እኔ፡ ለእውነት ልመሰክር፡ ስለዚህ ተወልጃለሁ፡ ስለዚህም፡ ወደዓለም መጥቻለሁ፡ ከእውነት የኾነ ኹሉ፡ ድምፄን ይሰማል፡' አለው። ጲላጦስ: 'እውነት፡ ምንድር ነው?' አለው።" ጲላጦስ፡ ይህን ጥያቄ አቅርቦ፡ መልሱን፡ ከተጠየቂው ለማግኘት አልጠበቀም፡ መልሱን ያወቀ ያስመሰለውን ብያኔውን ለማስፈጸም፡ ወደሌላው ቀጣይ ተግባሩ፡ ዘወር አለ እንጂ፡ ይኸውም፡ ለከሳሾቹ፡ ለአይሁድ፡ "እኔስ፡ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም፡ ነገር ግን፡ በፋሲካ፡ አንድ እሥረኛን ልፈታላችሁ፡ ልማድ አላችሁ፡ እንግዲህ፡ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን?" ሲል ያቀረበላቸው ጥያቄ ነው። ጲላጦስ፡ በዚህ ድርጊቱና አጠያየቁ፡ "እውነት"፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኾነ ማወቁን መሰከረዋል፤

ስለዚህ፡ የእግዚአብሔር የእውነት መንግሥት፡ በዚህ ዓለም ከሠለጠነውና ከሰፈነው፡ የዲያብሎስና የሰዎች፡ የሐሰት መንግሥት የተለየች መኾኗን፡ በገሃድ አግዝፎ ለመግለጽ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "መንግሥቴ፡ ከዚህ ዓለም አይደለችም!" ብሎ ተናገረ። የዚህ፡ የጌታ ቃል እውነተኛነት፡ በመጨረሻ፡ በዚያን ጊዜ፡ የሐሰተኛው ዲያብሎስ ሎሌዎችና አገልጋዮች በኾኑት፡ በአይሁድና በሮማውያን የስምምነት ግፍ ተረጋግጧል። ይኸውም፡ የእግዚአብሔር የእውነት መንግሥት ሕያው መገለጫ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "እናንተ፡ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ፡ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ፡ እርሱ፡ ከመጀመሪያ፡ ነፍስ ገዳይ ነበረ፡ እውነትም፡ በእርሱ ስለሌለ፡ በእውነት አልቆመም፡ ሐሰትን ሲናገር፡ ከራሱ ይናገራል፡ ሐሰተኛ፡ የሐሰትም አባት ነውና። እኔ ግን፡ እውነትን የምናገር ስለኾንሁ፡ አታምኑኝም። ከእናንተ፡ ስለኀጢአት የሚወቅሰኝ ማነው? እውነትን የምናገር ከኾንሁ፡ እናንተ፡ ስለምን አታምኑኝም? ከእግዚአብሔር የኾነ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፡ እናንተ፡ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና፡ ስለዚህ፡ አትሰሙም።" ባላቸው፡ በአይሁድ የሐሰት መንግሥት ከሳሽነት፡ በዘመኑ፡ የዓለም ኀያል ገዢ በኾነው፡ በአረማውያኑ የሮማውያን መንግሥት ተይዞና ታሥሮ፡ ተፈርዶበትና ተሠቃይቶ በመገደሉ ነው።

ደግሞም፡ ጌታ፡ ከመስቀል መከራው በኋላ፡ በሥጋ ሞት በሚለያቸው ጊዜ፡ ሐዋርያት እንዳይደናገጡና ተስፋ እንዳይቆርጡ፡ በማጽናናት የተናገራቸው ቃላት፡ በዚህ ዓለም፡ በሰዎች ዘንድ፡ እጅግ ተንሰራፍቶ በሚገዛው፡ በዲያብሎስ፡ የሐሰት መንግሥትና ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት እናቱ ጋር በሚመራት፡ በእግዚአብሔር የእውነት መንግሥት መካከል ያለውን ልዩነት፡ አጉልተው ያስረዳሉ።

# ምዕራፍ ፫፡ ጸሎት።

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

ከእነዚህ ውስጥ፡ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡ 'አሁን፡ የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሷል፡ አሁን፡ የዚህ ዓለም ገዢ፡ ወደውጭ ይጣላል፡ እኔም፡ ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ፡ ሁሉን፡ ወደእኔ እስባለሁ። ...ልባችሁ አይታወክ! ...አይፍራም! ...በእግዚአብሔር እመኑ! በእኔም ደግሞ እመኑ! '...እኔ እሄዳለሁ፡ ወደእናንተም እመጣለሁ፡' እንዳልኋችሁ ሰማችሁ። የምትወዱኝስ ብትሆኑ፡ ከእኔ፡ አብ ይበልጣልና፡ ወደአብ በመኼዴ፡ ደስ ባላችሁ ነበር። ከሆነም በኋላ ታምኑ ዘንድ፡ አሁን፡ አስቀድሞ ሳይሆን፡ ነግሬአችኋለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ፡ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም፡ የዚህ ዓለም ገዢ ይመጣልና፡ በእኔም ላይ አንዳች የለውም።

"...ዓለም ቢጠላችሁ፡ ከእናንተ በፊት፡ እኔን እንደጠላኝ እወቁ! ከዓለምስ ብትሆኑ፡ ዓለም፡ የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፡ ነገር ግን፡ እኔ፡ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ፡ ከዓለም ስላይደላችሁ፡ ስለዚህ፡ ዓለም ይጠላችኋል።

"...እኔ ባልኼድ፡ አጽናኙ፡ ወደእናንተ አይመጣም፡ እኔ ብኼድ ግን፡ እርሱን እልክላችኋለሁ፡ ...እርሱ፡ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፡ ወደእውነት ይመራችኋል፡ ...እርሱም መጥቶ፡ ስለኃጢአት (ስለሐሰት)፡ ስለጽድቅም (ስለእውነት)፡ ስለፍርድም፡ ዓለምን ይወቅሳል። ስለኃጢአት፡ በእኔ ስለማያምኑ ነው፡ ስለጽድቅም፡ ወደአብ ስለምኼድ፡ ከዚህም በኋላ፡ ስለማታዩኝ ነው፡ ስለፍርድም፡ የዚህ ዓለም ገዢ ስለተፈረደበት ነው። ...በዓለም ሣላችሁ፡ መከራ አለባችሁ! ነገር ግን፡ አይዟችሁ! እኔ፡ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።" የሚሉት ይገኛሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ከእኔ፡ አብ ይበልጣልና" ያለው፡ ሰውነቱን በሚመለከተው አካሉና ባሕርዩ ብቻ መኾኑን፡ እንዲህ ያለበትም ምክንያት፡ ራሳቸው፡ በፍርሃት ተመልተው፥ እርሱንም፡ ገና፡ እንደሰው ብቻ ይመለከቱት የነበሩትን ደቀ መዛሙርቱን[፻፴፫] ሊያበረታታቸው መኾኑን፡ ያስተዋላችሁት አይደለምን?

**መልስ፡-** አዎን! አሁን በበለጠ ልናስተውለው ችለናል።

**ጥያቄ፡-** ታዲያ! ስለእግዚአብሔር መንግሥትና "መንግሥትህ ትምጣ!" የሚለው ጸሎት ምላሽ ስለማግኘቱ፡ እንዲህ ተረጋግጦ የታወቀ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን፡ በዚህ የምሕረት ዘመን፡ የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት፡ "መንግሥትህም መጣችልን።" የሚል ሊኾን አይገባምን?

**መልስ፡-** አዎን! ይገባል።

**ጥያቄ፡-** መልካም! አሁን፡ "ፈቃድህ በሰማይ እንደኾነ፡ እንዲሁ በምድር ይኹን!" ወደሚለው የጸሎቱ ልመና እንኺድ!

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህ፡ የጸሎቱ ቃል፡ በቀ የኾነውን ምላሽ ማግኘቱን፡ አስተውሎ ለመረዳት የሚያዳግተው፡ የሃይማኖት ሰው ይኖራል ብሎ ማሰብ ያዳግታል፡ ምክንያቱም፡ የጸሎቱ ምላሽ፡ እውን ኾኖ፡ በአካልም፡ እጅግ ገዝፎና በግብር ተፈጽሞ ስለታየ ነው፡ ይኸውም፡ ይህ፡ ሰማያዊ ፈቃድ፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም መምጣት፡ ለአማናዊው ሕያው ፍሬ በመብቃቱ ነው:: እንደምታውቁት፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ የአባቱን፡ የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ የፈጸመው፡ በቀላል ገድል አይደለም፡ ከሰማያዊነት፡ ወደምድራዊነት፡ ከልዕልና፡ ወደውርደት፡ ከክብር፡ ወደኅሣር፡ ከሕያውነት፡ ወደመዋቲነት አምዘግዝጎ የጣለውን፡ ሰው የመኾንን ህልውና፡ በአንዲት ድንግል ማሕፀን ውስጥ፡ በተዋሕዶ ሰንሰት በመቀበል፡ በእንስሳት በረት፡ በመወለድና በሕፃንነት በመሰደድ ብቻም አይደለም፡ ነገር ግን፡ ያለአበሳው፡ የመላውን፡ የሥጋዊውን ፍጥረት ኃጢአትና በደል ተሸክሞና ቤዛ ኾኖ፡ ከግርፋቱና የእሾህ አክሊልን ከመቀዳጀት ጀምሮ፡ በመስቀል ላይ ዕርቃኑን ተሰቅሎና በጦር ተወግቶ፡ በመጨረሻዋ የእስትንፋሱ ቅጽበት እንኳ፡ "ተጠማሁ!" ቢል፡ ንጹሕ ጥርኝ ውኃ እንኳ የሚሰጠው አጥቶ፡ በመራራ ሐሞት ጭማቂ፡ የሞት ጽዋውን እስከመቀበል በደረሰ መከራ ጭምር እንደነበረ ይታወቃል:: ይህ፡ እውነት አይደለምን?

መልስ:- *አዎን! እውነት ነው::*

ጥያቄ:- ይህንስ እውነታ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ከመሞቱ በፊት በነበረችው፡ በመጨረሻዋ፡ የሐሙስ ምሽት፡ በሰውነቱ፡ እየወደቀና እየተነሣ፡ ወደአባቱ፡ ወደእግዚአብሔር አብ፡ መላልሶ ሲጸልይ፡ *"አባት ሆይ! ብትፈቅድስ፡ ይህችን ጽዋ፡ ከእኔ ውሰድ! ነገር ግን፡ የእኔ ፈቃድ አይኹን፡ የአንተ ፈቃድ ይኹን እንጂ::"* ብሎ በተናገረው ሃይማኖታዊ ቃሉና በማግሥቱ፡ በዕለተ ዓርብ፡ በምግባር በፈጸመው [፻፴፱] መሥዋዕትነቱ፡ ያረጋገጠው አይደለምን?

መልስ:- *አዎን! አረጋግጦታል::*

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን፡ በዚህ የምሕረት ዘመን፡ የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት፡ *"ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ::"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል::*

ጥያቄ:- መልካም! አኹን ደግሞ፡ *"የዕለት ሲሳያችንን ስጠን ለዛሬ!"* የሚለውን፡ የጸሎቱን ቃል እንመልከት!

## ምዕራፍ ፳፡ ጸሎት።
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

---

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ደቀ መዛሙርቱ ስለጠየቁት፡ በጸሎት መለመንን ከወደዱ፡ ፍላጎታቸውን፡ በዚያችው በዕለቷ ብቻ ወስነው፥ ልመናቸውንም፡ ለዚያችው፡ ለዛሬዋ ቀን ብቻ አድርገው፡ *"'የዕለት ሲሳያችንን ስጠን ለዛሬ!'* ብለው እንዲጸልዩ አስተማራቸው፤ ይህም፡ በዚያው የትምህርቱ ገቢታ ላይ፡ *"ነገ፡ ለራሱ ይጨነቃልና፡ ለነገ አትጨነቁ! ለቀኑ፡ ክፋቱ ይበቃዋል!"* ያለውን በማጽኖት መኾኑን አስተውሉት! "ነገ፡ በሕይወተ ሥጋ፡ ትኖሩ፡ ወይም አትኖሩ እንደኾነ፡ አታውቁትምና፡ መለመን ካስፈለጋችሁ፡ የዕለቱን ብቻ ጠይቁ!" ለማለት ነው። በጸሎት፡ መለመን አስፈላጊ ቢኾን ኖሮ፡ እነርሱ፡ "አስተምረን!" ብለው እስኪጠይቁት ድረስ ባልጠበቀና አስቀድሞ፡ *'የሰማዩ አባታችሁ፡ ሳትለምኑት፡ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና፡ ስትጸልዩ፡ እንደአሕዛብ፡ በከንቱ አትድገሙ!"* ብሎ፡ ባላዘዛቸው ነበር።

በተቀርማ፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ ባለው የተፈጥሮ አእምሮው እንኳ አስተውሎ መመልከት አቅቶትና ተስኖት ነው እንጂ፡ ከሚተነፈሰው አየር ጀምሮ፡ ለሕይወተ ሥጋ የሚያስፈልገውን፡ ምግብንና መጠጥን የሚያጠቃልለውን "ሲሳይ"ማ፡ ለዕለት ብቻ ሳይኾን፡ ለዕድሚያችን እንኳ ሳይቀር፡ እጅግ አትረፍርፎ የሰጠን መኾኑን፡ ይኸው፡ ፍጡሩ ኹሉ፡ በገሃድ የሚያየውና የሚጠቀምበት አይደለምን? እስኪ! ማርና ወተቱን፡ ይህንም የሚያስገኙልንን፡ በአክናፍ የሚበሩትን አእዋፋቱን፥ በእግር የሚሽከረከሩትን እንስሳቱንና በባሕር ውስጥ የሚዋኙትን ዓሣዎቹን ትተን፡ በሕይወተ ሥጋ ቆመን፡ እንድንንቀሳቀስ የሚያደርገንን፡ የምንተነፍሰውን አየር፥ የምናይበትንና የምንሞቀውን የፀሐይ ብርሃን፥ የምንጠጣውን ውኃ፥ የምንበላውን፡ የእህሉን ጥራጥሬ፥ ቅጠላቅጠሉን አትክልትና የተለያየውን በርካታ ፍራፍሬ የምትሰጠንን መሬት እንኳ፡ እስኪ፡ ለአንዲት አፍታ፡ መለስ፡ ቀለስ ብለን፡ አንድ በአንድ፡ በአንክሮ እንመልከታቸው! እነዚህ ኹሉ ሲሳያት የተሰጡን፡ ለሰውነታችን ምግብነት ብቻ ሳይኾን፡ ሊያጠቁን ከሚችሉ፡ ልዩ ልዩ የበሽታና የደዌ ተውሳኮች፡ መከላከያና ፈዋሽ መድኃኒቶች እንዲኾኑን ጭምር መኾኑን ታውቃላችሁን?

**መልስ፡-** *ይገርማል! ይህንስ አናውቅም ነበር።*

**ጥያቄ፡-** ከእነዚህ ኹሉ የሲሳያት ምንጮች የምናገኘው፡ ይኸው ሀብትስ፡ መጠኑ፡ ሊሠፈር፡ በዚህ ጊዜም፡ "ያልቃል!" ሊባልን ይቻላልን?

**መልስ፡-** *አይቻልም።*

**ጥያቄ፡-** ነገር ግን፡ እኛ፡ የሰው ልጆች፡ ይህን ኹሉ እውነታ፡ ዘወትር፡ በዓይኖቻችን፡ በገሃድ እያየንና እያረጋገጥን፡ ፈጣሪያችንን፡ ስለዚህ የቸርነት ስጦታው፡ ልናመሰግነው ቀርቶ፡ ራሳችንም ብንኾን፡ በዚህ፡ የተትረፈረፈ የሕይወት ጸጋ እየተጠቀምን፡ ልንደሰት እንኳ አልቻልንም።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ስለዚህ፡ ፈጣሪያችን "እግዚአብሔር ወልድ"፡ ይህንኑ ችግራችንን ስለተመለከተ፡ ደካማውንና በደለኛውን ሰብአዊ ተፈጥሮአችንን ተዋሕዶ፡ እነሆ፡ ይህን፡ *"የዕለት ሲሳያችንን ስጠን ለዛሬ!"* የሚለውን ጸሎት፡ ራሱ፡ ቀደም ብሎ፡ ወደአባቱ፡ ወደእግዚአብሔር አብ፡ ጸልዮት፡ "እናንተም፡ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ!" ብሎ፡ ለጠየቁት ደቀ መዛሙርቱ፡ አስተማራቸው::

ፈጣሪ፡ ለሰብአዊ ፍጡሩ ስላበረከተው፡ የቸርነት ስጦታው፡ እዚህ ላይ ከተነማ ዘንድ፡ ለእየራሳችን ልናቀርበው የሚገባን፡ አንድ መሠረታዊ ጥያቄ አለ፡ ይኸውም፡ ከሥጋዊው ፍላጎታችን ዓይነትና መጠን ይልቅ፡ እጅግ የሚበልጠውን፡ በእርሱ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርንባትን፡ የነፍስ ባሕርያችንንና የሥጋ አካላችንን የሚጨምረውን፡ ይህን ሰውነትና ለዚሁ ሰውነታችን የሚያስፈልገንን ሲሳይ ያገኘነው፡ እኛ፡ አስፈላጊነቱንና ጠቃሚነቱን፡ አስቀድመን፡ አውቀንና ተረድተን፡ ጠይቀንና ለምነን፡ ወይም አስበነውና አልመነው እንኳ እንደነበረ ወይም እንዳልነበረ፡ ለይቶ የሚያመለክተው፡ የየራሳችን ጥያቄ ነው:: ታዲያ! ለዚህ ጥያቄያችን፡ እናንተ፡ እየራሳችሁ የምትሰጡት መልስ፡ ከቶ፡ የትኛውን ይኾን? እስኪ ንገሩኝ?

**መልስ:-** *እኛንማ ከጠየቅኸን፡ መልሳችን የሚኾነው፡ "ይህን ሰውነትና ለዚሁ ሰውነታችን የሚያስፈልገንንና የሚጠቅመንን ሲሳይ ያገኘነው፡ እኛ፡ አስፈላጊነቱንና ጠቃሚነቱን፡ አስቀድመን አውቀንና ተረድተን፡ ጠይቀንና ለምነን፡ ወይም አስበነውና አልመነው እንኳ አይደለም፡" የሚል ነዋ!*

**ጥያቄ:-** ደግሞስ፡ ይህን ኹሉ ሲሳይ፡ እርሱ፡ ራሱ፡ ፈጣሪያችን፡ አስቀድሞ አዘጋጅቶ፡ ጸጋና በረከትም አድርጎ የሰጠን አይደለምን?

**መልስ:-** *አዎን! ነው::*

**ጥያቄ:-** ስለዚሁ የተትረፈረፈ ስጦታውስ፡ *"እላችኋለሁ፡ ስለነፍሳችሁ፡ በምትበሉትና በምትጠጡት፡ ወይም፡ ስለሰውነታችሁ በምትለብሱት፡ አትጨነቁ! ነፍስ፡ ከመብል፡ ሰውነትም፡ ከልብስ አይበልጥምን? ወደሰማይ ወፎች ተመልከቱ! አይዘሩም፡ አያጭዱምም፡ በጎተራም አይከቱም፡ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፡ እናንተ፡ ከእነርሱ፡ እጅግ አትበልጡምን? ከእናንተ፡ ተጨንቆ፡ በቁመቱ ላይ፡ አንድ ክንድ መጨመር፡ የሚችል ማነው?*

*"ስለልብስስ፡ ስለምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች፡ እንዴት እንዲያድጉ፡ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ! አይደክሙም፡ አይፈትሉም፡ ነገር ግን፡ እላችኋለሁ:- 'ሰሎሞንስ እንኳ፡ በዚያ ኹሉ ክብረቱ፡ ከእነዚህ፡ እንደአንዱ አልለበሰም:: እግዚአብሔር ግን፡ ዛሬ ያለውን፡ ነገም የሚደርቀውን፡ የሚቃጠለውን፡ የሜዳውን ሣር፡ እንዲህ የሚያለብሰው ከኾነ፡ እናንተ፡ እምነት የጐደላችሁ፡ እናንተንማ፡ ይልቁን እንዴት አብልጦ አያለብሳችሁም!?*

## ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት።
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

*"እንግዴህ፡ 'ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን?' ብላችሁ አትጨነቁ! ይህንስ ኹሉ፡ አሕዛብ* (ስለእግዚአብሔር፡ እውቀቱና ሃይማኖቱ የሌላቸው ሰዎች፡) *ተጨንቀው ይፈልጉታል፤ ለእናንተ ግን፡ ይህ ኹሉ እንዲያስፈልጋችሁ፡ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ስለዚህ፡ እናንተ፡ አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ እውነቱንም ፈልጉ!*[፮፡፴፫] *ይህም ኹሉ ይጨመርላችኋል።"* ብሎ ያስተማረውን ታውቁት የለምን?

መልስ:- *አዎን! እናውቀዋለን።*

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን፡ በዚህ የምሕረት ዘመን፡ የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት፡ *"የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን።"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል።*

ጥያቄ:- መልካም! ቀጥሎ፡ *"በደላችንን፡ ይቅር በለን፤ እኛ ደግሞ፡ የበደሉንን ይቅር እንደምንል!"* በሚለው፡ በተከታዩ የጸሎቱ ቃል ላይ እናተኩራለን።

ፈጣሪያችን፡ ለሥጋዊው የሰውነት አካላችንና ባሕርያችን፡ የሚያስፈልጉን ሲሳያት፡ "እኒህ ናቸው፡" ብለን፡ ዓይነታቸውንና መጠናቸውን አስቀድመን አውቀን፡ ለይተንና ዘርዝረን አቅርበንለት፡ ሳንጠይቀውና ሳንለምነው፡ እንዲህ አድርጎ፡ አትረፍርፎ መስጠቱ ብቻ ሳይኾን፡ ለነፍሳዊው የሰውነት አካላችንና ባሕርያችን ጭምር፡ የሚያስፈልገንን ልዩ ሲሳይ፡ አሁንም፡ ሳንጠይቀውና ሳንለምነው፡ እጅግ አትረፍርፎ፡ በፈቃዱ ያበረከተልን መኾኑን አስተውላችሁታልን?

ይህም የነፍሳችን ሲሳይ፡ እንደሥጋዊው ምግብና መጠጥ፡ ጊዜያዊውንና ምድራዊውን ረሃብ ብቻ የሚያጠግብ፡ ጥማቱንም ብቻ የሚያረካ ሳይኾን፡ ዘለዓለማዊውንና ሰማያዊውን ረሃብ፡ እንዲያጠግብ፡ ጥማቱንም፡ እንዲያረካ፡ ለነፍስ፡ የዘወትር ምግብና መጠጥ ኾኖ፡ ከዘለዓለማዊው መጋቢያችን የተሰጠን ነው፤ ከዚህ የተነሣ፡ ይኸው ሲሳይ፡ ለሥጋዊው የሰውነታችን አካልና ባሕርይ ጎጂ የኾነውን፡ ማናቸውንም የደዌያችንን ተውሳክ አስወግዶ፡ ፍጹም ፈውስን አጐናጽፎናል፤ ደግሞም፡ ለነፍሳዊው የሰውነታችን አካልና ባሕርይ፡ መርገም የኾነውን፡ ከፈጣሪያችን የለየንንና ለሞት የዳረገንን፤ የኃጢአታችንንና የበደላችንን ጠንቅ ደምስሶ፡ መለኮታዊውን ፍጹም ምሕረትና ዘለዓለማዊውን ሕይወት አስገኝቶልናል። እኛም የበደሉንን ኹሉ ይቅር እንል ዘንድ ያስቻለን፡ ይኸው፡ እኛ ይቅር የተባልንበት ሲሳይ ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይህ፡ ፍቱን መድኃኒትና የኃጢአት ማስተስረያ ኾኖ፡ ከእውነተኛው ዘለዓለማዊ ሐኪም የተሰጠን፡ ልዩና ዘለዓለማዊ የዘወትር ሲሳይ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መኾኑን፡ ቀደም ብለን ባደረግነው ውይይታችን፡ ያወቃችሁት አይደለምን?

መልስ:- *አዎን! አውቀነዋል።*

ጥያቄ:- *“የዕለት እንጀራችንን፡ ስጠን ለዛሬ!”* እንድንለው የፈቀደ አምላካችን፡ የዕለቱን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልጉንን ሲሳዩት አትረፍርፎ መስጠቱ፡ ይህንኑም አስተውለን፡ እንድናመሰግነው የሚያደርገንን ልቦና መለገሡ ሲገርመን፡ ከዚህ በላይ፡ አልፎ ተርፎ፡ ያልጠየቅነውንና ያልጠበቅነውን፡ ታላቁን የቸርነት ሥራውን በመቀጠል፡ ለዘለዓለም ከማይነጥፍ ጎተራው፡ ለዘለዓለም ከማይደርቅ ምንጩም፡ ለዘወትር ሲቆረስና ለዘወትር ሲቀዳ የሚኖረውን፡ እንጀራና መጠጥ፥ ይኸውም፡ የዘለዓለም ሕይወትን የሚያስገኘውን፡ የራሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ *“እንካችሁ፡ ብሉ! ጠጡ!”* ብሎ ማበርከቱ ደግሞ፡ በአስተዋይ ተመልካች ላይ፡ ምን ዓይነት የተመሰጦ ስሜትን ያሳድራል?

መልስ:- *በእኛ በኩል፡ በአንደበት፡ ሊነገር፥ በቃላትም ሊገለጽ የሚቻል አይመስለንም።*

ጥያቄ:- ለዚህ ኹሉ ስጦታው ፍጹምነት፥ እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ ይቅር ለማለት እስከምንችልበት ብቅዓት ለመድረሳችን፡ አጠቃላዩ ማረጋገጫ፡ *“እናንተ፡ ክፉዎች ስትኾኑ፡ ለልጆቻችሁ፡ መልካም ስጦታን መስጠትን ካወቃችሁ፡ በሰማይ ያለው አባት፡ ለሚለምኑት፡ እንዴት አብልጦ፡ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው!?”* የሚለው አይደለምን?[፻፴፯]

መልስ:- *አዎን! ነው።*

ጥያቄ:- *ታዲያ!* እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን፡ በዚህ የምሕረት ዘመን፡ የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት፡ *“ለዘላለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስስህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን። እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።”* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል።*

## ምዕራፍ ፭፣ ጸሎት።
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

---

ጥያቄ:- መልካም! አኹን ቀጥለን: ከዚሁ ጋር የተያያዘውን: *"አቤቱ! ወደፈተና አታግባን! ከክፉ ኹሉ: አድነን እንጂ።"* የሚለውን: የጸሎቱን ቃል እንመርምር!

እስካኹን አስተውለን ከተመለከትናቸው: ከእነዚህ ኹሉ ስጦታዎቹ በላይ: እግዚአብሔር: ኢትዮጵያውያን ሕፃናት: ወንዶቹ: በአርባ ቀናቸው: ሴቶቹም: በሰማንያ ቀናቸው: የክርስትና ሥርዓተ ጥምቀታቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ: ፍጹም የኃጢአት ስርየትን አግኝተው: በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር የኪዳን ልጆች የመኾንን ጸጋ ተቀዳጅተው: በዚህ ክብር እንዲኖሩ እንደሚያደርጋቸው አውቀችኋል። ይህ: ዘለዓለማዊ ልጅነት የተገኘው: እግዚአብሔር ወልድ: ሰው ኾኖ: ከዲያብሎስና የእርሱ *መሣሪያዎች* ከኾኑ ሰዎች በተቀበላቸው መከራዎች: በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ባፈሰሰው ደሙ: ሞቶ በመቀበሩና መበስበስን አጥፍቶ በመነሣቱ መኾኑን: ይህም ማለት: የክፋትን ኃይል: ድል ስላደረገ: የኃጢአትን ቀንበር ስለሰበረና የሞትን ዕዳ ስለሻረ መኾኑን ተረድታችኋል።

ከዚህ የተነሣ: የእግዚአብሔር ልጆች: በዚህ ልጅነታቸው: ከራሳቸው የተፈጥሮ ጠንቅ: ከዲያብሎስ የክፋት ጦርና ከዓለሙ የተዕዕኖ ኃይል: በተለያየ ረቂቅ መንገድ: ከሚዘረጋባቸው የፈተና ወጥመድ: ነጻ ለመኾን ስለቻሉ: መንፈሳዊውን አካልና ባሕርይ ተጎናጽፎ: በሥጋና በነፍስ ውሕደት የሚንቀሳቀሰውን ሰውነታቸውን: የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ላስገኘው: ለመጨረሻው መልካም ህልውና አብቅተውታል። ይህንም እውነታ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ለደቀ መዛሙርቱ: *"በዓለም ሳላችሁ: መከራ አለባችሁ! ነገር ግን: አይዟችሁ! እኔ: ዓለምን አሸንፌዋለሁ።"* ደግሞም: በመጨረሻዋ ሐሙስ ማታ: በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ሣለ: *"...ወደፈተና እንዳትገቡ: ትጉና ጸልዩ! መንፈስስ ተዘጋጅታለች: ሥጋ ግን: ደካማ ነው:"* ካላቸው በኋላ: *"እንግዲህስ ተኙ! ዕረፉም!"* ብሎ: በተናገራቸው ቃሎቹ አጽድቆታል።

በእነዚህ ቃላትና እስካኹን ባገኛችሁት እውቀት: *"አቤቱ! ወደፈተና አታግባን! ከክፉ ኹሉ: አድነን እንጂ።"* የሚለው: የጸሎቱ ቃል: መልስ ማግኘቱ አልተረጋገጠምን?

መልስ:- *አዎን! ተረጋግጧል።*

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ: እኛ ኢትዮጵያውያን: ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን: በዚህ የምሕረት ዘመን: የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት: *"የንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን: የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን። ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፋው ኹሉ አድነኸን: ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ: በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን።"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

**ጥያቄ:-** መልካም! ከዚህ በኋላ፡ *“መንግሥት የአንተ ናትና፥ ኃይልና ምስጋናም፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን!”* ስለሚለው፡ ስለጸሎቱ የመዝጊያና የማጠቃለያ ቃል እንነጋገራለን::

እግዚአብሔር አብ፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ስላደረገው የቸርነት ሥራው፡ “ልቦናው፡ በእውነተኛ የፍቅር ስሜት፡ በጥልቀት የማይነካ ሰብአዊ ፍጡር ይኖራል፧” ብሎ ማሰብ፡ ለማንኛውም አስተዋይ ተመልካች ያዳግታል:: ይህ አምላካዊ የቸርነት ሥራ፡ በፍጡር አንደበት ሊነገርና በእጅ ሊጻፍ ቀርቶ፡ በሕሊና እንኳ ሊታሰብ አይሞከርም:: ከዚህም ጋር፡ ቀደም ብለን፡ አግባብነት ባለው፡ በየቦታው ላይ እያነሣን፡ እስካኹን ስንወያይ እንደቆየነው፡ እግዚአብሔር፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላደረገው፥ “ይህ ቀርቷል!” የሚባል አንዳች ነገር እንዳለ፡ እስኪ፡ በእናንተ በኩል የምታስቡትን ንገሩኝ?

**መልስ:-** *ጨርሶ፡ ምንም የለም!* አሉ፡ እያንዳንዳቸው፡ ወደመሬት አቀርቅረው፡ ቡተመስጦ ካሰቡ በኋላ::

**ጥያቄ:-** እንዲያ ከኾነማ፡ ፊት፡ አዳምና ሔዋን፥ ከእነርሱ ቀጥሎ፡ ቃኤልና ልጆቹ፡ ለጠላት ዲያብሎስ አሳልፈው ሊሰጡበት ሞክረው፥ ነገር ግን፡ አቤልና ልጆቹ ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ቀድሞ፡ *“ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!”*፥ ኋላም፡ *“ምእ ኣንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!”* በሚሉት አምላካውያት ቃላትና መለኮታውያን ምልክቶች ጠብቀው ያኖርዋትን አማናዊት “*መንግሥቱ*”ን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መልሶ ከእጁ አግብቷት፡ በምድር ላይ እንደገና እንድትሰፍን አደረገ አይደለምን?[፻፴፰]

**መልስ:-** *አዎን! እኛ፡ “ትንግርት” የምንለውን፡ ይህን ሥራ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸሙን፡ እነሆ፡ ለእየራሳችን አረጋገጥን::*

**ጥያቄ:-** ይህም የኾነው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ *“ሥልጣን ኹሉ፡ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ!”* ብሎ፡ በተናገረው የምሥራች ቃሉ መሠረት መኾኑን፡ እናንተም ያወቃችሁት አይደለምን?[፻፴፱]

**መልስ:-** *አዎን! ነው::*

**ጥያቄ:-** ደግሞስ፡ በኃይሉ ሳይኾን፡ ጠላትን በመውደድና ለጠላቱ፡ ራሱን ቤዛ በማድረግ፡ በፈጸመው የፍቅርና የምሕረት መሥዋዕትነቱ፡ የማትበገር “ኃይልን”፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መልሶ፡ የራሱ አላደረጋትምን?

**መልስ:-** *አዎን! በእውነት፡ መልሶ፡ የራሱ አድርጓታል::*

## ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት።
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሓተታ።

---

*ጥያቄ:-* ይህም የኾነው፡ "እነሆ፡ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ፡ የእግዚአብሔር በግ!" የተባለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "እንደበግ፡ ወደመታረድ ተነዳ፡ የበግ ጠቦትም፡ በሸላቹ ፊት፡ ዝም እንደሚል፡ እንዲሁ፡ እርሱም፡ አፉን አልከፈተም፡" የሚለውን፡ የነቢዩን ቃል ለመፈጸም፡ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ በመሞትና በመቀበር፡ ከዚያም፡ ከሙታን ተለይቶ በመነሣት፡ የሰውን፡ የዘር ጠላት፡ ፈጽሞ ድል ስላደረገ፡ ሓዋርያው፡ "የእግዚአብሔር ኀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የኾነው ክርስቶስ ነው፡" ብሎ በሰጠው ምስክርነት፡ እርሱ፡ ራሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ "አይዟችሁ! እኔ፡ ዓለሙን አሸንፌዋለሁ፡" ብሎ በተናገረው ቃሉ መሠረት፡ አይደለምን?[፻፶፯]

*መልስ:-* አዎን! ነው።

**ጥያቄ:-** ከዚህ ኹሉ የተነሣስ፡ ይህን የመሰለው፥ ወደርና ወሰን የሌለው ቸርነት፡ ከፈጣሪው ስለተደረገላት፡ በመጨረሻ፡ ፍጥረቱ ኹሉ፡ በነፍስ ወከፍ፡ ከየራሱ አንቅቶ፡ የራሱን ደስታ ለመግለጽ፡ አምላኩን እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው ስለኾነ፡ ንጹሕ "ምስጋና"፡ የእርሱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የብቻው አልኾነችምን?

*መልስ:-* አዎን! በፍጹም፡ የእርሱ፡ የብቻው ኾናለች።

ጥያቄ:- ይህም የኾነው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ከመነሣቱ በፊት፡ *"ደቀ መዛሙርቱ፡ ኹላቸው፡ ደስ እያላቸው፡ ተአምራትንም ኹሉ ስላዩ፡ በታላቅ ድምፅ፡ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ ጀምረው፡ 'በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ንጉሥ፡ ቡሩክ ነው፡ ሰላም፡ በምድር፡ በአርያምም፡ ምስጋና ይኹን!' ሲሉ፡ በመቅደስም፡ 'ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ!' እያሉ፡ የሚጮኹትን ልጆች ሲያዩ፡ የካህናት አለቆችና ጻፎች፡ ተቈጥተው፡ 'እነዚህ፡ የሚሉትን፡ አትሰማምን?'፡ ከሕዝብና ከፈሪሳውያንም መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ 'መምህር ሆይ! ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው!' ባሉት ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልሶ፡ 'እሰማለሁ፡ እላችኋለሁ፡ "ከሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ፡ ምስጋናን፡ ለራስህ አዘጋጀህ!" የሚለውን ቃል፡ ከቶ አላነበባችሁምን? እነዚህ ዝም ቢሉ፡ ድንጋዮች ይጮኹሉ!' አላቸው።"*[፻፶፰] በሚለው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል መሠረት አይደለምን?

*መልስ:-* አዎን! ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጥያቄ፡- እዚህም ላይ፡ ልታስተውሉት የሚገባ፡ አንድ፡ ታላቅ ቍም ነገር አለ፤ ይኸውም፡-

፩ኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን የጸኑት ኢትዮጵያውያን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ እያሉ፡ በእውነትና በመንፈስ እየኖሩዋት መኾናቸውን፥

፪ኛ፡ ግዙፉ ዓለም፡ ይህች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በምድር ላይ፡ በይፋ መስፈኗን፡ በገሃድ ለሚያይባት ቀን እንዲበቃ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የሚጸልዩት፡ ለእርሱ፡ ለግዙፉ ዓለም እንጂ፡ ለእነርሱ፡ አለመኾኑን፥

፫ኛ፡ ያችም ቀን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በተስፋ ቃሉ፡ ለተከታዮቹ ያመለከታት፡ ዳግም ምጽአቱ መኾኗን፥

፬ኛ፡ በዲያብሎስ አበጋዝነት በሚካኼደው የክፋት ኃይል፥ በኃጢኣት ማዕበል ተጥለቅልቆ በመስጠምና በቀሣፊው የሞት ሠይፍ እየተፈጀ ያለው፡ ይኸው ግዙፉ ዓለም፡ ይህችኑ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ በሐሰት የጨለማ እውቀት፡ በተሸፈኑ ዓይኖቹ፡ ዛሬ ሊያያት ስላቃተው፡ ራሱን፡ በእውነት የብርሃን እውቀት ገላልጦ እንዲመለከታት፡ የሚያስችለውን ኃይል የሚያገኘው፡ በዚያች ቀን መኾኑን፥

፭ኛ፡ ዛሬ፡ በምድር ላይ ሰፍኖና ገንኖ፥ አይሎም የሚታየውን የዲያብሎስን ክፋት፥ ከእርሱ የተነሣም፡ በሰዎች ላይ የሠለጠነውን ኃጢአትና ያ ምርጫ ያስከተለውን ሞትን፡ ከግዙፉ ዓለም፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ የፍቅርን፥ የሰላምንና የዕረፍትን ሕይወት፡ ለሰው ልጆች፡ መልሳ የምታመጣ፡ ይህች፡ የእግዚአብሔር፡ የእውነት መንግሥት ስለኾነች፡ ኢትዮጵያውያን፡ የዚያችን ቀን መድረስ፡ በሃይማኖት ነቅተውና በምግባር በቅተው የሚጠብቁ መኾናቸውን፥

፮ኛ፡ *“ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ”* የሚለው መለኮታዊ ቃል የተሰጠው፡ ሟች ለኾነ ዕሩቅ ብእሲ ሳይኾን፡ ለዘለዓለም ሕያው ኾኖ ለሚኖረው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ስለኾነ፡ ንጉሥነቱና መንግሥቱ፡ የሚለወጥና የሚያረጅ፥ የሚፈርስና የሚሻር አለመኾኑን፥

፯ኛ፡ ይህች የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ዛሬና ለዘለዓለሙ፡ በምድርም፥ በሰማይም፡ የምትመራውና የምትተዳደረው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሠ ነገሥትነት፥ በድንግል ማርያምም መቅደስነትና ንግሥትነት መኾኑን ነው።

ይህን እውነታ፡ እስካኹን በደረሳችሁበት እውቀት፡ የተረዳችሁት አይደለምን?

መልስ፡- አዎን! በእርግጥ ተረድተነዋል።

## ምዕራፍ ፭፡ ጸሎት::

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ::

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ቸርነት ላደረገልን ፈጣሪያችን፡ በዚህ የምሕረት ዘመን፡ የምናቀርብለት የምስጋና ጸሎት፡ *"ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፡ ፍቅርህና ጸጋህ፡ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን::*

*"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" በተባለው፡ በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፡ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለማዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን::*

*"ኃይልና ምስጋና፡ መንግሥትም ያንተ ናቸው፡ ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን::"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- አዎን! ይገባል::

ጥያቄ:- እንግዲያስ፡ ራሱን፡ በእኛ ቦታ አስገብቶ፡ ራሱ፡ ስለእኛ ጸላይ፥ ራሱ፡ ጸሎት፡ ራሱ፡ የጸሎቱ ተቀባይ በመኾን፡ ይህን ኹሉ የቸርነት ሥራውን ለሠራልን፡ ፍጹም ደግ ፈጣሪ፡ በተለይ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ "ልጅህ፡ 'እንዲህ በሉ!' ብሎ፡ ያስተማረንን፡ ያን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ:-

፩ኛ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን የሚያስፈልገንን፡ ይህን ያህል፡ የማያልቅ ሲሳይ፥ ፍቱን መድኃኒትና ለዘለዓለም የሚኾን ሕይወትን፡ አትረፍርፈህ በመስጠት፡ ቸርነትህን፡ እንዲህ ስላበረከትክልን፥

፪ኛ፡ ከፍጥረታችን መጀመሪያ አንሥተን፡ ከሕያው ቃልህ ውጪ፡ በአንተ ላይ፡ ያን ኹሉ ክህደትና ዓመፅ፥ ክፋትና ጥፋት በመፈጸማችን፡ በየራሳችን ላይ ያመጣነውን የሞት ፍዳ፡ ራስህን፡ ለእኛ ቤዛ አድርገህ፡ በመስቀል ላይ በመሠዋት፡ ይቅር ብለህ፡ እንዲህ፡ ምሕረትህን ስላደረግህልን፥

፫ኛ፡ ስለእኛ፡ ሰው ኾነህ፡ ለእኛ ለጠላቶችህ፡ እስከመሞትና እስከመቀበር በደረሰ ጽናት፡ ፍቅርህን፡ በጉልህና በግዘፍ፡ እንዲህ ስለፈጸምክልን፥

፬ኛ፡ ይህን ኹሉ ቸርነት፥ ምሕረትና ፍቅር፡ ለእኛ ለፍጡራንህ ማበርከትህ፥ ማድረግህና መፈጸምህ ሳይበቃህ፡ እንደገና፡ የአንተ የባሕርይ ገንዘቦችህ የኾኑትን፡ እውነትህንና እውቀትህን፥ መንግሥትህንና ሕይወትህን፡ በኹለንተናችን ውስጥ የሚመላልንን፡ ቅዱሱን መንፈስህን ስለሰጠኸን፡ እናመሰግንሃለን::" ቢባል፡ ይበዛልን?

መልስ:- ያንሳል እንጂ፡ እንዴት ይበዛል?!

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

"እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

ጥያቄ:- መልካም! እንግዲህ፡ እንዲህ አድርገን፡ የ"አቡነ ዘበሰማያት"ን ሐተታ ከጨረስን፡ እኹን፡ ቀጥለን፡ የምንወያየው፡ *"በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ!" እያልን፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ስለምናቀርበው የሰላምታ ጸሎት ይኾናል።*

መልስ:- *እሺ! የምንጠብቀው ስለኾነ፡ ደስ ይለናል።*

ጥያቄ:- እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ለድንግል ማርያም የምናቀርበው፡ ይህ፡ የሰላምታ ጸሎታችን ተውጣጥቶ የተዘጋጀው፡ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ አምላክን ስለመጽነሷ፡ ምሥራቹን ባሰማት ጊዜ፡ ለእርሷ ያቀረበውን ሰላምታና የዮሓንስ መጥምቁ እናት፡ ቅድስት ኤልሣቤጥም፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ፡ ሕፃኑ ዮሓንስ፡ በማሕፀኗ እየዘለለ፡ ስለእርሷ ያሰማችውን የልዕልና ቃል፡ ራሷም፡ እመቤታችን የተናገረችውን የእግዚአብሔርን ቃል፡ መነሻ በማድረግ ነው፡ ይህም፡ ጥንት፡ ከአዳምና ሔዋን ፍጥረት ጋር ተያይዞ፡ እስከእርሷና እስከልጇ መገለጥ ድረስ ባለው ረዥም ዕድሜ ውስጥ የኾነውን፡ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ያጠቃልላል። የጸሎቱ ቃል፡ አጭርም ቢኾን፡ ምሥጢሩ፡ እጅግ የጠለቀ፥ መልእክቱም፡ እጅግ የላቀ ስለኾነ፡ በማስተዋል ልትከታተሉት ያስፈልጋችኋል።

እግዚአብሔር ወልድ፡ *"አባቴ!"* ብሎ የሚጠራውን፡ የባሕርይ አባቱን፡ እግዚአብሔር አብን፡ እኛም፡ *"አባታችን!"* ብለን እንድንጠራው ስለወደደ፡ *"'አባታችን ሆይ!' በሉ!"* ብሎ ያዘዘን መኾኑን አውቃችኋል። እንዲሁ ኹሉ፡ በሰውነቱ፡ ከእርሷ ተወልዶ፡ "እናቴ!" ብሎ የሚጠራትን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ *"እነኋት እናትህ!"* ብሎ፡ ለደቀ መዝሙሩ፡ ለዮሓንስ፡ በአደራነት በሰጠው እናትነቷ፡ እኛንም፡ የዚያ ባለአደራነት ተካፋዮች እንዳደረገን፡ እናንተም፥ እኔም እናምናለን።

ታዲያ! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህን ማድረጉ፡ እግዚአብሔር አብን፡ *"አባታችን ሆይ!"* ብለን በምንጠራበት አንደበታችን፡ እርሷንም፡ *"እናታችን ሆይ!"* ብለን እንድንጠራት ቢፈቅድ አይደለምን? ይህም ማለት፡ በዚህ መለኮታዊ ፈቃዱ፡ እርሱ፡ የባሕርይ አባቱ፡ የእርሱ ብቻ ሳይኾን፡ የእኛም አባት እንዲኾን እንዳደረገ ኹሉ፡ የሰውነት እናቱም፡ የእርሱ ብቻ ሳትኾን፡ የእኛም እናት እንድትኾን አደረገ ማለት አይደለምን?[፻፺፱]

መልስ:- አዎን! ነው።

# ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት::
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ::

---

ጥያቄ:- እኛስ ኢትዮጵያውያን: "እመቤታችን!" የምንላት: ያንኑ: "የእናትነቷን" እውነታ: መሠረት ያደረገውን ይትበሃል ይዘን መኾኑን: ከቃሉ ትርጉም ትረዱት የለምን? ይኸውም: በግእዙ: "እመቤት" የሚለው: "እም": "እናት": "ቤት": "ቤተሰብ" ማለት ስለኾነ: "የቤተሰቡ እናት" ማለት በመኾኑ ነው:: ደግሞስ: ጥንት: ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ: በኅብረት ስንኾን: "እምነ ጽዮን": "እናታችን ጽዮን"፤ ኋላም: በዘመነ ሐዲስ: "ማርያም: እምነ!" "እናታችን ማርያም!" እያልን፥ በግልም: "እምዬ ማርያም!" "እናቴ ማርያም!" እያልን: በየጸሎታችን ላይ የምናወሳት: ከዚህ የተነሣ አይደለምን?

መልስ:- *አዎን! ነው::*

ጥያቄ:- የቀድሞዎቹ የሰው ልጆች: በሥጋ መወለድንና ለዲያብሎስ መገዛትን: በኀጢአት መታሠርንና ለሞት መዳረግን የወረሱት: ከመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ሲኾን: እኛ: የዛሬዎቹ ደግሞ: በመታደል: በመንፈስ ቅዱስ: ከእግዚአብሔር የመወለድንና የመንግሥቱ ተካፋዮች የመኾንን: ኹለንተናዊ ነጻነትን የመቀዳጀትንና የዘለዓለም ሕይወትን የመውረስን ክብር ለማግኘት የበቃነው: በዳግማዊው አዳም: በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና በዳግማዊቷ ሔዋን: በቅድስት ድንግል ማርያም: የአምላክ እናትነት መኾኑን አውቀናል፡ ስለዚህ: በሥጋ ልደት ያስገኘችን ስለኾነች: የመጀመሪያዋን ሴት: ሔዋንን: "እናታችን!" ብለን እንጠራት እንደነበረ ኹሉ፡ እንዲሁ: ለሰውነት ባሕርያችን መመኪያና ለመዳናችን ምክንያት ኾና: ለእግዚአብሔር ልጅነት ያበቃችንን: ድንግል ማርያምን ደግሞ: አማናዊቷና ዘለዓለማዊቷ እናታችን አድርገን: "እናታችን" ብለን ልንጠራት አይገባንምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባናል::*

ጥያቄ:- ቀደም ብለው በተገለጹት ምክንያቶች: ፈጣሪያችንን: *'አባታችን!'* ብለን የምንጠራ ከኾነ: በተለይ: እኛ ኢትዮጵያውያን: ከጥንት ጀምረን: በኖኅ መርከብና በሙሴ ጽላት፥ በቀሩትም ቅዱሳት ኪዳናት: ደግሞ: *"እጆቿን: ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!"* በተባለችው: በዳዊት መዝሙርዋ *"ኢትዮጵያ"*፥ እንዲሁም: ወደኢየሩሳሌም ተጕዛ: ከእስራኤላዊው ዳዊትና ከኢትዮጵያዊቷ ቤትሳባ ልጅ: ከንጉሥ ሰሎሞን: ልጇን ምኒልክን በወለደችው በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት: በማክዳ አርአያነት እየተመለከትናት፤ በልዩ ልዩ ምሳሌዎችና አካላት፥ በመንፈስና በሥጋም እያየናት: አብራን: የኖረችውን ድንግል ማርያምን: "እናታችን" ብለን ልንጠራት አይገባንምን?

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*መልስ፡-* *አዎን! በእርግጥ ይገባናል። እዚህ ላይ ግን፡ ያለሁን ማብራሪያ ኢየይዘህ እንድትገልጽልን፡ አንድ ነገር እንድናነሣብህ፡ እጅግ አስፈልጎናል፥ ይህን ነገር፡ ልናነሣብህ የፈለግንበት ምክንያት፡ ነገሩ፡ ሃይማኖትን የሚመለከት ስለኾነ፥ በሃይማኖት ደግሞ፡ ምንም ዓይነት ነቀፅ ሊኖር ስለማይገባ፡ ሰብአዊው ሕሊናችን፡ አንዳች የኑፋቄ እንከን የሌለበት፡ ፈጽሞ የጠራ ንጹሕ እንዲኾን ስለቆረጥንበት ነው።*

*ደግሞም፡ ነገሩ፡ ምናልባት፡ በሌሎች አእምሮ ውስጥ የሚወጣና የሚወርድ፡ ከስሕተትም የሚያደርስ ስለኾነ፡ ኹሉንም፡ ከዚያ ውድቀት ለማዳን ይኾናልና፡ ይህንኑ ነገር፡ በጥያቄ መልክ እንድንገልጽልህ ግድ ኾኖብናል። ይኸውም፡ "ፈጣሪያችንን፡ 'አባታችን እግዚአብሔር ሆይ!' ብለን በጠራንበት አንደበታችን፡ እርሷን፡ ፍጡርዋን፡ 'እናታችን ማርያም ሆይ?' ብለን ስንጠራት፡ ፍጡርን፡ ከፈጣሪ ጋር፡ ማለትም፡ ሰውን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከል አይኾንምወይ?" የሚለውን አስተሳሰብ፡ የሚመለከት ነው።*

ጥያቄ፡- መልካም! ውይይታችንን የተለየ የሚያደርገው፥ እኔም፡ በዚሁ ውይይታችን፡ ደስ የሚለኝ፡ በፍጹም ግልጽነት የሚካኼድ በመኾኑ ነውና፡ በዚህ ጥያቄያችሁ፡ እንደገና እያደነቅኋችሁ፡ መልሱን፡ በጀመርነው፡ መልክና ይዘት፡ በየራሳችሁ እንድታገኙት አደርጋለሁ። በዚህ መሠረት፡ እናንተም፡ ፈቃዳችሁ ኾኖ፡ ከዚህ ጋር ለተያያዘ እውነታ፡ ለማቀርብላችሁ፡ ግልጽና ቀላል ጥያቄ፡ በቅድሚያ መልስ ትሰጡኛላችሁ። ጥያቄው፡ እንዲህ የሚል ነው። "ከእናንተ፡ ከእየራሳችሁ እና ከወለዷችሁ እናቶቻችሁ፡" ወይም፡ በሌላ አቀራረብ፡ "ከእናትና ከልጅ፡ የሚበልጠው፥ የሚቀድመውም ማነው?"

*መልስ፡-* *ኹለቱም ወጣቶች፡ እርስ በርሳቸው እየተያዩ፡ ዝም አሉ።*

ጥያቄ፡- መልሱን ስጡኝ እንጂ፡ እየጠበቅሁ ነኝ እኮ!

*መልስ፡-* አኹንም፡ ዝም ብለው፡ አፍ አፋቸውን በእጃቸው ይዘው፡ እየተገላመጡ መተያየታቸውን ቀጠሉ።

ጥያቄ፡- አኹንም፡ የጠበቅሁትን ምላሽ፡ ከኹለቱም ላገኝ ስላልቻልሁ፡ ለሦስተኛ ጊዜ፡ **ምነው?** **መልሱ**፡ እንኳንስ ለእናንተ፡ በዚህ፡ የሥልጣኔ ዘመን ለተፈጠራችሁትና ብዙ ነገር ለምታውቁ ወጣቶች ይቅርና፡ ለማንም፡ ያልተማረ ሰው እንኳ ቢኾን፡ የተፈጥሮና የተለመደ ተራ ነገር በመኾኑ፡ ቀላልና ግልጽ ስለኾነ፡ ምንም ዓይነት ችግር ያለበት አይደለም። ታዲያ! መልሱን ወዲያው ለመስጠት፡ ለእናንተ የከበዳችሁና ያስቸገራችሁ ከቶ ምንድርነው?

**መልስ:-** በመጨረሻ: ትንፋሹ ታፍኖ እንደተለቀቀና እንደበቱ ታሥሮ እንደተፈታ ሰው: በኃይለ ቃል: *"እናት ናት: የምትቀድመው! የምትበልጠውም!"* የሚለውን: የጠበቅሁትን መልስ ሰጡ::

**ጥያቄ:-** *አያችሁ!* በመጀመሪያ: ለዚህ ጥያቄዬ: መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁት: በሥጋዊው አእምሮአችሁ ስለነበረ: ሥጋዊው አእምሮአችሁ ደግሞ: ለሓሰት አገልግሎት የተጋለጠና የተመቸ ስለኾነ: እውነተኛው መልስ: የኋላ ኋላ: በእርሱ የሓሰት ፍላጎት ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ: አስቀድሞ በመገንዘቡ: ትክክለኛውን መልስ እያወቀው: ነገር ግን: በቀጥታና ወዲያው ሊሰጥ ስላልፈለገ: እንደበታችሁ: ግልጹንና ቀላሉን መልስ እንዳይሰጥ: እንዴት እንደዘጋው: እየራሳችሁ አስተዋላችሁት አይደለም?

**መልስ:-** *አዎን! ልክ ነህ:: ግን: ይኼን: በውስጣችን የተደበቀውን: የስሜታችንን ምሥጢር እንዴት ልታውቅ ቻልህ? እስኪ: እውነቱን ንገረን?*

**ጥያቄ:-** በመጀመሪያ ነገር: እኔም: እንደእናንተው: ሥጋ ለባሽና ሰብአዊ ፍጡር መኾኔን አትርሱ! ይህም: በእናንተ ውስጥ የሚኖረው አስተሳሰብ: በእኔም ውስጥ አለ ማለት ነው:: ስለዚህ: በውስጣችሁ የተደበቀው የስሜታችሁ ምሥጢር: ለእናንተ: መስሏችሁ ይኾናል እንጂ: በእኔም ዘንድ ስላለ: ለእኔ ምሥጢር ሊኾን አይችልም::

ቀጥሎ: ሓዋርያው: *"ለፍጥረታዊ: ማለትም: ለሥጋዊ ሰው: የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር: ሞኝነት ነውና: አይቀበለውም፤ በመንፈሳዊ ልቦናም የሚመረመር ስለኾነ: ሊያውቀው አይችልም:: መንፈሳዊ ሰው ግን: በመንፈሳዊ ልቦናው: ኹሉን ይመረምራል፤ ራሱ ግን: በማንም አይመረመርም::"* ያለውን ቃል: ማስታወስ ብቻ ሳይኾን: ቀደም አድርጋችሁ ያወቃችሁት አይደለምን?

**መልስ:-** *አዎን! አውቀነዋል::*

**ጥያቄ:-** ይኼን: በውስጣችሁ የተደበቀውን: የስሜታችሁን ምሥጢር ለማወቅ የቻልሁት በመንፈሳዊው መንገድ መኾኑን ተገንዘባችሁት አይደለም?

**መልስ:-** *አዎን!*

**ጥያቄ:-** እንግዲህ: ስለቅድስት ድንግል ማርያም ማንነትና ምንነት ለማወቅ: በመንፈስ ቅዱስ ካልኾነ በቀር: ለዕሩቅ ብእሲ: ማለትም: ለሥጋዊ አእምሮ እንደማይቻለው: ቀደም ብላችሁ ካወቃችሁት ጋር: አኹን ደግሞ: በይበልጥ ተረዳችሁት አይደለም?

**መልስ:-** *አዎን! ተረዳነው::*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

**ጥያቄ:-** እንዲያ ከኾነ: እናት: ከልጁ እንደምትቀድምና እንደምትበልጥ እየታወቀ: መልሱን ወዲያው ከመስጠት የከለከላችሁ: በሥጋችን ሊሠለጥን የሚሞክረውና የሚጥረው: "ሐሰት: የሐሰት አባት" የተባለው: የዲያብሎስ ርኵስ መንፈስ መኾኑን: ነገር ግን: በመጨረሻ: እውነቱን ለመናገር ያስቻላችሁ: ከልባዊው ፈቃደኛነታችሁ የተነሣ: በእናንተ ላይ የሰፈነው: የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ስላሸነፈ መኾኑን ተረዳችሁት አይደለምን?

**መልስ:-** *አዎን! በእርግጥ: ተረድነውእኮ! ይህን: የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የሰጠን ፈጣሪያችን: የተመሰገነ ይኹን!*

**ጥያቄ:** እንግዲህ: ኢየሱስ ክርስቶስ: በአምላክነቱ: እናቱን: ቅድስት ድንግል ማርያምን: የሚቀድማትና የሚበልጣት ሲኾን: እርሷ ደግሞ: በሰውነቱ: እናቱ በመኾኗ: በዚህ እናትነቷ: እንዲህ: የምትቀድመውና የምትበልጠው ስለኾነ: እግዚአብሔር: ክብሩን አዋርዶ: ራሱን ከሰው ደረጃ ጋር በማስተካከሉ: በእርሱ በኩል ያለውን ሚዛን: እንዴት ዝቅ እንዳደረገው: በሌላው ሚዛን በኩል ደግሞ: በፍላጎቱ: በምርጫውና በውሳኔው ፍጹም እውነተኛና ቆራጥ የኾነ: ሰብአዊ ፍጡሩን: ወደምን ዓይነቱ ልዕልና አልቆ: ከፍ እንዳደረገው: የፈጣሪን ቸርነት ተመልከቱት! በዚህ: በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የመገለጥ ምሥጢር: አምላክነትና ሰውነት: ልጅና እናት እንዴት እንደተስተካከሉ አስተውሉት!

ታዲያ! እንዲህ ከኾነ: የውዳሴ ማርያም ደራሲው: ቅዱስ ኤፍሬም: በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ: *"ዘዚአነ ሞተ ነሥአ: ወእንቲአሁ ሕይወተ ወሀበነ: ...ዘእምቅድመ ዓለም ሀልው: ተሰብአ እምኔኪ ብሉየ መዋዕል: ወጽአ እምከርሥኪ: ሥጋነ ነሥአ: ወመንፈሶ ቅዱሰ ወሀበነ:* ***ወረሰየነ ዕሩያነ ምስሌሁ*** *በብዝኀ ኂሩቱ:"* ማለትም: *"የእኛን ሞት: ለእርሱ ተቀብሎ: የእርሱን ሕይወት: ለእኛ የሰጠ! ...ከኹሉ አስቀድሞ የነበረውና ዕድሜ የማይቆጠርለት እርሱ: በማሕፀንሽ: ከእኛ: ሥጋን ነሥቶ: የእርሱን: ቅዱስ መንፈስም ለእኛ ሰጥቶ: ከአንቺ በመወለዱ: በቸርነቱ ብዛት:* ***ከእርሱ ጋር አስተካከለን!"*** እንዳለው: እንኳንስ: የአምላክ እናት: ተራው ሰብአዊው ፍጡር ሳይቀር: እየራሱን ካቢቃ: ከፈጣሪው: ከእግዚአብሔር ጋር መስተካከሉን: እነሆ: እውን ማድረግ አይደለምን? ይህ እውነታስ: *"አምላክ: ሰው ኾነ!* [፻፺] *ሰው: አምላክ ኾነ!"* ከሚለው የመጽሐፍ ቃል ጋር መተባበሩ አይደለምን?

**መልስ:-** *አዎን! ይተባበራል::*

**ጥያቄ:-** በዚህ ምሥጢር: እግዚአብሔር ወልድ: ከዓለም አስቀድሞ: ከእግዚአብሔር አብ: ያለእናት በመወለዱ: በመለኮቱ: "ባለአባት" ኾኖ ከቆየ በኋላ: በመጨረሻው ዘመን ደግሞ: ከድንግል ማርያም: ያለአባት በመወለዱ: በሰውነቱ: "ባለእናት" ኾነ::

# ምዕራፍ ፫፤ ጸሎት።

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

እግዚአብሔር ወልድ፡ እንዲህ፡ አባትና እናት ስላሉት፡ ከፈጣሪ በተገኘ የተፈጥሮ ሥርዓት ደግሞ፡ አባትና እናት፡ በወላጅነታቸው ያላቸው ግዳጅና ኃላፊነት፡ ክብርና መብት እኩል ስለኾነ፡ በዚህ መሠረት፡ ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው፡ በአንዱ ልጃቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት፡ የእግዚአብሔር አብና የድንግል ማርያም የወላጅነት ግዳጅና ኃላፊነት፡ መብትና ክብር፡ በአምላክነትና በሰውነት ባሕርዩ ብቻ፡ ከመበላለጡ በቀር፡ የተስተካከለ እንዲኾን፡ የፈጣሪ ፈቃዱ ኾነ ማለት አይደለምን?

መልስ:- *አዎን!*

ጥያቄ:- ያው ደራሲ፡ እርሱን የመሰለው፡ ሌላውም፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልተው፡ *"ማርያም ድንግል፡ ከብካብ ንጹሕ፡ ወመርዓ ቅዱስ፡ ነጸረ አብ እምሰማይ፡ ወኢረከበ ዘከማኪ፡ ፈነወ ዋሕዶ፡ ወተሰብአ እምኔኪ። ...ጸልዩ፡ ቅድመ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ መርዓተ አብ፡ ወእመ በግዑ! ...ለፍልስትኪ ከብካብ፡ ኀበ ዘሉዓሌ ተድባብ፡ እንዘ ይዌድሰኪ ዘራማ ኪሩብ፡ ንግሥትየ መርዓተ አብ፥ በሰጊድ ሰላም።"* ማለትም፡ *"ማርያም ሆይ! እግዚአብሔር አብ፡ ለንጹሑ ሠርግ፥ ለቅዱሱም ጋብቻ የምትበቃውን ድንግል ሊሻ፡ ከሰማይ ኾኖ፡ ወደምድር ተመለከተ፡ እንደአንቺ ያለች፡ የበቃች ስላላገኘ፡ አንድ ልጁን ወደአንቺ ሰደደው፡ እርሱም፡ ከአንቺ ሰው ኾነ! ...የአብ ሙሽሪት፡ 'የእግዚአብሔር በግ' ለተባለው ልጁም፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ እናት በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ፊት ጸልዩ! ...አንቺ፡ የአብ ሙሽራ ሆይ! በራማ የሚኖሩት፡ የኪሩቤል ነገደ መላእክት እየወደሱሽ፡ የሠርግሽ የልዕልና ዘውድ ወደኾነው ሰማያዊ መንበርሽ ላረግሽበት ትንሣኤሽ በመስገድ፡ 'ሰላም!' እልሻለሁ።"* እንዳለው፡ የጋብቻን ምሥጢር፡ በአዳምና በሔዋን የሠራና የመሠረተው፡ ራሱ እግዚአብሔር አብ፡ ይህን ሥርዓት፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእትና እርሱን በወለደችለት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሰውነት፡ በኹለቱተናው፡ እንደ፡ት አድርጎ ለፍጹምነትና ለዘለዓለማዊነት እንዳበቃው፡ እንደገና፡ በአንክሮ መመልከት ነው።

ሙሽራና ሙሽሪት፡ መጀመሪያ፡ በጋብቻቸው ጊዜ፡ ኋላ፡ በትዳራቸው ጊዜ፥ በመጨረሻም፡ በወላጅነታቸው ጊዜ፡ "ባልና ሚስት" ተብለው በአንድነት ሲኖሩ፡ ኹለቱም፡ ከፈጣሪያቸው ተፈቅዶ በተሰጣቸው መብትና ግዳጅ፥ ኃላፊነትና ክብር፡ የተካከለ የእኩልነት ሚና ያላቸው መኾኑ ይታወቃል፤ እንደዚሁ ኹሉ፡ በእግዚአብሔር አብና ኹለንተናዋን፡ በፍጹም ንጽሕና፡ ለልጁ እናትነት አብቅታ በተገኘችው፡ በድንግል ማርያም መካከል፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር የተፈጸመው፡ ይህ፡ የመለኮትና የትስብእት አንድነት፡ አምላክነትና ሰውነት፡ ማለትም፡ የሙሽራውን ወገን በያዘው፡ በእግዚአብሔር አብ በኩል ያለው ሚዛንና የሙሽሪትን ወገን በያዘችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም በኩል ያለው ሚዛን፡ መተካከላቸውን አረጋግጦ ያሳያል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ታዲያ! እግዚአብሔር፡ ከራሱ አንቅቶና ቀድሶ የሠራውን፡ በአዳምና ሔዋንም የመሠረተውን፡ በደጋጎቹ ልጆቻቸው ኢትዮጵያውያን ዘንድ አስጠብቆ ያቆየውንና በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት፡ በሰውነት ተገኝቶ የባረከውን የጋብቻን ሥርዓት፡ በዚህ ድንቅ የኾነ፡ የቸርነት ድርጊቱ፡ እንዴት አድርጎ አጽንቶ፡ ከምድራዊነት፡ ወደሰማያዊነት፡ ከሥጋዊነት፡ ወደመንፈሳዊነት፡ ከጊዜያዊነት፡ ወደዘለዓለማዊነት፡ በአጠቃላይ፡ ከሰብአዊነት፡ ወደአምላካዊነት እንዳሸጋገረው፡ ለፍጹምነትም እንዳበቃው፡ አስተዋላችሁት አይደለም?

መልስ:- *አዎን!*

ጥያቄ:- እንግዲህ፡ በዚህ ኹሉ ምክንያት፡ "ፈጣሪያችንን፡ *'አባታችን እግዚአብሔር ሆይ!'* ብለን በጠራንበት አንደበታችን፡ እርሷን፡ ፍጡርዋንም፡ *'እናታችን ማርያም ሆይ?'* ብለን ልንጠራት የሚቻለንና የሚገባን ኾነ ማለት አይደለምን?

መልስ:- *አዎን! እውነቱና ትክክሉ፡ እርግጡና ገሃዱ፡ ይኼ ኾኖ ሳለ፡ "በረ ማርያም" የሚባሉት ወገኖች፡ "እግዚአብሔር፡ ድንግል ማርያምን የፈጠረው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድትወልድ ብቻ ነው፡ እርሱን የመውለድ አገልግሎቷንም ስለፈጸመች፡ ከዚያ በኋላ የማታስፈልግ ኾናለች፡" ብለው ሊናገሩ የደፈሩት፡ እንዴት ነው? እንዴትስ፡ እንዲህ ሊያምኑ ቻሉ?*

ጥያቄ:- መልካም! ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ ይኾናችሁ ዘንድ፡ እኔም፡ ወደቀደመው ጥያቄዬ ተመልሼ፡ በዚያው መል[illegible] እጠይቃችኋለሁ:: እናንተን የወለዱት እናቶቻችሁ፡ የተፈጠሩት፡ ለእየራሳቸው ህልውና ሳይኾን፡ እናንተን የመውለድና የማሳደግ አገልግሎትን ለ[illegible] ብቻ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ታምናላችሁም? ራሳችሁን በቻላችሁበትስ ጊዜና ከዚያ በኋላ፡ እየንዳንዳችሁ፡ እናቶቻችሁን፡ "እናቴ! እንግዲህ፡ እኔን ፀንሰሽ የመውለድና አጥብተሽ የማሳደግ አገልግሎትሽን ግዳጅ ፈጽመሻልና፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ አታስፈልጊኝምና፡ ኺጂ! አሰናብቼሻለሁ!" ብላችሁ፡ የእነርሱን እናትነት፡ የእናንተንም ልጅነት ትሽራላችሁ ማለት ነውን?

መልስ:- በዚህ ጥያቄዬ፡ ኹለቱም ወጣቶች፡ በየገጻቸው ላይ፡ ከፍተኛ የንዴትና የኀዘን ስሜት እየታየባቸው፡ *"ይህ ነገር፡ ሊጠየቅ ቀርቶ፡ ሊታሰብም እንኳ አይገባም!"* አሉ፡ በቊጣ ቃል::

ጥያቄ:- በእናቶቻችሁ ላይ፡ በቀላል ጥያቄ መልክ የተቃጣው፡ ይህ ነገር፡ እናንተን እንኳ፡ በዚች አጭር አፍታ ውስጥ፡ እንዴት፡ እንዲህ፡ ሊያስቆጣችሁና ሊያሳዝናችሁ እንደቻለ፡ እስኪ ተመልከቱት!

## ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት::
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ::

*"ሰውን: ወንድና ሴት አድርጎ: እኩል: በመልኩ ፈጠረ!"* በተባለለት: ለፈጠረውም ለዚሁ ሰው: *"እናትህንና አባትህን አክብር!"* የሚል ትእዛዝን በሰጠው: በፈጣሪ እናት ላይ: ይህን የመሰለው አስተሳሰብ: ከጥያቄነት አልፎ: ሃይማኖት እስከመኾን ከደረሰ: ይህ ነገር: ራሱን: ኢየሱስ ክርስቶስን: በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመውን: ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን: ይልቁንም: በእርሷ: በቅድስት ድንግል ማርያም: በኤልሣቤጥና ገና በማሕፀኗ በነበረው: በልጇ: በመጥምቁ ዮሐንስ ላይ ሳይቀር አድሮ ያወደሳትን: እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን: የቱን ያህል ያሳዝን? ያስቈጣስ? ይህን የመሰለው ሃይማኖትስ: ግብሩን በትክክል የሚገልጸው ስሙ እንደሚያመለክተው: ከማን የተገኘ ለመኾኑ: በራሱ መስክረ ማለት አይደለምን?

መልስ:- ኹለቱም ወጣቶች: አኹንም: በዚያው: የቀድሞና የንጹሕ ስሜታቸው እንዲሁ: "ከባዕዱ መንፈስ እንጂ: ከመንፈስ ቅዱስማ: ይህ: እንዴት ሊገኝ ይቻላል? አይቻልም::" አሉ::

ጥያቄ:- ለነገሩማ: እውነታው: ሔዋን የተገኘችው: አዳም: አስቀድሞ ተፈጥሮ አይደለምን? እንዲያውም: እኛ: ኢትዮጵያውያን በሃይማኖታችን አምነን የምንለው: "አዳምና ሔዋን: እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደች ድንግል ማርያምን ለማስገኘት ተፈጠሩ!" ነው:: ደግሞስ: ወንጌላዊው: *"መቼም ቢኾን: እግዚአብሔርን ያየው: አንድ ስንኳ የለም: በአባቱ ዕቅፍ ያለ: አንድ ልጁ: እርሱ ተረከው!"* ብሎ እንደጻፈውና ራሱም: *"እኔን ያየ: አብን አየ!"* ብሎ እንደተናገረው: እግዚአብሔርን ያወቅነውና ያየነው: በኢየሱስ ክርስቶስ ሲኾን: ኢየሱስ ክርስቶስንስ ያወቅነው: ያገኘነውና ያየነው: በቅድስት ድንግል ማርያም አይደለምን? ታዲያ: እንዲህ ከኾነ: ይህ የእግዚአብሔር ድንቅ ድርጊት: ወደምን ዓይነቱ እውነታ ይመራናል? ራሱ ባለቤቱ: ኢየሱስ ክርስቶስ: *"በእኔ ካልኾነ በቀር: ወደአብ የሚመጣ የለም!"* ሲል እንደተናገረው: ማንኛውም ፍጡር: እርሷን: ማለትም: እናቱን: ቅድስት ድንግል ማርያምን አስቀድሞ ሳያውቅና በእናትነቷ ሳያምን: እንደምን: ወደኢየሱስ ክርስቶስ: መቅረብና መድረስ ይቻለዋል? አይቻለውም::

መልስ:- አዎን ነው::

ጥያቄ:- እንዲያው ለመኾኑ: እንኳንስ እግዚአብሔርን የወለደች እናትን ይቅርና: እስኪ: ቀደም ብለን ባወሳነው አስተሳሰብ መሠረት: የየራሳችሁን እናቶች ንቆና አዋርዶ፥ ጠልቶም: "እናንተን እወድዳለሁ፤ አከብራለሁ!" የሚል ቢኖር: "እውነት ነው!" ብላችሁ ትቀበሉታላችሁ?

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*መልስ:- መቀበሉ ቀርቶ፡ አኹን፡ ነገሩን መስማቱ እንኳ ከብዶብናልና፡ እባክህ፡ ፈቃድህ ኾኖ፡ ጥያቄያችንን፡ በዚሁ አብቅቶ ብትዘጋው!*

ጥያቄ:- በዚህ ውይይታችን ላይማ፡ ከሃይማኖታዊው ቅንዓት የተነሣ፡ በውስጣችን፡ አልፎ አልፎ መነሣሣቱ የማይቀረው፡ ስሜታዊ ሁከት እንዳያጥለቀልቀን፡ እየራሳችንን መቆጣጠርና ማስከን ይገባናል፡ አለዚያ፡ የምንፈልገው ቍም ነገር ኹሉ ሊያመልጠን ይችላል:: ስለዚህ፡ ጥያቄያችሁ፡ ተሟጥጦ እስኪያልቅ ድረስ የምንቀጥልበት እንጂ፡ ተቋርጦ የሚዘጋበት ምክንያት ከቶ አይኖርም:: አኹንም፡ ውይይታችንን፡ በጀመርነውና እዚህ ባደረስነው አያያዝ ልንቀጥለው ያስፈልገናል፡ በዚህ ርእስ ላይ፡ ልትዘጉት የሞከራችሁትንም የእውቀት በር፡ እንደገና ክፈቱት! አሳባችሁንም፡ በፍጹም ነጻነት ከመግለጽ ወደኋላ አትበሉ! ይህን ቀና አካኼድ፡ አስቀድማችሁ ልታውቁትና ልትዘጋጁበት፡ ወደፊትም፡ ልትከተሉት የሚያስፈልጋችሁ ግዳጅ ሊኾን ይገባል::

መልስ:- ስለመልካሙ ምክርህ! እግዜር ይስጥልን! ይኸው ምክርህ፡ የጠቀመን፡ ይህን፡ የአኹኑን ድክመታችንን ለማስወገድ ብቻ አይደለም፡ ወደፊት ለሚያጋጥመን፡ ለማናቸውም ዓይነት ተመሳሳይ ችግር ኹሉ፡ በመፍትሔነት የሚጠቅመንና የምንመራበት ይኾናል እንጂ::

እንግዲህ፡ ለመዝጋት የሞከርነውን ጉዳይ እንድንከፍተው ከፈቀድህልን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ስለሚሠነዘረው ትችት፡ በተጨማሪ የምታብራራልን የተያያዘ ነጥብ አለ፤ ይኸውም፡ እነዚያው "ዐረ ማርያም" የሚባሉት ወገኖች፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "የሱስ ጌታ" የሚለውን ስም ሰጥተው፡ የቅድስት እናቱን ስም ሳያነሡ፡ ከእርሷ በወረሰው ሰውነቱ የኾነውንና ያደረገውንም ሳይገልጹ፡ በአምላክነቱ በኩል ያለውን ብቻ የሚናገሩት ለምንድር ነው?" በሚለው ጥያቄ ላይ የተመሠረተው ነው::

መልስ:- እነዚያ ወገኖች፡ ይህን ድርጊት የሚፈጽሙት ኾን ብለው፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር ለማሳነስ ሲሉ ነው:: ምክንያቱ ለምን ይመስላችኋል? ዲያብሎስ፡ የክርስቶስን የመስቀል ምልክት የቱን ያህል እንደሚፈራውና እንደሚጠላው ታውቃላችሁ፤ ከዚያ ይልቅ፡ ይበልጥ የሚፈራውና የሚጠላው ነገር ቢኖር፡ የድንግል ማርያም፡ ስም አጠራርዋን በመኾኑ ነው:: ደግሞስ፡ አጋንንትና እነዚህ፡ የእርሱ ጭፍሮች የኾኑት ልቡሳነ ሥጋ፡ ኾን ብለው፡ ደካማውን ሰብአዊ ፍጡር ማርከው፥ ወይም፡ አጥምደው፡ ሥጋዊ አእምሮውን፡ በ"ሱስ" ኃይል ዐሥረው በሚይዙበት፡ አፍዝ አደንግዝ የዕፀዋት ቅጠላ ቅጠላቸው አደንዝዘው፡ እንዴት የእነርሱ ማደሪያና ባሪያ እንደሚያደርጉት ታውቃላችሁ?' ለጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "የ'ሱስ' ጌታ" የሚለውን ስም ሰጥተው በሚያሰሙት የሐሰት ስብከታቸው አይደለምን?

# ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት።

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሐተታ።

ስለዚህ፡ እነዚህ ወገኖች፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም የማያነሡት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፡ ከድንግል ማርያም በወረሰው ሰውነቱ የኾነውንና ያደረገውን ሳይገልጹ፡ በአምላክነቱ በኹል ያለውን ብቻ የሚናገሩት በዚህ ምክንያት መኾኑን ልታውቁት ይገባል።

ቅድስት ድንግል ማርያምን በሚመለከት፡ የዲያብሎስንና የሎፍሮቹን ሐሳዊና ጽልመታዊ ሙከራና ድርጊት እዚህ ላይ እናቁመውና፡ የእግዚአብሔር የኾነውን፡ አማናዊውንና ብርሃናዊውን ሥራ እንመርምር! ይህንም፡ እንዲህ፡ በሚል መጠይቃዊ ቃል፡ ለእናንተው በማቅረብ፡ እጀምረዋለሁ፡- "ለመኾኑ፡ እግዚአብሔር፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ለሰውና ለፍጥረተ ዓለሙ ያደረገውን ቤዛነት፡ ሰው ሳይኾን፡ በዚያው በእግዚአብሔርነቱ ባሕርይ ብቻ ኹኖ ማድረግ ያቅተው ነበርን?

*መልስ፡- እንዴት ያቅተዋል?! ይቻለዋል እንጂ። የነገርኹን፡ "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም!" የሚለው፡ የሊቀ መላእክቱ ቃል፡ የጸና አይደለምእንዴ!? ፍጹምነትን፡ ከምንም ያስገኘ፡ ድንግልን፡ ያለወንድ ዘር፡ በድንግልና እንድትወልድ ያደረገ፡ ሞቶ የበሰበሰውን፡ በሕያውነት ያስነሣ፡ ሌላውንስ ኹሉ ማድረግ እንዴት ይሳነዋል? አይሳነውም።*

ጥያቄ፡- አዎን! እንግዴህ፡ እንዲህ፡ ኹሉን ማድረግ ሲቻለው፡ ሥራውን፡ በእግዚአብሔርነቱ ብቻ ከመወሰን ይልቅ፡ ሰው ኾኖ፡ በሰው ሥርዓት፡ ኹሉን ነገር፡ በሰውነት ለመፈጸም ፈቀደ። በእግዚአብሔርነቱ፡ ፈጣሪ፤ ወልደ አብ ዋሕድ፤ አካላዊ ቃል፤ የአማልክት አምላክ፥ የገዢዎች ገዢ፥ የንጉሦች ንጉሥና በባሕርየ መለኮቱ፡ መሥዋዕት ተቀባይ ሲኾን፡ በሰውነቱ፡ የሰው ልጅ፤ ሊቀ ካህናት፥ መልከ ጼዴቅ፤ ንጉሠ ሳሌምና ራሱን ለመሥዋዕትነት ያቀረበ የእግዚአብሔር በግ መባልን መረጠ ማለት ነው። "ወልደ አብ"፥ ወይም፡ "የአብ ልጅ" ብቻ ከመባል፡ "ወልደ ማርያም"፡ ወይም፡ "የማርያም ልጅ" መባልን መረጠ። "ኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለው ስም፡ ይህንኑ ያረጋግጣል።

ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ ረቂቅ ህልውናውንና መለኮታዊ መንግሥቱን፡ በመንፈሳዊ ቅርጹና መልኩ ብቻ እንዲቀጥል ማድረግ ሲቻለው፡ ከዚህ ይልቅ፡ እርሱ አዘጋጅቶ ወደሠራው፡ ወደሰውኛው ሥርዓት፡ በግዝፈት ተለውጦ እንዲካኼድ መምረጡን፡ እንዲህ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ያለወንድ ዘር፡ ሰው ኾኖ ተፀንሶ ለመወለድ የመፈለጉ ምሥጢርና ከዚህ ጋር በተከታታይ የተከናወኑት ድርጊቶቹ ኹሉ ያመለክቱናል፤ ይህም ማለት፡ -በተለይ፡ በተንሣንበትና በምንወያይበት ዓላማ ስንወሰን- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእናቱ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ባለው ፍቅርና በሰጣት ክብር፡ ፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ በዚሁ በሰው ሥርዓት፡ በአምላክ እናትነቷ እንዲቀበላት፡ ፈቃዱ መኾኑንና በእርሱም በኹል፡ በዚሁ መሠረት እንዲፈጸም ማድረጉን፡ በቀላሉ እንመለከታለን።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! በቃና ዘገሊላ የሠርግ ቤት ተገኝቶ፡ የተናገረውን፡ የእግዚአብሔርነቱን ፈቃድ ከማስፈጸም ይልቅ፡ ለእናትነቷ ፈቃድ 'መንበርከክን መምረጡ አይደለምን? በዚህስ፡ "*አባትህንና እናትህን አክብር!*" የሚለውን ትእዛዙን፡ ራሱ፡ በይፋ፡ በተግባር ላይ ዐውሎ መፈጸሙን፡ ለዚሁ፡ እርሱ ለሠራው፡ የሰው ሥርዓት፡ ያለውን ፍጹም ፈቃደኛነት፡ ታዛዥነትና ታማኝነት፡ ለፍጥረቱ፡ በአደባባይ ማሳየቱ አይደለምን? እኛም የሰው ልጆች፡ ይህን እውነታ አስተውለን እንድንመለከተውና እንድንፈጽመው ሊያሳስበን አይደለምን?

መልስ:- *እንዴታ! አዎን! በሚገባ ማሳየቱ ነው እንጂ::*

ጥያቄ:- ይህ፡ "*አባትህንና እናትህን አክብር!*" የሚለው አምላካዊ ትእዛዝ፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ እንዲህ፡ "በፍጹም ፈቃደኛነት፡ ታዛዥነትና ታማኝነት ተፈጸመ!" ሲባል፡ እርሷ፡ እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ በሰውነቷ፡ ለእርሱ፡ ለመለኮታዊው ፈጣሪዋ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእግዚአብሔርነቱ እንደታዘዘችለት ኹሉ፡ እርሱም፡ ለእርሷ፡ ለሰብአዊት እናቱ፡ ለድንግል ማርያም፡ በሰውነቱ የታዘዘ ለመኾኑ ማረጋገጫ አይደለምን?

መልስ:- *አዎን! ነው::*

ጥያቄ:- በሰውኛ ሥርዓት፡ ወይም፡ ወግና ልማድ ማለት፡ ምን እንደኾነ፡ ለእናንተ ማስረዳት የሚያስፈልገኝ አልመሰለኝም፤ ምናልባት ካስፈለገኝ ግን፡ እስኪ፡ በራሴ የደረሰውን፡ ምሳሌ አድርጌ ላውጋችሁ!

ከሕፃንነቴ ጀምሮ፡ ምን እንዳስመለከተኝ ባላውቀውም፡ በቤተ ሕዝቡ፡ ያገር ሽማግሌ፡ በቤተ ክህነቱም፡ ቄስ፡ በቤተ ምልክናውም፡ ዳኛ የኾነው፡ የሥጋ ወላጅ አባቴ፡ ከምክር፣ ከተግሣፅና ከማስጠንቀቂያ ቀጥሎ፡ በሌሎቹ ታላላቅ ወንድሞቼ ላይ የሚፈጽመውን የቍንጢጥ ቅጣት እያየሁ፡ እኔንም፡ ያን የመሰለው ጽዋ "ይደርስብኛል!" ብዬ፡ በሕፃንነት አእምሮዬ በምጠራጠርበት ጊዜያት ኹሉ፡ ራሴን፡ ከዚያ ቅጣት ለማዳን፡ የማካኼደው ልማድ ነበረኝ፤ ያም ልማድ፡ ከሚያንገዋብበው ቅጣት፡ ለእርሱ፡ ሚስቱ የኾነችው፡ የወለደችኝ እናቴ እንኳ፡ ልታስጥለኝ እንደማትችል በመገንዘብ፡ መኖሪያቸው፡ ከእኛ፡ ጥቂት ራቅ ወዳለው፡ ወደአያቶቼ ቤት ሮጬ በመኼድ፡ ወንድ አያቴን ሳይኾን፡ ሴት አያቴን፤ ማለትም፡ የአባቴን ወላጅ እናት፡ "ሙጥኝ!" ብዬ የምማጸንበት አድራጎቴ ነበር:: እናቴ፡ ይህንኑ ዘዴዬን ስለምታውቅ፡ አያቴን ለመማጠን፡ ወደእርሳቸው መኼዴን፡ አባቴ፡ ማታ፡ ከሥራው በሚመለስበት ጊዜ ስትነግረው፡ ቢመሽም እንኳ፡ ወደአያቴ ቤት መምጣቱ ስለማይቀር፡ ምሕረት እንዲያደርግልኝ፡ ከእናቱ፡ በቀጥታ የሚቀርብለትን ጥያቄ፡ በፍጹም ፈቃደኛነትና ታዛዥነት ተቀብሎ፥ ጕልበታቸውንም ስሞ፥ ተመርቆና ተስሞ ከተሰናበተ በኋላ፡ እኔን፡ በይቅርታ ፍቅር አቅፎ ወደቤቱ ይመለስ ነበር::

# ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት::

## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሓተታ::

ይህን የመሰለው ኹኔታ የሚደርሰው አልፎ አልፎ ቢኾንም: ለእኔ ሲበጀኝ: አባቴን ግን: ለካ አላስደሰተውም ኖሮአል፡ እንዲያውም: የሚያስቆጣው እየኾነ ኼዶ ኖሮአል፡ ምክንያቱም: እርሱ: በእኔ ላይ ሊፈጽም ካቆተመብኝ ቅጣት ኹሉ: በዚህ ዘዴዬ እየተጠቀምሁ አመልጠው ስለነበረ ነው:: አንድ ቀን: ይህን የመሰለው ችግር ደርሶ: እኔም: እንደተለመደው: አያቴን "ያስጥሉኝ!" ብዬ: ወደእርሳቸው ኼጄ: ባጠገባቸው ባለሁበት ጊዜ: አባቴ: ያለወትሮው ሳይመጣ ቀረና: እዚያው: ከአያቴ ጋር አደርሁ፡ በማግሥቱም: እንዲሁ ኾነና: እዚያው ዋልሁ፡ አደርሁ፡ ለካ አባቴ: በእኔ አድራጎት: በጣም ተበሳጭቶ ኖሮአል፡ በሦስተኛውም ቀን: አባቴ የማይመጣ መኾኑን: አያቴ ሲያረጋግጡ: ከሥራው እንደሚገባ ባረጋገጡበት የምሽቱ ሰዓት: ተነሥተውና እኔን ይዘው: ወደአባቴ ቤት ኼዱ፡ ከወላጆቼ ቤት ሊደርሱ ሲቃረቡ: አባቴ: ተነግሮት ይኹን: አይኹን: አላውቅም: ወደእርሳቸው ሲመጣ: እመንገድ ተገናኘን::

እንደተለመደው: ጎንበስ ብሎ: የእናቱን ጉልበት ስሞ ቀና ሲል: በምሽቱ ድንግዝግዝ ውስጥ: እኔን: ከአያቴ ኋላ ራቅ ብዬ ቆሜ አየኝ፡ በጣም ተናዶብኝ ኖሮ: አያቴ የማያዩት መስሎት: ወደኋላቸው ዘወር ብሎ: የያዘውን ረዥም መቋምያ ወደእኔ አግጣጫ ሲሠነዝር: የመመርኰዣው ብረት ጫፍ ክንዴ ላይ ዐረፈ:: ለካ: ይህን የአባቴን ድርጊት: አያቴ: አይተው ኖሮ: በቍጣ: "ኧ!" ብለው ጮኹበት፡ ወዲያው: "በል ና!" ብለው: እኔን: እጄን አፈፍ አድርገው ያዙና: ወደቤታቸው ምልስ አሉ:: በፍጥነት እየተራመዱ ሣሉ: አባቴ: "እማማዬ! እማማዬ!" እያለ ቢለማመጣቸው: "ልጄን እንግዲህ አታገኘውም! ምን አደከመህ? ይልቅስ: ወደቤትህ ተመለስ! ፊቴንም: እንግዲህ ወዲህ እንዳታይ! በቃ!" ብለውት: ያለሌላ ቃል: እቤታቸው ገቡ:: አባቴም: ተደናግጦ: ይቅር እንዲሉት: ወንድ አያቴን ሽምግልና ይዞ ቢወድቅ ቢነሣ: ይልቁንም: የሴት አያቴ ቍጣ እየነደደ ኼዶ: ሌላ: የባሰ ነገር ሊከተል የተቃረበ መኾኑን ሲያይ ተሰናብቶ: ባዶ እጁን: ወደቤቱ ተመለሰ::

በሚያከብራቸው፥ በሚወድዳቸውና በሚፈራቸው እናቱ ላይ በፈጸመው በደል: አባቴ: እጅግ አዝኖና ተጸጽቶ: ከአንድ ሳምንት በላይ እየተመላለሰ: ደጅ ሲጠናና አማላጅ ይዞ: ሲለምናቸው ቆየ፡ በመጨረሻ: ይቅር ብለውት: ለወደፊቱ: በእኔም ላይ ኾነ: እናትነታቸውን በተማጸነ በሌላ ሰው ላይ: ይህን የመሰለውን ድፍረት ላይፈጽም: ቃል ገብቶላቸው: እኔን በፍቅርና በክብር ተረክቦ: ወደቤቱ መልሶ ሊወስደኝ በቃ::

አባቴ ስለሚወድደኝ: በቀጥታ: "ይቅር በለኝ!" ብዬ በእግሩ ላይ ብወድቅ: ወይም: በእናቴ ሽምግልና እንዲታረቀኝ ማድረግ የሚቀልለኝና የሚቀርበኝ፡ የሚቻለኝም ሲኾን: እኔ: በዚያ: በሕፃንነት ዕድሜዬ: ለምን: ወደአባቴ እናት እየኼድሁ መማጠንን መረጥሁ? እንግዴህ: "የሰውኛ ሥርዓት" የሚባለው ይኼ ነው::

እግዚአብሔርም፡ ከሰብአዊ ፍጡሩ ጋር ያለውን ግንኙነቱን፡ በኪዳነ ልቦና፡ በተለይም፡ በኪዳነ ኦሪቱ ዘመን እንደነበረው፡ በሚያስፈራው መለኮታዊ ግርማውና ሥልጣኑ መቀጠሉን አልፈቀደውም፤ ያ ቀርቶ፡ በዚያ ምትክ፡ ለዘለዓለም ጸንቶ እንዲካኼድ የወደደው፡ የፈለገውና የመረጠው፡ እንዲህ፡ ከድንግል፡ በሰውነት ተወልዶ፡ በሰውኛው ሥርዓት መኾኑን፡ ይኸው፡ በሚያስተማምን እውነታ አረጋገጥን ማለት አይደለምን?

መልስ:- አዎን! እያንዳንዳችን፡ በየውስጣችን እንደሚሰማን፡ እውነቱና እርግጡ ይኸው ነው።

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ ረገድ፡ ለዚህ ጸጋ ያበቃችን እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አምነን፡ በጸሎት የምናቀርብላት ሰላምታ፡ *“እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ 'ሰላም!' እንልሻለን። በአሳብሽ ድንግል ነሽ፡ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ ላንቺ ይገባል።”* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል።*

ጥያቄ:- አዳምና ሔዋን፡ በገነት ሣሉ፡ ትእዛዙን ባፈረሱ ጊዜ፡ ይህ፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት ሥራቸው፡ በእነርሱና በእባቡ ዲያብሎስ ላይ፡ ስላስከተለው እርግማን፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ያሰማቸውን ቃል ታስታውሱታላችሁ። *“እግዚአብሔር አምላክም፡ እባቡን አለው፤ 'ይህን ስላደረግህ፡ ...በአንተና በሴቲቱ መካከል፡ በዘርህና በዘርዋ መካከል፡ ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ፡ ራስህን ይቀጠቅጣል፡ አንተም፡ ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።”* በሚለው በዚያ ቃል ውስጥ፡ “ሴቲቱ”፡ ድንግል ማርያምን፥ “ዘርዋ”፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክት መኾኑን አስተውላችሁታል።

ደግሞም፡ *“አዳምም፡ ለሚስቱ፡ 'ሔዋን' ብሎ፡ ስም አወጣ፡ የሕያዋን ኹሉ እናት ናትና።”* የሚለው እውነተኛው የስሙ ትርጓሜ የተገኘው፡ ለዘለዓለማዊው ሕይወት ምክንያት በኾነችው፡ በድንግል ማርያም እንጂ፡ ለሥጋና ለነፍስ ሞት ምክንያት በኾነችው፡ በቀደመችው ሔዋን አለመኾኑ፡ በኹለቱም፡ “ሔዋኖች” የሃይማኖትና የምግባር ፍሬዎች ተገልጦ ታይቷል።[፻፵፯]

ከዚህ የተነሣ፡ ድንግል ማርያምን በሚመለከት የሚነገር፡ ማናቸውም ዓይነት የሰላምታ፥ ወይም የውዳሴ ቃል፡ በተለይ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ይህን እውነታ፡ ማለትም፡ ቅድስቲቱ ሔዋን፡ እርሷ መኾኗን፥ ቅዱሱ አዳምም፡ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፡ በግልጽ የሚያንጸባርቅ ኾኖ ሊቀርብ የሚገባ አይደለምን?

## ምዕራፍ ፭፤ ጸሎት።
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሓተታ።

---

**መልስ፡-** *አዎን! የሚገባ ነው።*

**ጥያቄ፡-** ከኹሉም በላይ፡ እግዚአብሔር፡ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ፡ በገነት ባኖራቸው ጊዜ፡ የአንደኛውን ፍሬ መርጠው ይበሉ ዘንድ፡ ከተከለላቸው፡ ኹለት ዛፎች መካከል፡ ህልውናቸውን፡ በዘለዓለም ሕይወት ለመቀጠል ይችሉ ዘንድ፥ እንዲበሉ የፈቀደውን የሕይወት ዛፍ ትተው፡ እንዳይበሉ ያሳሰባቸውንና የሰውን ዘር በሙሉ፡ ለሞት የዳረገውን፡ የአንደኛውን ዛፍ ፍሬ፡ ሔዋን በመብላቷ፡ እርሷ፡ የክፉዋ ዛፍ ምሳሌ አልኾነችምን?

**መልስ፡-** *አዎን! ኾናለች።*

**ጥያቄ፡-** በእርሷ አንጻር ደግሞ፡ ራሱን ለሞት የዳረገው፡ ይኸው የሰው ዘር፡ እያንዳንዱ፡ በፍላጎቱ፡ ከእርሱ በልቶ፡ ከሞት ይድንበት ዘንድ፥ በትንሣኤ ክብርና ደስታም፡ ለዘለዓለም ይኖርበት ዘንድ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም ያስገኘች፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስለኾነች፡ እርሷ፡ ያች የሕይወት ዛፍ፥ አማናዊቷና ዘለዓለማዊቷ ሔዋንም መኾኗ አይደለምን?

**መልስ፡-** *አዎን! በእርግጥ፡ እርሷ ናት።*

**ጥያቄ፡-** ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ ረገድ፡ ለዚህ ጸጋ ያበቃችን እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አምነን፡ በጸሎት የምናቀርብላት ሰላምታ፡ *"ማኅጸንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ።"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

**መልስ፡-** *አዎን! ይገባል።*

**ጥያቄ፡-** ይህን ጸሎት የምንጸልይ፡ እኛ፡ ኢትዮጵያውያን፥ ወይም፡ ኢትዮጵያዊነትን የተቀበለ ሰው ብቻ መኾኑን እንዳትዘነጉት ያስፈልጋል። "ኢትዮጵያ"፡ ድንግል ማርያም ስለመኾኗም፡ በዝርዝር ሓተታ ስለተነጋገርንበት፡ እርግጠኝነቱን፡ በሚበቃ አውቃችኋል። እንዲያ ከኾነ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በመጽሓፍ ውስጥ፡ ስለኢትዮጵያ የተነገረውን ኹሉ፡ በጸሎታቸው ሊያወሱ አይገባቸውምን?

**መልስ፡-** *አዎን! ይገባቸዋል።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ ረገድ፡ ለዚህ ጸጋ ያበቃችን እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አምነን፡ በጸሎት የምናቀርብላት ሰላምታ፡ *"ቀድሞ በነቢዩት፡ 'ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የተባልሽ፡ እኛም፡ 'እምነ ጽዮን' ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ::"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል::*

ጥያቄ:- የቀደሙት ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ለተፈጸሙበትና ለዘለዓለማዊነት ህልውና ለበቁበት፡ ለሰባተኛው የምሕረት ቃል ኪዳን፡ የመጨረሻው ማኅተም የኾነውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ያስገኘች በመኾኗ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት የሰላምታ ጸሎት፡ ይህን እውነታ የሚያንጸባርቅ ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል::*

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ ረገድ፡ ለዚህ ጸጋ ያበቃችን እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አምነን፡ በጸሎት የምናቀርብላት ሰላምታ፡ *"እግዚአብሔር አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳኑ ምሕረቱን ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ 'ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ' እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን::"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል::*

ጥያቄ:- ኢትዮጵያውያን፡ ስለድንግል ማርያም፡ በሚያስቡበት ጊዜ ኹሉ፡ ከእርሷ ጋር ያላቸው ግንኙነት፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፥ የዚያም ግንኙነታቸው መጠን፡ የቱን ያህል ቅርበትና ጽናት እንዳለው፡ ለአንዲት አፍታ እንኳ ሳያቋርጡ፡ በጠለቀ ስሜት የሚመሰጡበት፡ ታላቅ የአደራ ቃል መኖሩን፡ ያም የአደራ ቃል፡ በማንና እንዴት፥ ደግሞም፡ የት እንደተነገረ አውቃችኋል፤ እርሱም፡ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ ሣለ፡ ነፍሱ ከሥጋው ከመለየቷ በፊት፡ ለቅድስት እናቱና ለሚወድደው ደቀ መዝሙሩ የተናዘዘው፡ *"እነሆ ልጅሽ! እነሆ እናትህ!"* የሚለው የመጨረሻ ቃል ነው::

ታዲያ! ኢትዮጵያውያን፡ *"እናታችን!"* ለሚሏት ድንግል ማርያም፡ በጸሎት በሚያቀርቡት ሰላምታቸው ጊዜ፡ ይህን የመሰለውን ሕያው ቃል ሳይጠቅሱት ማለፍ እንዴት ይቻላቸዋል?

መልስ:- *አይቻላቸውም::*

## ምዕራፍ ፰፤ ጸሎት::
## "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው: የሰላምታ ጸሎት ሐተታ::

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ: እኛ ኢትዮጵያውያን: በዚህ ረገድ: ለዚህ ጸጋ ያበቃችን እርሷ: ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አምነን: በጸሎት የምናቀርብላት ሰላምታ: *"በአምላካችንና በመድኃኒታችን: በኢየሱስ ክርስቶስ: አንቺ ለእኛ: የአደራ እናታችን: እኛም ለአንቺ: የአደራ ልጆችሽ ነንና: ከተወደደው ልጅሽ: ያልተለየው እናትነትሽ: ከእኛም: ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን::"* የሚል ሊኾን አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል::*

ጥያቄ:- እግዚአብሔር: እኛን ሰዎችን: በመልኩ ፈጥሮ: በምድረ ገነት ማኖሩ ሳያንስ: በገዛ የጥፋት ምርጫችን: አጥተነው የነበረውን: የተቀደሰ ህልውናችንን: በቤዛነቱ መልሶ: ባቀዳጀን: በዘለዓለም መንግሥቱ: በዚህ ዓለም ኾነ: በሚመጣው ዓለም: በሕይወት እንድንቀጥል ማድረጉን አውቀናል:: እንደገና ደግሞ: ይህ ኹሉ ቸርነቱ ሳይበቃው: በዚህ ምድራዊና ሰማያዊ ህልውናችን ጊዜ: እኛ: የእርሱ ልጆች ኾነን: እርሱን: "አባታችን!" ብለን እንድንጠራው ብቻ ሳይኾን: የልጁ እናት: የድንግል ማርያምም ልጆች ኾነን: እርሷን: "እናታችን!" ብለን እንድንጠራ ማድረጉንም እነሆ: ተገነዘባችሁ::
በሥጋ ወልደውን: በሞተ ሥጋ በተለዩንና በሚለዩን: በምንወድዳቸው ወላጆቻችን ምትክ: አባት: እንዳያምረን: እርሱ: እግዚአብሔር: እንዲህ: የዘለዓለም ሕያው አባት ሊኾነን: እናትም እንዳያምረን: እርሷ: እመ አምላክ ድንግል ማርያም: እንዲህ: የዘለዓለም: ሕያውት እናት እንድትኾነን በመፍቀዱ ልናመሰግነው አይገባንምን?

መልስ:- *ፈጽሞ ይገባናል እንጂ::*

ጥያቄ:- ታዲያ! እንዲህ ከኾነ: እኛ ኢትዮጵያውያን: በዚህ ረገድ: ለዚህ ጸጋ ያበቃችን እርሷ: ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አምነን: በጸሎት የምናቀርብላት ሰላምታ: *"ይህን ያደረገ: ቸሩ አባታችን: ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: ለዘለዓለሙ፤ አሜን::"* በሚል ቃል ሊፈጸም አይገባምን?

መልስ:- *አዎን! ይገባል::*

እኔም: ከዚህ አያይዤ: "እንግዲህ: ኢትዮጵያውያን የሚያቀርቡትን: የ"አቡነ ዘበሰማያትን" እና የ"በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል"ን ጸሎታት በሚመለከት: በእኔ ጠያቂነትና በእናንተ መላሽነት ስንለዋወጥ የቈየነውን ሐተታ: በዚህ የመጨረሻ አዎንታዊ መልሳችሁ: እነሆ: አጠቃልለን ጨረስን:: ከዚህ በኋላ: ወደመደበኛው የቃለ ምልልስ ሥርዓታችን ተመልሰን: በእናንተ ጠያቂነትና በእኔ መልስ ሰጪነት: ውይይታችንን እንቀጥላለን::" አልኳቸው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ኹለቱ ወጣቶች፡ "እሺ!" በሚለው የስምምነት ቃል፡ ነገሬን ከተቀበሉኝ በኋላ፡ ከዚህ ቀጠል አድርገው፡ እንዲህ የሚል ጥያቄን አቀረቡልኝ፦

መለኮት፡ በሰብአዊው ምርጫና ውሳኔ ውስጥ ያለው ተሳትፎ፡፡

ጥያቄ፦ *የዚህን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን የሰላምታ ጸሎት ሐተታ ከመዝጋትህ በፊት፡ በመጀመሪያው ዋና ውይይታችንና በኋኹኑም ላይ፡ ድንግል ማርያምን በሚመለከት፡ ካገኘነው እውቀት የሠረፁ አንዳንድ የጥያቄ አሳቦች ስላሉን፡ እንደተለመደው፡ መልሱን በማግኘት፡ አእምሮአችን እንዲያርፍ ትረዳን ዘንድ፡ በዚህ አጋጣሚ እንድናነሣቸው ብትፈቅድልን?*

መልስ፦ *መልካም ነዋ! በሏ፡ ታዲያ እስኪ አምጡት!? ደስ ይለኛል፡፡*

ጥያቄ፦ *በቀደሙት ውይይቶቻችን ላይ፡ ድንግል ማርያምን በተመለከተ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰብአዊው ፍጡሩ፡ ያለአድልዎና ያለልዩነት፡ ለኹሉ፡ በነፍስ ወከፍ በሰጠው፡ የመምረጥና የመወሰን ሥልጣን ጸጋ፡ እርሷም ተጠቅማ፡ ራሷን በንጽሕና፥ በቅድስና በመጠበቋ፡ ለእግዚአብሔር እናትነት መብቃቷን፡ አብራርተህ ገልጸህልን እንደነበረ፡ ትዝ ይለናል፡፡*

*ይኼ እንዳለ ኾኖ፡ በእዚህ የፍጹምነት ብቅዓት ውስጥ፡ የእግዚአብሔር ጥበብ የለበትም ወይ? በብፅዓት እንድትወለድ፡ በቤተ መቅደስ እንድታድግ እና የመሳሰሉት እውን ድርጊቶች፡ በእርሷ ምርጫ፥ ወይም፡ በእርሷ ፈቃድ ያልተፈጸሙ፡ የእግዚአብሔር ድንቅ ጥበቦች አይደሉምወይ?*

*ይህን ውይይታችንን ከጀመርን ወዲህ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ዜና አበውን የማንበብ ባህልን ስለመሠረትን፡ ከዚያ አድራጎታችን ካተረፍነው እውቀት፡ አንዳንድ እውነታዎችን፡ ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስልህ፡ እንደነኤርምያስ እግዚአብሔር፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመን፡ ከነቢያት መካከል፡ እንደነኤርምያስ፡ በአዲስ ኪዳኑም ያሉትን፡ ገና በማሕፀን ሣሉ፡ ለራሱ የመለየቱን ምሥጢር፡ በአዲስ ኪዳኑም ዘመን፡ ከቅዱሳን ጻድቃኑ መካከል፡ እንደቅዱስ ቂርቆስ፡ እንደነአባ ገብረ መንፈስ ቅዱስና አባ ተክለ ሃይማኖት ያሉትን፡ ገና፡ በሕፃንነታቸው፡ ለቅድስና የመምረጡን ነገር፡ ከአንተ አገላለጽ ጋር ብታስማማልን?*

መልስ፦ ለዚህ ጥያቄያችሁ፡ የተለመደ አድናቆቴን በማስቀደም፡ መልሴን አከታትልላችኋለሁ፦ "*እግዚአብሔር፡ ሰውን፡ በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ በልቡም አዘነ፡*" የሚለው አገላለጽ፡ በዚያን ጊዜ፡ የሰው ክፋት፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ የቱን ያህል የበዛና የጸና እንደነበረ፡ ለፍጥረታዊው ሰው፡ ሊገባው በሚችል አነጋገር ለማስረዳት ያህል እንጂ፡ ከአዳምና ሔዋን ጥፋት ጀምሮ፡ የሰው ልጆች የፈጸሙት ድርጊት፡ አስቀድሞ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ በገሃድ ሳይታወቅ ቀርቶ አልነበረም፡፡

## ምዕራፍ ፫፣ ጸሎት።
## መለኮት፡ በሰብአዊው ምርጫና ውሳኔ ውስጥ ያለው ተሳትፎ።

ደግሞም፡ ኹሉን የሚያውቀው ፈጣሪ ይቅርና፡ ስለመጪው፡ ምንም የማያውቀው ፍጡሩ ሰው እንኳ፡ በወላጅነት ፍቅሩ፡ በልጆቹ መካከል፡ ማበላለጥ አይታይበትም፡ እግዚአብሔርማ፡ በእግዚአብሔርነቱ፡ በፍጡሩ መካከል፡ አበላልጦ የመውደድ ልዩነትን እንዴት ያደርጋል? እንደማያደርግ ይታመናል፡ ይህንም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለፍጥረቱ ኹሉ በፈጸመው ፍጹም ፍቅሩ፡ አረጋግጦ አሳይቷል።

ነገር ግን፡ *"'ያዕቆብን ወደድሁ፡ ኤሳውን ግን ጠላሁ፡' ተብሎ እንደተጻፈ፡ ለእርሷ* (ለእናቲቱ ለርብቃ)፡ *'ታላቁ፡ ለታናሹ ይገዛል!' ተባለላት።"* የተባለው አምላካዊ ቃል፡ ምን መልእክት እንዳለው፡ በሃይማኖት ያገኘነው የመንፈስ ቅዱስ እውቀት፡ ምሥጢሩን እየተረጐመና እያብራራ ይነግረናል፡ ይኸውም፡-

ሀ. እግዚአብሔር፡ ሰብአውያን ፍጡሮቹን የሚያውቃቸው፡ በንጽሓ ጠባይዕ ከተፈጠሩበት ከእናታቸው የማሕፀን ሽል ጀምሮ፡ ተወልደው፡ ነፍስ እስከሚያውቁበት ዕድሜያቸው፡ ከዚያም፡ እስከዕለተ ሞታቸው ድረስና ፍጻሜ በሌለው፡ በዘለዓለማዊው ህላዌያቸው ብቻ ሳይኾን፡ ገና፡ ከመፈጠራቸውም በፊት የመኾኑ እና፡

ለ. በዚህ፡ መነሻ ባለው፡ ግን፡ መድረሻ ባልተደረገለት ዘመናቸው መካከል፡ እነዚሁ ፍጡሮቹ፡ እርሱ፡ በሰጣቸው፡ የማወቅ ኃይል፡ የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን በመጠቀም፡ በኑሮአቸው አካኼድና በህልውናቸው ግብ፡ ከምን ዓይነቱ የሕይወት ዓላማ እንደሚደርሱ፡ በመለኮታዊው የፈጣሪነት ባሕርዩ፡ አስቀድሞ የማወቁ እውነታ ነው።

ስለዚህም፡ እነዚህ መንትዮች ወንድማማቾች (ኤሳውና ያዕቆብ)፡ ገና፡ በእናታቸው ማሕፀን ሳሉ፡ በንጽሓ ጠባይዕ የተሠራው የደግነት ተፈጥሮአቸው፡ እየራሳቸውን ለአካለ መጠን ሲያደርሱ፡ እያንዳንዳቸው፡ የትኛውን ዓይነት የህልውና ምርጫን በማድረግ፡ በንጽሕናው እንደሚቀጥሉበት፡ ወይም፡ እንደሚያሳድፉት፡ ስላወቀ፡ ስለእያንዳንዳቸው ምንነት፡ ፈጣሪ፡ አስቀድሞ፡ እንዲህ ተናገረ፡ ይህም ማለት፡ ኤሳው፡ ፈጣሪው የሚጠላውን፡ በእግዚአብሔር ሥርዓት ላይ ማመፅን፡ ያዕቆብ ግን፡ ፈጣሪው የሚወድደውን፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት አክብሮ መኖርን እንደሚመርጡ፡ እግዚአብሔር፡ አስቀድሞ አወቀ ነው።

በኢየሱስ ክርስቶስና በተከታዮቹ ላይ ከነበረው ጽኑ ጥላቻ የተነሣ፡ እስከመግደል የደረሰ ተቃውሞን ያሳየውንና *"የመውጊያውን ብረት መቃወም፡ ለአንተው ይብስብሃል!"* የሚል ማስጠንቀቂያ የተሰጠውን፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የኋላ ኋላ፡ ለምን የተመረጠ መሣሪያው አድርጎ፡ ዓለምን አስተማረበት? እግዚአብሔር በሚያውቃት እውነት፡ ፈጣሪው ለመሠረታት ሃይማኖት፡ ፍጹም ቀናተኛ መኾኑን፡ በአምላክነቱ፡ አስቀድሞ ስላወቀ አይደለምን?

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ታዲያ! እውነታው እንዲህ ከኾነ፡ በአንድ በኩል፡ ሌላው ፍጡር፡ በምንም መንገድ ሊያውቀው የማይቻለውን፥ በእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ሕሊና ውስጥ የተደበቀውንና እንደቀደሙት አነጋገር፡ "ልቡና ያሰበውን፥ ኩላሊት ያመላለሰውን"፡ ሥውር አሳብ ብቻ ሳይኾን፡ ያ ግለሰብ፡ ነፍስ ሲያውቅ፡ ማንነቱ የሚገለጽበት፡ የኑሮ ምርጫው፡ ምን እንደሚኾን፡ ገና ሳይወለድ፥ ሳይፀነስም፡ አስቀድሞ የማወቁ ሥልጣን፡ የፈጣሪ ብቸኛ ሀብት ሲኾን፥ በሌላው በኩል ደግሞ፡ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ያለው፡ ያ፡ የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን፡ ራሱ፡ የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ፥ የአምላክ ተአምራዊ ሥራና የመለኮት ድንቅ ጥበብ መኾኑ አይደለምን?

እግዚአብሔር፡ እነኤርምያስን፡ በማሕፀን፥ እነቅዱስ ቂርቆስን፥ ገብረ መንፈስ ቅዱስንና ተክለ ሃይማኖትን፡ በሕፃንነት፡ ለራሱ የለየው፥ ይልቁንም፡ እመቤታችን፡ በብፅዓት እንድትወለድ፡ ማለትም፡ መካኖቹ ወላጆቿ ኢያቄምና ሐና፡ እርሷን ይወልዱ ዘንድ እንዲሳሉ፥ እርሷም፡ በቤተ መቅደስ እንድታድግ የኾነበት ትንቢታዊ ትንግርት የተፈጸመው እኮ፡ ከዚሁ፡ ከእግዚአብሔራዊው የቅድሚያ እውቀትና ከፈጣሪነቱ የቸርነት ስጦታ፥ ከአምላክነቱ ተአምራዊ ሥራና ከከሃሊነቱ ድንቅ ጥበብ የተነሣ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ በተፈጥሮው በታደለው፡ በዚሁ፡ የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን፡ ስማቸው፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ነቢይና ጻድቃን፥ እመቤታችንና ወላጆቿ ስለተጠቀሙበት እኮ ነው።

እመቤታችንስ፡ በውዳሴዋና በቅዳሴዋ፡ "ተፈሥሒ እስመ ድልወ፡ ተሰመይኪ፡ ኦ ወላዲተ አምላክ! ...እስመ ድልወ ኮንኪ፡ ለተወክፎ ቃለ አብ፤" "ወሶበ ርእየ ንጽሕናኪ ለሊሁ እግዚአብሔር አብ፡ ፈነወ ኀቤኪ፡ መልአኮ ብርሃናዊ!" ማለትም፡ "በቅተሽ ብትገኚ፡ የአምላክ እናት ተብለሻልና። ...የእግዚአብሔር ቃልን ለመቀበል፡ በቅታ ተገኝታለችና!" "እግዚአብሔር አብ፡ ራሱ፡ ንጽሕናሽን ባየ ጊዜ፡ ብርሃናዊ መልአኩን ወደአንቺ ሰደደ!" መባልዋ፡ በፈጣሪዋ ዘንድ፡ አስቀድሞ የታወቀውን፥ በዚያ የምርጫ ነጻነቷና የመወሰን ሥልጣንዋም፡ ራስዋን፡ ለእርሱ እናትነት የተገባችና የበቃች[፻፶፰] አድርጋ የማስገኘቷን ነገር፡ ለማረጋገጥ አይደለምን? አዎን! ነው።

### የሴቶች ርኵሰትና መርገም፡ በቅድስናና በበረከት ስለመተካቱ።

*ጥያቄ፡- የአምላክ እናት ለመኾን የበቃችው፡ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ነገር፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና ከተነሣ ዘንድ፡ በተለይ ሴቶችን በሚመለከት፡ ከሰብአውያን ፍጡራን እናት፡ ከሔዋን ጀምሮ፡ እስከእርሷ ድረስ፡ በኪዳነ ልቦናም ኾነ፡ በኪዳነ ኦሪቱ፡ ጸንቶ ስለኖረው ርኵሰትና መርገም፡ ከዚህ ጋር አያይዘህ ብትነግረን? ማለትም፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዳና አድጋ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እስክትጸንሰውና እስክትወልደው፥ እርሱም፡ በቤዛነቱ፡ ፍጥረተ-ዓለሙን እስኪያድነው ድረስ ጸንቶ የኖረው፡ ይኸው ርኵሰትና መርገም፡ በኪዳነ ምሕረቱም ዘመን፡ ቀጥሏል? ወይስ፡ ተሻሽሏል? ወይስ፡ ተሽሩዋል?*

## ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት።
## የሴቶች ርኵሰትና መርገም፡ በቅድስናና በበረከት ስለመተካቱ።

*እኛ ግን፡ ከሕፃንነታችን አንሥተን እስካኹን፡ በኢትዮጵያዊው ቤተሰባችን ዘንድና በዚሁ ኅብረተሰባችን መካከል፡ በይፋና በገሃድ ሰፍኖ እንደምንመለከተው ከኾነ፡ በአዲስ ኪዳኑ የምሕረት ዘመን አቢጋዞች፡ በድንግል ማርያም እመ አምላክነትና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች፡ የፈጸመው የቸርነት ሥራውና ያጎናጸፈው የማዳኑ ጸጋ፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ በተለይም፡ ለኢትዮጵያውያት፡ በዚህ ረገድ፡ ምንም ዓይነት ለውጥን፡ ወይም፡ መሻሻልን ያመጣ መስሎ አይታይም፡ እንዲያውም፡ ያን ኹሉ፡ የአምላክን፡ የቸርነት ሥራና የማዳን ጸጋ፡ ከንቱ ያደረግነው ይመስላል። ታዲያ! ይህ፡ ታላቅ ስሕተት፡ እንዴት ሊኾን፡ እስከዛሬም ጸንቶ ሊቀጥል ቻለ?*

መልስ፡- ይህን ጥያቄ፡ እንኳን አነሣችሁት! መቼም፡ ጠንቀኞች ለኾኑት ችግሮቻችን ኹሉ፡ መፍትሔዎቹን ፈልገን ለማግኘት፡ የተቻለንን ያህል ጥረት እናደርግ ዘንድ፡ እናንተን፡ ለመድኃኒትነት ልኳችኋልና፡ እግዚአብሔር ይመስገን! አኹንም፡ ለዚህ ቁም ነገር ላለው ጥያቄያችሁ የምሰጣችሁን መልስ፡ እንደቀደሙት ኹሉ፡ በጥንቃቄ አዳምጣችሁና በማስተዋል ተመልከታችሁ፡ ለጣፋጩ ፍሬ ታበቁት ዘንድ አሳስባችኋለሁ።

አዎን! እኛ ሰዎች፡ ከሥጋዊው ተፈጥሮአችን የተነሣ፡ የክፉት ኃይል፡ የኃጢአት ቀምበርና የሞት ፍዳ ሠልጥኖብን የኖርንበትን ያባርነትና የጨለማ ኑሮ፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ፡ እንዴት አድርጎ፡ አስወግዶና ከዚያ አሠቃቂ ህልውና፡ ነጻ አውጥቶ፡ ባስገኘልን የንስሓ ጸጋና በቅዱስ ቍርባኑ አማካይነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን፡ የጽድቅ ትጥቅንና የትንሣኤ ሕይወትን አጎናጽፎ፡ በሥጋችንም፡ በነፍሳችንም፡ ለተድላ ገነት እንዳበቃን፡ በዝርዝር አውቃችኋል። ይህም ማለት፡ የክፉት ዝንባሌያችን፡ ካመጣው ኃጢአታችን የተነሣ፡ ከወደቀብን መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ ተላቅቀን፡ በዚያ ፋንታ፡ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን ተቀብለን መኾናችንን፡ እስካኹን ካደረግናቸው ውይይቶቻችን፡ በሚበቃ እንደተገነዘባችሁ አምናለሁ።

ይኹን እንጂ፡ የሰው ልጆች፡ በሥጋም፡ በነፍስም ላይ ሰፍኖ፡ ይገዛ ከነበረው፡ ከማናቸውም ረቂቅ ባርነትና ግዙፍ ጭቈና፡ ሰው በኾነው፡ በራሱ፡ በመለኮት መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ አርነት በመውጣት፡ ይህን የመሰለውን የድል አክሊል የተቀዳጁ ኾነው ሣሉ፡ ምንም ነገር እንዳልተደረገላቸው በማስመሰል፡ ይልቁንም፡ ከእኛ፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ልጆችና ባለአደራዎች ከተባልነው ኢትዮጵያውያን መካከል ጭምር፡ ብዙዎች፡ እየራሳቸውን፡ ገና በመርገሙ ቀምበር ውስጥ ተቀፍደው እንዳሉ አድርገው በመቍጠር፡ እነሆ፡ በዘመኑ ብሉዩ የኦሪቱ ሥርዓት ተሸክመነው በኖርነው ከባድ ቀንበር ሥር ሲማቅቁ ይታያሉ። ታዲያ! እንዲህ ኾነው መገኘታቸው፡ እጅግ የሚያስገርም፡ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ብቻ ሳይኾን፡ በዓለም ክርስቲያናውያን ሕዝቦችም ዘንድ የሚያሳፍርም አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ያሳፍራል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*ይህም የሚኾነው፡ "እናንት ደካሞች! ሸክማችሁ የከበደ ኹሉ! ወደእኔ ኑ! እኔም አሳርፋችኋለሁ! ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ! ከእኔም ተማሩ! እኔ፡ የዋህ፡ በልቤም፡ ትሑት ነኝና፡፡ ለነፍሳችሁም፡ ዕረፍትን ታገኛላችሁ፣ ቀንበሬ፡ ልዝብ፡ ሸክሜም ቀሊል ነውና፡፡"* የሚለውን፡ ገና፡ የዛሬ ኹለት ሺ ዓመት፡ ሰው በኾነው አምላክ እንደበት የተነገረውን፡ የርኅራኄና የምሕረት አዋጅ፡ ይኸው ኢትዮጵያዊው ትውልድ፡ አኹንም፡ ገሸሽ በማድረግ ነው፡፡ ለዚህ እውነታ ማረጋገጫ የሚኾን ማስረጃን ለማግኘት፡ ብዙ መድከምም አያስፈልግም፡ በዘወትሩ ጸሎታችን ውስጥ ያሉትና ከዚህ አከታትዬ የምጠቃቅስላችሁ፡ እየራሳችን፡ በአንደበታችን፡ ለልማዱ፡ በየቀኑ የምንደግማቸው፡ ነገር ግን፡ ኸን ብለን፡ እውነተኛ ትርጉማቸውንና ግልጽ መልእክታቸውን ተረድተንና አስተውለን፡ በዚህ ረገድ የሚገባንን ግዴታ ለመፈጸም [፻፶፱] ያልፈለግናቸው ሃይማኖታውያን ቃላት፡ ለምስክርነት ይበቁናል፡፡

የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ብዙው፡ ከንስሓው ጥሪና ከቅዱስ ቍርባኑ ግብዣ ይልቅ፡ በክፋቱና በኀጢአቱ ሥራ ጸንቶ፡ በአመንዝራነቱ መቀጠልን፡ በዓመፁና በክህደቱም በኩል፡ የአምልኮ ባዕዱን ግብር ጭምር፡ በተለያየ መልኩ ማጠናከርን፡ ምርጫውና ግዴታው አድርጎ የተያያዘው መኾኑን፡ እነሆ፡ በጊዜያችን ኹኔታ፡ በገሃድ እያየነው እንገኛለን፡፡

እንደምታውቁት፡ የክፋቱ ውጥን፣ የኀጢአቱም ድርጊት፥ የመርገሙ ቅጣትና በመጨረሻ፡ የሞቱ ጠንቅ የሠረፀው፡ ከሔዋን መኾኑን፡ የሃይማኖታችን ምንጭ የኾኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ያመለክታሉ፡ ይህም፡ *በፀነስሽ ጊዜ፡ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፡ ፈቃድሽም ወደባልሽ ይኾናል፡ እርሱም፡ ገዢሽ ይኾናል!"* ከሚለው የፈጣሪ እርግማን ይነሣል፡ ቀጥሎም፡ *"ሴት ብታረግዝ፡ ወንድ ልጅም ብትወልድ፡ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፡ እንደሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች፡፡ በስምንተኛውም ቀን፡ ልጁ፡ ከሥጋው ሸለፈት፡ ይገረዝ! ከደምዋም እስክትነጻ፡ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ! የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ፡ የተቀደሰን ነገር አትንካ! ወደመቅደስም አትግባ! ሴት ልጅም ብትወልድ፡ እንደመርገምዋ ወራት፡ ኹለት ሳምንት ያህል፡ የረከሰች ናት፣ ከደምዋ እስክትነጻ ድረስ፡ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ!"* እስከሚለው [፻፷] ድረስ፡ በብሉይ ኪዳኑ ውስጥ የተመዘገበው አምላካዊ ቃል ነው፡፡

ይህን መርገም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል መከራው፡ ቅዱስ ሥጋውን እስከመቍረስና ክቡር ደሙንም እስከማፍሰስ፥ ከዚያም፡ ጽዋ ሞቱን ተቀብሎ፡ እስከመሞትና እስከመቀበር፡ በመጨረሻም፡ እስከመነሣት ደርሶ፡ ፈጽሞ አስወግዶታል፡፡ የዚህም እውነታ፡ ከዚህ በሚከተሉት፡ የአዲስ ኪዳኑ ጥቅሶች በሚበቃ ተገልጿል፡-

# ምዕራፍ ፫፡ ጸሎት።
# የሴቶች ርኵሰትና መርገም፡ በቅድስናና በበረከት ስለመተካቱ።

*"ወንድሞቻችን [እና እኅቶቻችን] ሆይ! አኹንም፡ የክርስቶስ አካል ስለኾናችሁ፡ ከሙታን ተለይቶ ለተነሣው፡ ለዳግማዊው አዳም ትኾኑ ዘንድ፥ ለእግዚአብሔርም፡ የጽድቅ ፍሬን ታፈሩ ዘንድ፡ ከኦሪት፡ በሞት ተለይታችኋል። እስካኹን፡ የሰውን ሕግ ስለሠራን፡ በኦሪት ሕግ ደካማነት ምክንያት፡ ቅጣቱ ጸናብን፤ ሞትንም አፈራን። አኹንማ፡ በአሮጌው ኪዳን የጽሑፍ ሕግ ሳይኾን፡ በአዲስ ኪዳኑ፡ የመንፈስ ሕግ እንኖር ዘንድ፡ ከኦሪት ተሰናብተናል! የቀደመ ትምህርታችንንም ትተናል!*

*"በኦሪት ሕግ ያሉ ኹሉ፡ በመርገም ውስጥ ይኖራሉ፡ መጽሐፍ፡ "በዚህ፡ በኦሪት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን ሠርቶ የማይፈጽም ኹሉ፡ ርጉም ይኹን!" ብሏልና። የኦሪትን ሕግ በመሥራት፡ እንደማይጸድቁስ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ይታወቃል፤ "ጻድቅ ግን፡ በሃይማኖት ይኖራል።" ተብሎ እንደተጻፈ።*

*"ክርስቶስ፡ ቤዛእኛ፡ ሕግን በመፈጸሙና የኦሪትን መርገም በመሸከሙ፡ እኛን፡ ከኦሪት መርገም ዋጅቶናል፤ መጽሐፍ፡ በእንጨት ላይ የተሰቀለ ኹሉ፡ "ርጉም ነው!" ይላልና።*

*"በእኛ ላይ የነበረውን፡ የሚቃወመንንም፥ በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት[፻፵፮] ደመሰሰው፤ እርሱንም፡ በመስቀል ጠርቆ፡ ከመንገድ አስወግዶታል።"*

ከመጀመሪያዪቱ ሔዋን ጀምሮ፡ እስከዳግማዊቷ ሔዋን ድረስ፡ የነበሩት የቀደሙት ሴቶች፡ ከባሕርያቸው ያነቁት (ያፈለቁት) የክፋት አሳባቸው፡ ባስከተለው የኃጢአት ጠንቅ ምክንያት፡ በተፈጥሮ ሥርዓት የሚያዩት የወር አበባ ሳይቀር፡ ርኵሰትና መርገም እንዲኾንባቸው ተፈርዶባቸው የኖሩበት፡ የውርደት ህልውና፡ በቅድስት ድንግል ማርያም አብቅቶላቸዋል፤ ይህም፡ በልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ለዘለዓለም ተወግዶላቸውና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተተክቶላቸው፡ በምሕረት በረከትና በቅድስና ሕይወት እንዲኖሩ መደረጉን፡ ከብሉያቱና ከሓዲሳቱ መጻሕፍት የተጠቀሱት፡ የእግዚአብሔር ቃላት በግልጽ አመልክተውናል።

ይህ፡ በአዲሱ ኪዳን ስርየት የተገኘው፡ የቅድስና ሕይወትና የምሕረት በረከት፡ በማንና እንዴት ሊገኝ እንደቻለ፡ ሴቶችን ኹሉ ወክላ፡ ከዘመናት የርኵሰት ውርደትና የመርገም ቀንበር ነጻ በማውጣት፡ ለዚህ ታላቅ ጸጋ ያበቃቻቸው የአምላክ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ መንፈስ ቅዱስን በተመላ አንደበቷ፡ እንዲህ ስትል፡ ራሷ የተናገረችው የጸሎት ቃል፡ አጠቃልሎ ያስረዳል፡-

*"ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን በታላቅ ክብር ታመሰግነዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ እጅግ ደስ ይላታል፤ እኔ አገልጋዩ፡ በውርደት የምቀበለውን ፈተናና መከራ ተመልክቶልኛልና። እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ "ብፅዕት!" ይሉኛል፤ እርሱ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና። ስሙ፡ ቅዱስ ነው። እርሱን በሚፈሩት ዘንድ፡ ምሕረቱ፡ ለልጅ ልጅ ይኖራል። ታላላቅ ሥራዎቹን፡ በክንዱ ያደርጋል።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*"በእውቀታቸው የታበዩትን፡ በታተናቸው፤ በኃይላቸው የተመኩትን፡ ከሥልጣናቸው አወረዳቸው፤ የተዋረዱትንም፡ ከፍ ከፍ አደረጋቸው፤ የተራቡትን፡ ከበረከቱ አጠገባቸው፤ በሀብታቸው የታመኑትን፡ ዕርቃናቸውን ሰደዳቸው፤ ብላቴናውን እስራኤልን ተቀበለ፤ ለአባቶቻችን፡ ለአብርሃምና [፻፶፱] ለዘሩም፡ እስከዘለዓለም የገባውን፡ የቃል ኪዳን ምሕረቱን አስታወሰ።"*

እንግዲህ፡ ሴቶች፡ በተለይም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያት፡ እየራሳቸውን፡ ለዳግማዊቷ ሔዋን፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ልጅነት ማብቃት እንጂ፡ እንደገና ተመልሰው፡ የቀዳማዊት ሔዋን ልጆች ወደሚያሰኛቸው፡ ወደነበሩበት ውርደት፡ ማለትም፡ ወደክፋትና ወደርኵሰት፡ ወደኃጢአትና ወደመርገም፡ በመጨረሻም ወደሞት ግብር መመለስ የሚገባቸው አይደለም።

ጥያቄ:- *የሃይማኖታችን እውነታ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ፡ ለምንድር ነው፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ የሴት የወር አበባ፡ በየራሳቸው፡ በእናቶቻችንና በእኅቶቻችን፡ ዘንድ ኾነ፡ በኅብረተሰቡ ዘንድ፡ በካህናትም ዘንድ ሳይቀር፡ ልክ፡ እንደአራቱ ዘመን፡ "አደፍ ጉድፍ" ተብሎ፡ የርኵሰትና የመርገም ምልክት ኾኖ የሚታየው? ከዚህ የተነሣም፡ እነርሱም፡ እየራሳቸውን፡ ሌላውም፡ እነርሱን፡ እንደርኩስና እንደርጉም በመቍጠር፡ ወደቤተ ክርስቲያን ገብተው፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ከመቀበል፡ እየራሳቸውን የሚከለክሉት፡ ሌላውም፡ የሚከለክላቸው ለምንድር ነው? እንዲያውም፡ ሴት፡ በምትወልድበት ጊዜ፡ የወለደችው፡ ወንድ የኾነ እንደኾነ፡ እስከአርባ ቀን ድረስ፡ ሴት የኾነች እንደኾነ፡ እስከሰማንያ ቀን ድረስ፡ እንደርኵስና ርጉም ተቆጥራ፡ እርሷ ብቻ ሳትኾን፡ እርሷን፡ "እንኳን ማርያም ማረችሽ!" ብሎ ሊጠይቃት የመጣው ሰው ኹሉ ጭምር፡ ዐራሷ ቤት በመግባቱ ብቻ፡ እንደርኵስና ርጉም ተቆጥሮ፡ "ጠበል፡ ማለትም፡ ካህን የጸለየበትን፡ የተቀደሰ ውኃ ሳይረጭና በካህኑ መስቀል ሳይባረክ፡ ወደቤተ ክርስቲያን አይገባም!" የሚባለው፡ ኩፉ ለምንድር ነው?*

መልስ:- ይህ፡ የሴት የወር አበባ መታየት ልማድ፡ የኋላ ኋላ፡ በአዳምና ሔዋን ኃጢአት ምክንያት፡ ሰዎች፡ የርኵሰትና የመርገም ምልክት ኾኖ እንዲቆጠር አደረጉት እንጂ፡ ጥንት፡ ፈጣሪ፡ በጥበቡ የሠራው፡ ይኸው፡ የሥነ ፍጥረት ድንቅ ሥርዓት፡ ይህን ለመሰለው፡ ጸያፍ መጣሪያነት እንዲያገለግል ይደረጋል ብሎ ለማሰብም ቢኾን፡ እጅግ ይከብዳል። እግዚአብሔር፡ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት ውሕደት እንዲወሰን አድርጎ የሠራውን የጋብቻን ሥርዓት፡ ሙሴ፡ በዘመን አራት፡ በአይሁድ ክፋትና ልበ ደንዳናነት ምክንያት፡ እንዲለያዩ የሚገፋፋ ፈቃድን የሚሰጠውን ሰው-ሠራሽ ሕግ እንዲያወጣ ተገድዶ እንደነበረ፡ ያም፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተንቅፎ፡ ወደቀድሞ መሠረቱ እንዲመለስ መደረጉን ታውቃላችሁ።

## ምዕራፍ ፳፡ ጸሎት።
## የሴቶች ርኵሰትና መርገም፡ በቅድስናና በበረከት ስለመተካቱ።

ይህም፡ የሴትን የወር አበባ፡ የርኵሰትና የመርገም ምልክት የማድረጉ ነገር፡ በዚህ መልክ የገባ ወግ ሊኾን እንደሚችል መገመቱ ያስኬዳል፡ ለዚህም፡ ቀደም ብዬ በጠቀስሁላችሁ፡ እግዚአብሔር፡ በሔዋን ላይ ባሰማው የእርግማን ፍርድ ላይ እንኳ፡ ይህንኑ፡ የሴትን ወርኃዊ ደም፡ በርኵሰትና በመርገምነት መልክ አለማንሣቱ፡ በቂ ማረጋገጫ ነው። ምናልባት ያም ባይኾን፡ በቅድስት ድንግል ማርያም፡ የአምላክ እናትነትና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ መርከሻነቱና እርግማንነቱ ተሽሮ፡ ርኵሰቱ፡ በቅድስና፡ መርገሙ በበረከት መተካቱን፡ አኹን ያደመጣችሁት፡ የመጽሐፍ ቃል፡ ከምሥራቹ መልእክት ጋር አረጋግጦ ያስረዳል።

ከእነዚህ፡ ከሰማችኋቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት በቀር፡ በሰባቱም የሳምንቱ ቀኖች፡ በየዕለቱና በየሰዓቱ የምንደግመው፡ አምላክን የወለደች፡ የእናታችንና ንግሥታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የውዳሴዋ ጸሎታችን፡ የሚያሰማን የምሥራች አዋጅ፡ ምን እንደሚል፡ እስኪ፡ ለማስረጃ ያህል፡ በጥቂቱ ጠቃቅሰን እንመልከተው!

፩ኛ. በሰኞ ዕለት ከሚጸለየው መካከል:-

*ሀ. ዲያብሎስ፡ በእባብ ተመስሎ፡ የሳታትን ሔዋንንም፡ "ምጥሽንና ጣርሽን አበዛዋለሁ!" ብሎ፡ ከፈረደባት በኋላ፡ ለሰው ልጅ ራርቶና ሰውን ወድዶ፡ ከዚህ መርገም ነጻ አደረጋት።*

*በ. ሕያው ነፍስ ያላቸው የሰው ልጆች ኹሉ፡ እጅግ ደስ ይላቸዋል፡ ሐኔትም ያደርጋሉ፡ "በሰማይ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና ይኹን! በምድርም፡ ሰላም ይኹን! የሰው ልባዊ ምኞቱ ነውና፡" እያሉ፡ ከመላእክት ሠራዊት ጋር አስምተው በመዘመር፡ ንጉሡን ክርስቶስን ያመሰግኑታል፡ <u>እርሱ፡ የቀድሞውን እርግማን ሽሮአልና፡</u> የዲያብሎስንም የጠላትነት ዕቅድ አፈራረሰበት። በዳዊት አገር የተወለደልን፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አዳምና ሔዋን፡ በዕዳ ተይዘው የኖሩበትን መዝገብ ቀድዶ አጠፋላቸው፤ ከዕዳውም፡ ነጻ አደረጋቸው።*

፪ኛ. በማግሰኞ ዕለት ከሚጸለየው መካከል:-

ሀ. *<u>የመመኪያችን ዘውድ፥ የደኅንነታችን መጀመሪያ፡ የንጽሕናችንም መሠረት፡ በድንግል ማርያም ተገኘልን፤</u> ቤዛ ኾኖ፡ እኛን ያድነን ዘንድ፡ ሰው የኾነ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ወልዳልናለችና።*

በ. *ድንግል ማርያም ሆይ! "የአምላክ እናት!" ተብለሽ <u>ለመጠራት የተገባሽ ኾነሻልና፡ ደስ ይበልሽ! ለሔዋን መድኃኒቷ የኾንሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ!</u>*

፫ኛ. በረቡዕ ዕለት ከሚጸለየው መካከል:-

*ምሕረት ከሌለው፡ ከጠላታችን ከዲያብሎስ፡ የጭካኔ አገዛዝ፡ ነጻ አውጥቶ ሊያድነን የመጣውን፡ እግዚአብሔር ወልድን የወለድሽ ሆይ! ይኸው፡ <u>የማሕፀንሽ ፍሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ የሌለበት፥ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን የሚያድል ነው።</u>*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ስለዚህ፡ አንቺ፡ በሥጋሽም፥ በነፍስሽም ድንግልና፡ ፍጽምት ነሽ፤ መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፥ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጭ ነሽ።

፩ኛ. በሓሙስ ዕለት ከሚጸለየው መካከል:-

በተፈጥሮ ባሕርያችን ውስጥ ጸንቶ የኖረው፡ የቀድሞው መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ፡ በእርሷ ምክንያት የጠፋልን፡ አምላክን የወለደች፡ ድንግል ማርያም፡ የኹላችን መመኪያ ናት፤ ያም መርገም፡ እግዚአብሔር፡ አዳምንና ሔዋንን፡ "ሞትን ትሞታላችሁና፡ የእርሷን ፍሬ አትብሉ!" ያላቸውን፡ ዕፀ በለስን፡ ሔዋን፡ በሊታ፡ ያን ዓመፅ በፈጸመችበት ጊዜ ያመጣችው ነው። እንዲህ ኾኖ፡ በሔዋን ምክንያት፡ የተዘጋው የገነት ደጅ፡ በድንግል ማርያም ምክንያት፡ ዳግመኛ ተከፈተልን። እኛን ከመውደዱ የተነሣ፡ ከእርሷ፡ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም የመጣው፥ በመስቀል ላይ ተሠውቶም፡ ከዲያብሎስ፥ ከኃጢአትና ከሞት ያዳነን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከገነት የሕይወት ዛፍ ፍሬ እንበላ ዘንድ አደለን። ይህም፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ፡ "እንካችሁ፥ ብሉ! ንሡ፥ ጠጡ!" ብሎ፡ በምሴተ ሓሙስ የሰጠን፡ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው።

...ወዮ! የእግዚአብሔር የጥበቡ ምላትና ስፋት፡ ምን ይረቅ!? ምን ይጠልቅ!? ለዚህ እንክሮ ይገባል! "በፀነስሽ ጊዜ፡ ጭንቅሽን፡ እጅግ አበዛለሁ! በጭንቅ ትወልጃለሽ! ፈቃድሽም፡ ወደባልሽ ይኾናል!" ብሎ፡ በጣር፥ በጋርና በጽኑ ኀዘን አምጣ ትወልድ ዘንድ፡ የፈረደባት፡ ያች ማሕፀን፡ ማኅተመ ድንግልናዋ የተጠበቀ ኾኖ፡ ያለወንድ ዘር፡ ትድግናን ያስገኘች የሕይወት ምንጭ ኾነች! ከአዳምና ሔዋን ተያይዞ፡ በባሕርያችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣብንን፡ መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ ያጠፋልንን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደችልን።

፫ኛ. በዓርብ ዕለት ከሚጸለየው መካከል:-

ሀ. ድንግል ማርያም ሆይ! ከሴቶች ተለይተሽ፡ መርገመ ሥጋ፡ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፥ በረከተ ሥጋን፡ በረከተ ነፍስን፡ ከእግዚአብሔር ያስገኘሽ ነሽ! የማሕፀንሽም ፍሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መርገመ ሥጋ፡ መርገመ ነፍስ የሌለበት፥ በረከተ ሥጋን፡ በረከተ ነፍስን የሚያድል ነው። አደፍ ጉድፍ ሳይኖርብሽ፡ አምላክን የወለድሽ፡ ድንግል ማርያም ሆይ! የእውነት ፀሓይ የኾነው ጌታ፡ ከአንቺ ተወለደልን!

ለ. ድንግል ማርያም ሆይ! አንቺ፡ መርገመ ሥጋ፡ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፥ በረከተ ሥጋን፡ በረከተ ነፍስን፡ ከእግዚአብሔር ያስገኘሽ ነሽ! የማሕፀንሽም ፍሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መርገመ ሥጋ፡ መርገመ ነፍስ የሌለበት፥ በረከተ ሥጋን፡ በረከተ ነፍስን የሚያድል ነው።

ገ. ማርያም ድንግል፡ የሽቱ ሙዳይና የሕይወት ውኃ ምንጭ ናት። የማሕፀንዋ ፍሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዓለሙን ኹሉ አዳነ። ከእኛ፡ መርገመ ሥጋን፥ መርገመ ነፍስን አጠፋልን። በመስቀሉም፡ እኛን፡ እርስ በርሳችን፥ ከእግዚአብሔርም ጋር አስታርቆን፡ በመካከላችን ሰላምን አደረገ። በልዩ ትንሣኤውም፡ ሰውን፡ ወደ ገነት መልሶ አገባው።

## ምዕራፍ ፳፤ ጸሎት::
## የሴቶች ርኵሰትና መርገም: በቅድስናና በበረከት ስለመተካቱ::

---

*ደ. ቅዱሳን ሰብአ ሰገል ባዩት ጊዜ: እጅግ ደስ ብሏቸው የተከተሉትን ብሩህ ኮከብ: ከአንቺ አውጥተሽ ያስገኘሽ: እማናዊቷ ምሥራቅ አንቺ ነሽ! ከእርሱም: ሔዋን: "በጣር: በጭንቅ: ልጆችን ውለጂ!" የሚለውን የእርግማን ድምፅ ሰምታ ነበር:: አንቺ: ድንግል ማርያም ግን: "ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ!" የሚል የበረከትን ድምፅ ሰምተሽ: ሰው ኾኖ ያዳነንን: እርሱን: የፍጥረቱ ኹሉ ጌታ አምላክ፥ መሐሪና ሰው ወዳጅ የኾነውን ንጉሥ ወለድሽልን:: ስለዚህም ነገር: በመልእኩ በቅዱስ ገብርኤል ቃል: እኛም: "ድንግል ማርያም ሆይ! አንቺ: በእግዚአብሔር የተባረክሽ ነሽ! ማሕፀንሽ: በረከተ ሥጋን፥ በረከተ ነፍስን የሚያድለውን: የሕይወት ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስን አስገኝቷልና!*

እነዚህን ቃላት: የዘወትር ጸሎት አድርገን የምንጸልያቸው ለምንድር ነው? የሃይማኖታችን መገለጫዎች ስለኾኑ፥ ማለትም: ስላመንንባቸው አይደለምን? አለዚያማ: የክርስትናን ዘውድ የተቀዳጀው: የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችን: ይህን የጸጋ ክብሩን ተገፍፎ: ሃይማኖትነቱ ሊቀር አይደለምን? በምግባር የማይገለጥና የማይፈጸም ሃይማኖትስ: "ሃይማኖት" ሊባል ከቶ ይቻላልን? አይቻልም::

እንግዲህ: ሴት: የወር አበባ በማየቷና ልጅን በመውለዷ ምክንያት: ከሔዋን ጀምሮ: በኪዳነ ልቦና፥ በተለይም: በኪዳነ ኦሪቱ የኾኑኔ ዘመናት: በርኵስነትና በመርገም ቀንበር ታሥራ የኖረችበትን የውርደት ኑሮ: አኹንም: በቅድስት ድንግል ማርያምና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው: በአዲስ ኪዳኑ የምሕረትና የበረከት ዘመን: በዚያው መልክ እንድትቀጥል ማድረግ: የኦሪቱ ሕግ እንደጸና ኾኖ፥ አምላክ: በሰውነት መጥቶ የፈጸመው መሥዋዕትነቱና ቤዛነቱ ኹሉ: "ከንቱ ይኹን! መና ኾኖም ይቅር!" ማለት አይደለምን? እንዲህ: ከመርገምና ከርኵሰት፥ ለዲያብሎስ ከመገዛትና ከኃጢአት ቀንበር፥ ከሞት ፍዳ ሳይቀር ነጻ መውጣታቸውን: በሃይማኖት አውቀው የተቀበሉት ኢትዮጵያውያት ሴቶችስ: ይህን የአስተሳሰብና የአሠራር ጭቈና: እንዴት አድርገው: በእየራሳቸው ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ፈቅደው ሊቀጥሉበት ቻሉ?

አያችሁ! ዲያብሎስና አገልጋዮቹ ሠራዊት: እስከዛሬ ድረስ: በእናቶቻችን፥ እኅቶቻችንና ልጆቻችን ላይ ሲፈጽሙት የኖሩትን፥ ዛሬም እየፈጸሙት ያለውን ረቂቅ ደባ!? ማለትም: እኒሁ ሴቶቻችን: በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ምክንያት: በቅድስናና በበረከት የተተካውን የወር አበባቸውን መርገምና የወላድነታቸውን ርኵሰት: ገና እንደጸና አድርገው እንዲመለከቱት በማድረግ: የሚፈጽሙትን ደባ!? ይህ: ከፉ ድርጊታቸው: ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት: ቅዱስ ቍርባንን እንዳይቀበሉ፥ ይልቁንም: ከእርሱ እንዲርቁ ከሚደረገው ጽኑ ጥረት ጋር: ተመሳሳይ መኾኑን: በማስተዋል ልትመለከቱት ይገባችኋል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይህ ደባ፡ አኹንም እየቀጠለ በመኼድ ላይ ያለው፡ *"በሔዋን ምክንያት፡ የተዘጋው የገነት ደጅ፡ በድንግል ማርያም ምክንያት፡ ዳግመኛ ተከፈተልን። እኛን ከመውደዱ የተነሣ፡ ከእርሷ፡ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም የመጣው፤ በመስቀል ላይ ተሠውቶም፡ ከዲያብሎስ፥ ከኃጢአትና ከሞት ያዳነን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከገነት የሕይወት ዛፍ ፍሬ እንበላ ዘንድ አደለን። ይህም፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ፡ "እንካችሁ፡ ብሉ! ንሡ፡ ጠጡ!" ብሎ፡ በምሴተ ሐሙስ የሰጠን፡ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው።"* የሚለውን ቃል፡ በዘወትሩ የውዳሴ ማርያም ጸሎታችን ውስጥ ባለማስታጐል ማነብነባችን ሳይቋረጥ መኾኑንም አትዘንጉ!

ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ *"እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፡ እንግዲህ፡ ሰው አይለየው! ...ብዙ! ተባዙ! ምድርንም ሙሉአት!"* የሚለውን መለኮታዊ ቃል በመከተል፡ ከተፈጸመ የጋብቻ አንድነት፡ ሰውን የሚያህል ፍጡርን እንዲያስገኝ፡ በፈጣሪ፡ ድንቅ ጥበብ የተሠራው፡ የወር አበባ ሥርዓትና የወላዲነት ጸጋ፡ በራሷ በሔዋንና በሴቶች ልጆቿ ስሕተት፡ ለርኵሰትና ለመርገም መዳረጉ፡ እጅግ ሲያሳዝንና ሲያስተክዝ መኖሩ ይታወቃል፤ በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ያው የፈጣሪ ቸርነት፡ በንጽሕናዋ፡ አምላክን ለመውለድ በበቃችው፡ በድንግል ማርያም ላይ በፈጸመው፡ የቅድስናና የበረከት ሥራ፡ ይኸው፡ የወር አበባ ሥርዓትና የወላዲነት ጸጋ፡ ወደቀደመ ክብሩ መመለሱን፡ እነሆ፡ አኹን፡ በሚበቃ ተረድታችሁታል።

ስለዚህ፡ በዚህ ውይይታችን ላይ፡ አግባብ በየኾነበት ቦታ ኹሉ፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየተጠቀሰ በተብራራላችሁ መሠረት፡ በቀዳማውያኑ አዳምና ሔዋን ምክንያት፡ በሰው ልጆች ላይ ጸንቶ የኖረው፡ የአሪቱ የርኵሰትና የመርገም ቀንበር፡ በዳግማዊው አዳም፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በዳግማዊቷ ሔዋን፡ በድንግል ማርያም ምክንያት፡ እንዲህ፡ የተሻረና የተወገደ መኾኑ ሊታበል፤ ሊያከራክርም ከቶ አይቻልም።

ከዚህ የተነሣ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያት ሴቶቻችን፡ በወር አበባቸው ጊዜ፡ በየራሳቸው ፍላጎትና ፈቃድ፡ አካላዊውን ንጽሕናቸውን ለመጠበቅ ካልኾነ በቀር፤ ወይም፡ በወሊድ ግዳጃቸው ጊዜ፡ የውስጥና የውጭ መላ ሰውነታቸው፡ ከጽንሰት ጀምሮ ከቆየበት ድካሙ እስኪበረታ ድረስ፡ እየታረሱ እንዲሰነብቱ ለማድረግ ካልኾነ በቀር፡ ወደቤተ ክርስቲያን ከመግባት፥ የተለመደውን ንሥሓቸውንም እየፈጸሙ፡ ቅዱስ ቊርባንንና ሌሎቹን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ከመቀበል የሚከለክላቸው ምንም ነገር እንደሌለ ሊታውቁት ይገባችኋል።

### ለድንግል ማርያም ስለሚቀርበው ምስጋናና ስግደት።

*ጥያቄ:- ወደሌላ ርእስ ከመሻገራችን በፊት፡ በዚሁ፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን በሚመለከተው ውይይታችን ላይ፡ ልታስረዳን የምንፈልገው፡ አንድ ጥያቄ አለን።*

# ምዕራፍ ፰፡ ጸሎት።
# ለድንግል ማርያም ስለሚቀርበው ምስጋናና ስግደት።

*ይኸውም፡ በዘወትሩ ጸሎታችን መግቢያ፡ ለእግዚአብሔር ከምናቀርበው ስግደትና ምስጋና ጋር፡ "አምላክን ለወለደች፡ ለድንግል ማርያም፡ እንሰግዳለን! ምስጋናም እናቀርባለን!"፡ "እየሰገድንልሽ፡ ሰላምታን እናቀርብልሻለን!" በማለት፡ ለእመቤታችን ስለምናቀርበው ምስጋናና ስግደት ነው፡ ታዲያ፡ በዚህ አድራጎታችን፡ ምንም እንኳ፡ የአምላክ እናት ብትኾን፡ መቼም፡ ፍጹም ሰው ናትና፡ እርሷን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከል አይኾንብንምን?*

*መልስ፡-* በግእዙ፡ *"ንሰግድ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ!"፡ "ስብሐት ለእግዝእትነ ማርያም፡ ድንግል ወላዲተ አምላክ!" እና "ሰላም ለኪ፡ እንዘ ንሰግድ! ንብለኪ ማርያም እምነ!"* በምንለው፡ በዚህ የምስጋና ቃላችን፡ ፍጹም ሰው የኾነችውን፡ እርሷን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከልም፡ ባለማስተካከልም ነው።

ምስጋናውና ስግደቱ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ባለማስተካከል የሚኾነው፡ እርሷ፡ እንደማናቸውም ሰው፡ ራሳቸው ሰዎች ከኾኑት፡ ከአባቷ አብራክ ወጥታ፡ በእናቷ ማሕፀን፡ በንጹሐ ጠባይዕ ተፀንሳ የተወለደች በመኾኗ ነው፡ ማለትም፡ የእርሷ ጽንሰትና ልደት፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከእርሷ፡ በድንግልና ተፀንሶ፡ በድንግልና እንደተወለደው፡ የመለኮትነት አካልና ባሕርይ እንዳለው፡ እንደልጇ፡ እንደኢየሱስ ክርስቶስ ሳይኾን፡ የእርሷ፡ እንደዕሩቅ ብእሲ በመኾኑ ነው።

ምስጋናውና ስግደቱ፡ ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከል የሚኾነውም፡ እግዚአብሔር ወልድን በመውለዷ፡ ከዚህ የተነሣም፡ የአምላክ እናት በመኾኗ፡ ደግሞም፡ ቀደም ብለን እንደተወያየንበት፡ ከልጅ፡ እናት ስለምትበልጥ፡ እንዲሁም፡ "አምላክ፡ ሰው ኾነ!" የተባለው ትንቢታዊ ቃል፡ በልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ እሙንና እውን ኾኖ እንደተፈጸመ ኹሉ፡ "ሰው፡ አምላክ ኾነ!" የሚለው የቅዱሳት መጻሕፍትም ቃል፡ እንዲሁ፡ በእርሷ፡ እሙንና እውን ኾኖ ተፈጽሚል ብሎ ማመን አግባብ በመኾኑ ነው።

እንደመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ ከሰብአውያን ፍጡሮች መካከል፡ ፍጹም የተለየችና የበቃች ኾና ለተገኘች፡ ለአንዲቷ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊት ድንግል፡ ራሷን፡ ለአምላክ እናትነት ለማብቃት መቻል፡ ከአምላክነት ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ይህን እውነታም፡ አይሁድ፡ ልጇን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊወግሩት፡ ድንጋይ ባነሡበት ጊዜ፡ *"በምን ምክንያት ትወግሩኛላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው። አይሁድም፡ 'አንተ፡ ሰው ስትኾን፡ ራስህን እግዚአብሔር በማድረግህ፡ በዚህ ስድብህ ምክንያት እንጂ፡ ስለመልካም ሥራ አንወግርህም፡' አሉት። ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡ "እኔ ግን፡ 'አማልክት ናችሁ!' አልሁ፡" ተብሎ፡ በኦሪታችሁ ተጽፎ የለምን? የእግዚአብሔር ቃል፡ ወደእነርሱ የመጣላቸውን፡ እነዚያን፡ 'አማልክት' ካላቸው፡ ይህ፡ የመጽሐፍ ቃል፡ ሊፈርስ፡ ሊታበልም አይቻልም።"* ብሎ በመለሰላቸው መለኮታዊ ቃሉ አረጋግጦታል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ስለዚህ፡ *"የእግዚአብሔር ቃል፡ ወደእነርሱ የመጣላቸውን እነዚያን ቅዱሳን ሰዎች፡ 'አማልክት' ካላቸው፡* እኛም፡ በነግሁ የኪዳን ጸሎታችን፡ *"ዘፈጠርከ ሕሊናተ ርቱዓተ፡ ለእለ የአምኑ ብከ፡ ከመ እምሰብእ ይኩኑ አማልክተ!"* ማለትም፡ *"ለሚያምኑብህ፡ ንጹሓ ልቡናን ሰጥተህ፡ ከሰው ወገን 'አማልክት' እንዲባሉ የምታበቃ!"* የምንል ከኾነ፡ ራሱን፡ እግዚአብሔርን፡ በእናትነት ለመውለድ፡ አጥብታም ለማሳደግ፡ በአካለ ሥጋም፡ እስከዕርገቱ ድረስ ሳትለየው ለመቆየት፡ ወደሰማየትም ዐርጋ፡ እስከዛሬና ዛሬ፡ ለዘለዓለምም፡ በሕያውነት አብሬው፡ በንግሥና ለመኖር የበቃችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያምማ፡ የአምላክነት ደረጃ ተሰጥቷት፡ እንደአምላክ ብትመሰገን፡ ቢሰገድላትም፡ ምን ያስደንቃል? አያስደንቅም። "ምን ይደንቅ! ምን ይረቅ!" የሚያስሰኘውስ፡ ድንግሊቱ፡ ለዚህ ታላቅ ጸጋ እንድትበቃ ያስቻላትን ሥልጣንና መብት፡ ለእርሷ ብቻ ሳይኾን፡ በተፈጥሮ፡ ለሰው ልጅ ኹሉ የሰጠ፡ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበብና ቸርነት ነው።

እንግዲህ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚህ ደረጃና መልክ፡ መመስገን የሚገባት መኾኑን፡ እናንተም፡ በማስተዋል ተመልክታችሁት፡ በሃይማኖት እንድታጸኑት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ ያስገነዝባችኋል።

## ሥርዓተ ጸሎት።

ጥያቄ፦ *ለእነዚህ፡ ላቀረብናቸው ጥያቄዎቻችን፡ በሰጠኸን ማብራሪያ ስለረካን፡ "እግዜር ይስጥልን!" እንልሃለን። ቀጥሎም፡ ቀደም ብለንና እስካኹን የሰማናቸውን ጸሎቶች፡ እየካኼድን የምንፈጽመው፡ እንዴት እንደኾነ፡ ሥርዓቱን ዘርዝረህ ብታስረዳን?*

መልስ፦ ጸሎት፡ ፈጣሪ ዓለማትና አምላከ አማልክት፡ ሊቀ ካህናትና ንጉሠ ነገሥት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከንግሥት እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር፡ ማንኛውንም ፈቃደኛ የኾነ ፍጡራቸውን ለመቀበል፡ በተቀመጡበት ዙፋናቸው ፊት፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮ፡ አቅርበው የሚያነጋግሩበት ሥርዓት ስለኾነ፡ ጸሎተኛው፡ በንቃትና በትጋት፡ ቀጥ ብሎ ቊሞ ሊፈጽመው የሚገባው ምግባር ነው። ጸሎቱ፡ በልብ ብቻ፡ በአንደበት፡ ማለትም፡ በቃል፡ ወይም በንባብ፡ በዜማና በመዝሙርም ሊኾን ይችላል።

ስለዚህ፡ ለመጀመሪያው ጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፡ በቅድሚያ፡ ከመኝታችሁ ተነሥታችሁና በንጽሕና ቤት ተጸዳድታችሁ፤ እጅና ፊታችሁንም ተጣጥባችሁ፤ በአግባብ ለብሳችሁና የአገር ልብስ ከደረባችሁ፡ አደግድጋችሁ ልትገኙ ያስፈልጋችኋል። ከዚያ፡ ፊታችሁ፡ ወደምሥራቅ (ወደፀሓይ መውጫ) ሊኾን ይገባል።

# ምዕራፍ ፳፡ ጸሎት፡፡
## ሥርዓተ ጸሎት፡፡

ባላችሁበት ቦታ፡ ምሥራቁን ማወቅ ቢሣናችሁ፡ ወይም፡ ያን አግጣጫ ለመያዝ የሚያዳግት ኹኔታ ቢያጋጥማችሁ፡ እግዚአብሔር፡ በኹሉ የመላ ስለኾነ፡ ፊታችሁ፡ ወደማናቸውም ማዕዘን ሊያቀና ይችላል፡፡ አለዚያ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ በአካባቢያችሁ ካለ፡ ወደዚያ ማቅናት መልካም ነው፡፡ በዓፀደ ቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ በምትገኙበት ጊዜ ግን፡ ፊታችሁ፡ ምንጊዜም፡ ወደመቅደሱ መኾን አለበት፡፡

የሃይማኖት አምልኳችን፡ በእውነትና በመንፈስ የሚፈጸም በመኾኑ፡ በፊታችሁ፡ ምንም ዓይነት የአምልኮ ምልክት ባይኖር ግድ የለም፡ በግድ፡ መኖር አለበት የሚያሰኝ ሥርዓት የለንም፡፡ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ካላችሁ ግን፡ የምስለ ፍቁር ወልዳ ኢትዮጵያዊ ሥዕል (እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ ተወዳጅ ልጇን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን አቅፋ፡ በእርሱ፡ በቀኙ፡ የምትታይበት) እና/ወይም የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስቅለት የሚያዘክር የመስቀል ምልክት መኾን ይኖርበታል፡፡ ርኩስ መንፈስ የሚጠላቸውና የሚሸሻቸው ቅዱሳት መንፈሳውያት ኀይላት ቢኖሩ፡ እኒህ፡ ኹለት ምሥጢራት፡ ማለትም፡ የድንግል ማርያምና የመስቀል አጠራር፡ ሥዕልና ምልክት ናቸው፡፡

የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል፡ ኢትዮጵያዊት መልክ ያላት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እርሷ በስተቀኝ ኾና፡ ሕፃን ልጇን፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳቀፈች፡ በመንበረ መንግሥት ተቀምጣ፡ ቅዱሳን ሊቃነ መላእክት፡ ሚካኤልና ገብርኤል፡ በቀኝና በግራ ቆመው የሚታዩበት እንዲኾን ያስፈልጋል፡፡ ድንግል ማርያምና ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለየብቻቸው ኾነው የሚታዩበት ሥዕል፡ አብረውም ኾነው፡ በነጭ መልክ የተሣለው ሥዕል፡ የኢትዮጵያውያን አይደለምና፡ ካልታጣ በቀር፡ እንዳትገለገሉበት ተጠንቀቁ! የመስቀሉ ምልክት ግን፡ ሥነ ስቅለቱ ያለበት፡ ወይም፡ የሌለበት ሊጣ፡ ከእንጨት፡ ወይም፡ ከሌላ፡ ከማናቸውም ንጥረ ነገር የተሠራ ሊኾን ይችላል፡፡

ማናቸውንም ዓይነት ሸማ ለብሳችሁ ከኾነ፡ በቀኝና በግራ፡ ማደግደግ ይኖርባችኋል፡ ድግድጋቱም፡ ከወገብ ወይም ከትከሻ ሊኾን ይችላል፡ ከወገብ ሲኾን፡ ከዙርያ ትጥቅ ተነሥቶ፡ በቀኝ ጀርባ በኩል ወደትከሻ ወጥቶ፡ በቀኝ ደረት በኩል ወደወገብ ትጥቅ የሚመለሰው፡ የጥንግ ድርብ፡ ሙሉ ድግድጋት ሊኾንም ይችላል ፡፡ ወንድ አይከናነብም፡ ሴት ግን እንድትከናነብ፡ ተፈጥሮ ብቻ ሳትኾን፡ ባህላችንም፡ ሥርዓታችንም ይደግፋታል፡፡

በጸሎት ጊዜ፡ የነፍስና የሥጋ አካሎቻችሁ፡ በአስተሳሰባቸው ተለያይተው ሳይባክኑ፡ በመንፈሳዊው ቅዱስ አካላችሁ፡ አንድ መኾናቸውን፡ "እኔ" የምትሏት የራሳችሁ ነፍስ፡ ራሷን በመቆጣጠር፡ ማረጋገጥ አለባት፡፡ አምልኳችሁ የሚፈጸመው፡ የቆማችሁትም፡ በራሳችሁ ልቦና ውስጥ፡ በዓይነ ኅሊናም፡ ዐፊታችሁ በተዘረጋው፡ በእናትና ልጇ፡ ማለትም፡ በካህኑ ንጉሥ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በንግሥት እናቱ፡ ድንግል ማርያም መለኮታዊ ዙፋን ፊት መኾኑን፡ እነርሱና እናንተም፡ በዚያች ሰዓት፡ በእውነትና በመንፈስ እየተነጋገራችሁ መኾኑን፡ ለአንዲት ቅጽበት እንኳ መዘንጋት የለባችሁም፡፡ በጸሎታችሁ መካከል፡ አሳባችሁ፡ ወደሌላ በሚባዝንበት ጊዜ፡ ወደመንፈሳዊው ልቦናችሁ፡ በፍጥነት ልትመልሱት ይገባል፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፥
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ጸሎቱ፡ በግእዝ ወይም በኢትዮጵያኛ ሊደረግ ይችላል። ዓቅማችሁ በፈቀደ መጠን ግን፡ ጸሎቱን፡ በመጽሐፍ በመመልከት ብቻ ሳይኾን፡ በቃላችሁም ልትጸልዩት የምትችሉ ቢኾን፡ ይበጃል፡ ምክንያቱም፡ በየግል ሰውነታችሁ፡ ወይም፡ በአገር ደረጃ፡ የፈተናና የመከራ ዘመን በሚመጣባችሁ ጊዜ፡ ምናልባት፡ መጽሐፉን ለመያዝ፡ ወይም፡ ለማግኘት በማያዳግታችሁ ኹኔታ ላይ መውደቅ ይደርስ ይኾናልና።

እንግዲህ፡ በግልም ኾነ በጋራ፡ ወይም፡ በማኅበር የሚካኼደውን ጸሎት፡ ከመክፈቻው አንሥቶ፡ እስከፍጻሜው፡ ከንሥርዓቱ ያካተተው ልዩ መጽሐፍ፡ ራሱን በቻለ መልክ ተዘጋጅቶ፡ በዚህ ውይይታችን መጨረሻ ላይ እንድታገኙት ስለሚደረግ፡ በዚያ እየተከታተላችሁ መገልገል ነው።

## የጸሎት ጊዜያት።

*ጥያቄ፦ ይህን የመሰለውን ጸሎት፡ ማድረግ የሚገባን መቼ፡ መቼ ነው? በቀን፡ መጸለይ ያለብንስ፡ስንት ጊዜ ነው?*

መልስ፦ በመሠረቱ፡ ከተመቸንና ከቻልን፡ በየዕለቱ፡ ለፈጣሪያችንና አምላካችን፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ ምስጋናንና አምልኮን፡ ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያምና ለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል አክብሮትንና ሰላምታን፡ ለጻድቃንና ሰማዕታት፡ ለቅዱሳን መላእክትም እንክሮንና ተዘክሮን እንድናቀርብባቸው፡ የተመደቡልን የጸሎት ጊዜያት፡ ፯ (ሰባት) ናቸው፡ የእነዚህ ጊዜያት አመዳደብ፡ ራሱን የቻለ በቂ ምክንያት አለው፡ ዝርዝራቸው፡ እንደሚከተለው ቀርቧል፡

የመጀመሪያው፡ "የነግህ ጸሎት" ይባላል። ፀሓይ ሳይወጣ፡ ከእንቅልፍ እንደነቁ፡ ከመኝታ ተነሥተው፡ ከንጋቱ፡ በ፩ ሰዓት ግድም ባለው ጊዜ፡ "የሌሊቱን ጨለማ አርቀህ፡ የቀኑን ብርሃን ያመጣህልን!" በማለት፡ የኹሉ አባት፡ አዳም፡ የተፈጠረባትን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፡ በጲላጦስ ፊት ቁሞ፡ የተመረመረባትን ሰዓት በማስታወስና በማሰብ የሚጸለይ ስለኾነ፡ "የነግህ ጸሎት" ተባለ፡

፪ኛው፡ "የ፫ ሰዓት ጸሎት" ይባላል። የኹሉ እናት ሔዋን የተፈጠረችበት፡ ነቢዩ ዳንኤል፡ በምርኮ በሚኖርባት በባቢሎን ኾኖ፡ በኢየሩሳሌም አንጻር ያለ፡ መስኮቱን ከፍቶ ይጸልይበት የነበረ፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ ሰማያዊ ብሥራትን ሰምታ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የፀነሰችበት፡ ኋላም፡ ጌታ፡ በጲላጦስ ፊት የተገረፈበት፡ በመጨረሻ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በጽርሐ ጽዮን፡ በሐዋርያት ላይ የወረደበት ሰዓት ስለኾነ፡ እነዚህን ድርጊቶችና ኹኔታዎች በማስታወስና በማሰብ፡ የ"፫ ሰዓት ጸሎት"ን እናደርጋለን።

# ምዕራፍ ፳፡ ጸሎት።
## የጸሎት ጊዜያት።

፫ኛው፡ "የ፮ ሰዓት ጸሎት" ይባላል። በቀትር፡ ከፀሓይ ሙቀት የተነሣ፡ ሰውነት ሲዝልና አእምሮ ሲበተን፡ አጋንንት ስለሚሠለጥኑ፡ ያን፡ የመናፍስት ጦር ለመከላከል፡ በተለይም፡ ጊዜው፡ ሄኖክ፡ ቤተ መቅደስን ያጠነበት፡ ይልቁንም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ስለኾነ፡ ያን ሕማማተ መስቀል በማሰብ፡ የምንጸልይበት ሰዓት ነው።

፬ኛው፡ "የ፱ ሰዓት ጸሎት" ይባላል። ይህች ሰዓት፡ መላእክት፡ የሰውን ምግባርና ጸሎት የሚያሳርጉባት፡ ከዚህም በላይ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተሰቅሎ ሳለ፡ በጦር ተወግቶ ደሙን ከማፍሰሱ በፊት፡ "ተፈጸመ!" ብሎ፡ ነፍሱን፡ ከሥጋው የለየባት ሰዓት ስለኾነች፡ በዚያ መንፈስ ኾነን፡ ጸሎታችንን የምናቀርብባት ጊዜ ናት።

፭ኛው፡ "የሠርክ ጸሎት" ይባላል። ከ፲፩ እስከ፲፪ ሰዓት ባለው የምሽት ጊዜ፡ የሚደረገው ጸሎት ነው። በጌታ ዳግም ምጽአት ይመሰላል። ሰው፡ ሲሠራ ውሎ፡ ዋጋውን፡ የውሎ አበሉን፡ ደመወዙን የሚቀበለው፡ በሠርክ እንደመኾኑ፡ ምእመናንም፡ ምግባር፡ ትሩፋታቸውን፡ ሲሠሩት ኖረው፡ ዋጋቸውን፡ ከፈጣሪያቸው የሚያገኙት፡ በዕለተ ምጽአት ስለኾነ፡ እንዲሁም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሕማማተ መስቀሉን ጨርሶ፡ ከተገነዘ በኋላ፡ በሥጋው፡ ወደመቃብር የወረደበት ጊዜ ስለኾነ፡ ያን፡ የመለኮት ፍቅር በማዘከር፡ በጸሎት የምንጠመድባት ወቅት ናት።

፮ኛው፡ "የማታ ጸሎት" ይባላል። ከመኝታ በፊት፡ ከምሽቱ ፫ ሰዓት ግድም ባለው ጊዜ፡ የሚጸለየው ነው። ፈጣሪያችን፡ በቸርነቱ፡ የቀኑን ድካም አሳልፎ፡ የሌሊቱን ዕረፍት ስላመጣልን፡ ደግሞም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምሴተ ሐሙስ፡ በአይሁድና በሮማውያን ወታደሮች እጅ ተይዞ፡ ከመታሠሩ በፊት፡ በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ፡ የጸለየው፡ በዚህ ጊዜ ስለነበረ፡ ያን፡ ስለእኛ ሲል፡ በጭንቀት ተሠቃይቶ፡ ከእኛ የሞት ፍርሃትን ያስወገደልን፡ ሞትንና በመቃብር መበስበስንም፡ በትንሣኤው አስወግዶ፡ የዘለዓለም ደስታንና ሕይወትን ያቀዳጀን መኾኑን በማሰብ፡ ለእርሱ፡ ምስጋናችንን ከማቅረብ ጋር፡ የምንጸልይበት ሰዓት ነው።

፯ኛው፡ "የእኩለ ሌሊት ጸሎት" ይባላል። የአፍላ እንቅልፋችንን፡ በመኝታ ካሳለፍን በኋላ፡ ከሌሊቱ ፮ ሰዓት ግድም ላይ፡ ነቅተንና ተነሥተን፡ ተጸዳድተንና እጃችንን ታጥበን የምናቀርበው የምስጋና ጸሎት ነው። መጸዳዳቱና መተጣጠቡ ያስፈለገው፡ ከተኛ ዘንድ፡ ምናልባት፡ የሰውነት አካል ማደፍ፥ ወይም፡ መጉደፍ አይቀርምና፡ ሰውነታችንን፡ ከዚያ፡ አንጽተን፡ በፈጣሪ ፊት ለመቅረብ ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህች፡ የመንፈቀ ሌሊት ሰዓት፡ ጳውሎስና ሲላስ፡ በእሥር ቤት ሣሉ፡ ጸልየው፡ በእግዚአብሔር ተአምራዊ ኃይል፡ ከእሥራታቸው የተፈቱባት፡ ከዚህም በላይ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደባት፡ የተጠመቀባት፡ የተነሣባትና ዳግመኛ የሚመጣባት ስለኾነች፡ "ፈጣሪ፡ ይህን ኹሉ የኾነው፡ ይህን ኹሉ የቸርነቱን ሥራ ያደረገውም፡ ለእኔ ሲል አይደለምን?" ብሎ፡ ይህን ላደረገ እግዚአብሔር፡ ምስጋናን በማቅረብ፡ የሚጸልዩባት ሰዓት ናት።

ከዚህ በኋላ፡ እስከነግህ የጸሎት ሰዓት፡ ያለው ጊዜ፡ የሌሊቱ ማረፊያችን ነው።

በእነዚህ ጊዜያት የምንጸልያቸውን ጸሎት፡ ባለመደጋገም፡ በ፳፬ቱ ሰዓቶች ውስጥ መከፋፈል፡ ከመከፈቻው ጸሎት ቀጥሎ የምናደርገውን የጸሎት መጠንና ዓይነት፡ ማለትም፡ አጭርም፡ መካከለኛም፡ ረዥምም እንዲኾን፡ በእየራሳችን መምረጥና መወሰን እንችላለን።

\+ + +